# በአብክመ ፍትህ ቢሮ
# የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ

ነሀሴ 2015 ዓ/ም

ባህርዳር፤

## ማውጫ


1. መግቢያ ....................................................................................................1

2. የ2015 በጀት ዓመት 12 ወራት የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ/የሁኔታ ዳሰሳ.......................4

2.1. ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁኔታ እና ዳሰሳ ............................................................4

2.1.1. ሀገራዊ ሁኔታ ............................................................................4

2.1.2. ክልላዊ ሁኔታ ............................................................................5

2.2. የለውጥ ተግባራትና የመልካም አስተዳደር አፈጻጸም ..........................................6

2.3. የአበይት ተግባራት አፈጻጸም ..........................................................................9

2.3.1. የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተግባራት አፈጻጸም ........................................9

2.3.2. በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ ......................................13

2.3.3. የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ጉዳዮች አፈጻጸም ...................................13

2.3.4. የሰነዶች ማረጋገጥ እና የጠበቆች ጉዳይ ተግባራት አፈጻጸም ..........................17

2.3.5. የህግ ምክር፣ ማርቀቅ እና ማጠቃለል ተግባራት አፈጻጸም ............................18

2.3.6. የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን በተመለከተ ....................................................19

2.3.8. የመስሪያ ቤቱ የኮምኒኬሽን ተግባራት አፈጻጸም .......................................25

2.3.9. የፍትሕ ባለሙያዎች ማሠልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት አፈጻጸምን በሚመለከት 27

3. ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች ..............................................................................30

4. የዕቅዱ መነሻዎች፣ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዓላማዎች፤ ግቦች እና የትኩረት አቅጣጫዎች......31

4.1. ለቀጣይ እቅዳችን መነሻዎች .........................................................................31

4.2. የትኩረት አቅጣጫዎች ..................................................................................32

4.3. ተልዕኮ ....................................................................................................32

4.4. ርዕይ.......................................................................................................32

4.5. የተቋሙ መሰረታዊ እሴቶች ...........................................................................32

4.6. የባለ ድርሻዎች እና የአጋር አካላት ትንተና፣ ...................................................33

4.7. የጥንካሬና የድክመት ማሳያዎች፣ የመልካም አጋጣሚና የስጋት መገለጫዎች ሰንጠረዥ፣... 40

4.8. ዓላማ፣ ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት ..............................................................47

ዓላማ 1፡-ተልዕኮውን ማሳካት የሚችል ጠንካራና ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ ኃይል መገንባት፤47

ዓላማ 2፡-መልካም አስተዳደርን በማስፈን ህ/ሰቡ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ያለውን አመኔታ ማሣደግ፤ ........ 52

ዓላማ 3፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ የሙስና፣ መደበኛ እና ኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ወንጀል ፈፃሚዎችን በማስቀጣት የህ/ሰቡን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ፤ ........ 58

ዓላማ 4፡-በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ጉዳዮች የመንግስትና የህዝብን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ ........ 66

ዓላማ 5፡- የሰብዓዊ መብት አያያዝና የስርዓተ ጾታ ጉዳይን ማረጋገጥ ........ 75

ዓላማ 6፡-በኢንፎርሜሽን፣ ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም፣ እንዲሁም የተደራሽነት ውጤታማነትን ማሳደግ፣ ........ 79

5. የማስፈጸሚያ ተቋማዊ አቅም፣ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ........ 83

6. የፋይናንስ አቅም ........ 83

7. ዋና ዋና የማስፈፀሚያ ስልቶች፣የእቅድ አፈጻጸም ክትትል፣ ግምገማና ምዘና ስርዓት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ........ 84

# 1. መግቢያ

የክልሉ መንግስት የረጅም ጊዜ ዕቅዶችን በማውጣት በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ መስኮች የተያዙ ግቦችን ለማሳካት እንዲሁም የፍትህ ዘርፉን የአገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል የህብረተሰቡን ፍትህ የማግኘት መብት በማስከበር የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። የአብክመ ፍትህ ቢሮም በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ በማድረግ ሕዝብና መንግሥት የሚጠብቁትን ውጤት ለማሳካት ከ10 ዓመት (2013-2022) መሪ ዕቅድ የተቀዳ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት በርካታ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል። በዕቅድ ዘመኑ ተቋሙ ተልዕኮውን በብቃት የሚወጣ ጠንካራ ህግ አስከባሪ ተቋም ለመገንባት የአሰራርና የአደረጃጀት ስርአቶችን እንደገና በመፈተሽና ከነበሩት ተጨማሪ አዳዲስ አደረጃጀቶችን ወደ ስራ በማስገባት ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

በ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ የነበረው የሰሜን ጦርነት እስከ 2014 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የቆየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በደረሰው ጉዳት በርካታ መሰረተ ልማቶች ወደ ነበሩበት ያልተመለሱ ከመሆኑም በተጨማሪ በክልላችን የሕግ የበላይነት ከማረጋገጥ አንፃር አሁኑም የሚታዩ ችግሮች በመኖራቸው እና ሰላም በሚፈለገው መጠን አለመረጋገጡ በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ለሁለንተንተናዊ ልማት/ ዕድገት ዋነኛ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም ይህንን ሁኔታ ከመሰረቱ ለመለወጥ መንግስት ከህወሃትና ሌሎች ሀይሎች ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ወደ ሰላም ልንመጣ የምንችልበት ዕድል ቢኖርም በክልሉ ውስጥ እየታዩ ያሉ አለመረጋጋትና የሰላም እጦት ችግር የክልላችንን ህዝብ እፈተነው ይገኛል። ስለሆነም መንግስት ቁርጠኛ አቋም በመያዝ ህገ ወጥ የሆኑ ተግባራትን ለመከላከል እና የዜጎችን ሰላም ለማረጋገጥ የሕግና ስርዓትን ለማስፈን ተግባራዊ እርምጃዎች መውሰድ ጀምሯል። በዚህ መሰረት የሕግ የበላይነት በማረጋገጥ የሕግ፣ የፍትሕና የተቋማት ማሻሻያ ስራ እየተከናወነ ነው።

የአብክመ ፍትህ ቢሮም በዘርፉ በሚደረጉ የሕግና ፍትሕ ስርዓት ማስፈን ላይ ከሚመለከታቸው አካላት እና ከሕብረተሰቡ ጋር የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በተለይም ተቋሙ የሕግ የበላይነት የማረጋገጥ ቁልፍ ሀላፊነት የተጣለበት መሆኑን በውል በመገንዘብ በዚህ ረገድ መሰረታዊ ተቋማዊና የአሰራር ለውጥ ለማምጣት ዕቅዱን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም መሰረት መሰረታዊ የሕግና የፍትሕ ችግሮችን በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ችግሮቹን ለመቅረፍና ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት አደረጃጀትና አሰራር በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ በመንቀሳቀስ የተለያዩ ውጤቶችን ማስገኘት ጀምሯል። በመሆኑም የሕግ የበላይነት

ለማረጋገጥ የሕግ ጥሰቶችን የማረምና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ቢሮአችን እየሰራ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በህግ ማስከበርና ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ከባባድ የምርመራ ስራዎችን ከፌዴራል ፍትህ ሚኒስቴርና ከፖሊስ ጋር በርካታ ተግባራት ተከናውነው የምርመራ ውጤቶች ይፋ ተደርገዋል፡፡ በምስራቅና ምዕራብ አማራ ቀጠናዎችም የባለሙያዎች ቡድን ተንቀሳቅሶ በፍትህ ተቋማቱ እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮችን በመለየት የጋራ መግባባት የተደረሰበት በመሆኑ የፍትህ አካላት የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም የፍትህ አካላት የጋራ መድረክ ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቶ ቆይቷል፡፡

በቢሮው የተለያዩ ስራዎች ቢሰሩም የህግ የበላይትን ለማረጋገጥ በርካታ ተግዳሮቶች ሃገሪቱን፣ ክልላችንና የፍትሕ ዘርፉን ሲፈታተኑት ይስተዋላሉ፡፡ በተለይም በመብትና ግዴታ፣ በነጻነትና በሃላፊነት መሃል እንዲሁም በሰብአዊ መብትና ደህንነት በማስጠበቅ መካከል ያለውን ሚዛን ባለመጠበቅና የመብት ጥያቄን በሃይል ለማስፈፀም በሚደረጉ የተደራጁ ሕገ ወጥ ተግባራት የሚታዩ የስርአት አልበኝነት አዝማሚያዎችና በሃገሪቱና የክልላችን አካባቢዎች የተከሰቱና እየተከሰቱ ያሉት ብሄርና ሀይማኖት ተኮር ግጭቶች በዚህም የተነሳ የደረሰው የዜጎች ሞትና መፈናቀል፣ በአጠቃላይ በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት መድረስ፣ እንዲሁም ህገ ወጥ የጦር መሳሪያና የገንዘብ ዝውውር፣ የሀይማኖት ግጭት ለመፍጠር ያሉ መኩራዎች፣ የሀሰት ወሬዎችና የጥላቻ ንግግር መስፋፋት፣ ህግና ስርአትን የሚገዳደር፣ የህግ የበላይነትን የሚፈታተን የወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የህዝብና የመንግስትን ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ውስንነት እና ተቋማዊ አገልግሎቱ ደካማ ከመሆኑም በተጨማሪ የተቋማት ግንባታና ጅምር ለውጡ ተቋማዊ አለመሆኑ ተግዳሮቱ ፈታኝ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በተጨማሪ ቢሮአችን እስካሁን ያከናወናቸው ተግባራት በሕግ ከተሰጠው ተልዕኮ፣ ከህዝብና መንግስት የለውጥ ፍላጎት አንጻር ሲገመገምና ከላይ ከተጠቀሱት ወሳኝ ስኬቶችና ተግዳሮቶች በመነሳት መሰረታዊና ስትራተጂያዊ እይታ የሚጠይቁ ጉዳዮች መኖራቸው ግልፅ ነው፡፡ በተለይም የለውጡን ቀጣይነት ወደ ተሻለ ከፍታ ለማድረስና የሕግና የፍትሕ ማሻሻያው ውጤታማነት ለማረጋገጥ የመንግስት፣ የፍትሕ ዘርፉ አመራር፣ የባለሙያዎች፣ የባለድርሻ አካላትና ሕብረተሰቡ በማቀናጀት የሃገራችንና የክልላችን የፍትሕ ስርአት ገጽታ በመሰረቱ ለመቀየር የረጅም ጊዜ ስትራተጅያዊ ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር ስትራተጅያዊ አመራር መስጠት ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም በቢሮው የሕግና ፍትሕ ስርዓት የተገኙትን ውጤቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ጥራት ያለው ዕቅድ መቅረጽና መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ ከ10 ዓመቱ (2013-2022) የተቀዳ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

# 2. የ2015 በጀት ዓመት 12 ወራት የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ/የሁኔታ ዳሰሳ

## 2.1. ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁኔታ እና ዳሰሳ

### 2.1.1. ሀገራዊ ሁኔታ

በሀገራችን ከ2013-2014 የነበረው ከትግራይ ወራሪ ኃይል ጋር የተከሰተው ጦርነት ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራ ከማስከተሉም ባሻገር ተቋማት ወደነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ የሚደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ ከደረሰው ጉዳት አኳያ የሚጠበቀውን ያህል ስራ ባለመሰራቱ ቁሳዊ ጉዳቶችን ወደነበሩበት የመመለስ ስራው ጊዜ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በተለይ ክልላችን የችግሩ ከፍተኛው ገፈት ቀማሽ በመሆኑ ሀገራችን ካለችበት ሁኔታ ያለመረጋጋት፣ ስራ አጥነት መስፋፋት፣ የኑሮ ውድነት ችግር ለመውጣት በእንቅርት ላይ ጎሮ ደግፍ እንደሚባለው አሉታዊ ጎኑ የከፋ ሆኗል፡፡ ስለሆነም ፈጣን ሊባል የሚችል የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ በሀገራችን ሰላም፣ ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን መንግስትም ዋነኛ የለውጥ አጀንዳ አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደር በማስፈን ረገድ ያልተሻገርናቸው በርካታ ፈተናዎች እና ችግሮች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ በ2015 በጀት ዓመት በሕብረተሰቡ በርካታ ጥያቄዎች በየጊዜው ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ በተለይ በሃገራችን በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ዉስጥ የሕግ የበላይነት መስፈን ዋነኛ ምሰሶ በመሆኑ ህዝብ ከሚፈልገው አንፃር የፍትሕ ስርዓቱና ሕግ የማስከበር፣ የማስፈጸም ተልዕኮአችን ሰፊ ክፍተት ይታይበታል፡፡ በተጨማሪም የሕግ አስከባሪ ተቋማት ገለልተኛ፣ ለፍትህና ለሙያቸው ታማኝ፣ ለዜጎች መብት ቀናኢ እንዲሆኑ የሕዝብ ፍላጎት ቢሆንም ተቋማቱ ይህንን ፍላጎት በሚያሳካ ቁመና ላይ አለመሆናቸው፣ ሕግ ሁሉንም በዕኩል በመዳኘትና ዜጎች በተፈጥሮ ያላቸውን ሰብዓዊ ክብር በማስጠበቅ ረገድ ጥያቄ የሚነሳበት በመሆኑ በአገራችን ዴሞክራሲ እንዲያብብ፣ ነጻነትና ፍትሕ እንዲሰፋ፣ የሕግ የበላይነት ዕውን እንዲሆን አስፈላጊውን ማሻሻያ በማድረግ በዘርፉ ያለውን ክፍተት መሙላት ይጠይቃል፡፡ በሌላ መልኩ በሀገራችን በየቦታው አሁንም ግጭቶችና የህዝቦች መፈናቀል አለመቆሙ፣ የህብረተሰቡ የህግ የበላይነት አልተከበረም የሚል ስሜት መፈጠሩ፣ የወንጀል መከላከል ስራ በተፈለገው መልኩ አለመሆኑ ያልተፈቱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመሆኑም ፍትህ ቢሮ በፍትሕ ዘርፍ የሚካሄደው ለውጥ ዋነኛ አካል እንደመሆኑ ቢሮው ተነጻጻሪ ነጻነቱንና ገለልተኝነቱን በማረጋገጥ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ፍትሐዊነት ሁኔታ በማሻሻል፣ ሰብዓዊና ዲምክራሲያዊ መብቶችን በማክበርና በማስከበር በሕግ የተሰጠውን ኃላፊነት በሚገባ በመወጣት የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ ሥር ነቀል ለውጥ በማድረግ ሕዝብና መንግስት

የሚፈልጉትን ማሟላትና ሕዝቦች አመኔታ የሚጥሉበት ተቋም ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከሚፈለገው አንጻር በተለይም በሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ረገድ ያልተሻገርናቸው በርካታ ችግሮች ያሉ ሲሆን ለእነዚህ ችግሮች ምላሽ ከመስጠት ተዓማኒነትን ከማስፈን አንጻር ከፍተኛ ርብርብን የሚጠይቅበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ስለሆነም በዚህ ዕቅድ ውስጥ ቢሮውን የሚመለከት ሀገራዊ የዘርፉን ጉዳዮች ከተግባርና ሃላፊነቱ በመነሳት በተገቢው መንገድ መምራትና ማስፈፀም አስፈላጊ በመሆኑ ከላይ የተቀመጡት መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀም እንዲሁም ክፍተቶችና ፈተናዎችን በሚፈታ መልኩ ታሳቢ አድርጓል፡፡

### 2.1.2. ክልላዊ ሁኔታ

በክልላችን በአሁኑ ወቅት ያለው ሁኔታ በአንድ በኩል ከትግራይ ወራሪ ሃይል ጋር ያለው ጦርነት ያልተቋጨ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በክልሉ ውስጥ ያለው አለመረጋጋት፣ ሀይማኖት ተኮር ግጭቶች መኖር በህዝባችን ላይ ከፍተኛ ስጋት የደቀነ መሆኑና ፀረ ሰላም ኃይሎች ክልሉን የትርምስ ቀጠና ለማድረግ እያደረጉ ያለው ጥረት በአጭር ጊዜ ካልተቋጨ ክልሉን ከልማት ወደ ኋላ የሚያስቀር በመሆኑ በመንግስት በኩል ተገቢውን ትኩረት በመስጠት መስራትና ቢሮአችንም የሚጠበቅበትን ህግ የማስከበር ተግባር በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል፡፡ በክልሉ በተለይም ከአጎራባች ክልሎች አካባቢ አልፎ አልፎ የሚታዩ የሰላም መደፍረስ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ይህንን ችግር ከስሩ ለመፍታት ከዚህ ቀደም ሲሰሩ የቆዩ የአጎራባች ክልሎች የጋራ ውይይትና በጋራ ችግሮችን የመፍታት ስራ ተጠናቅሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ቢሮው ለህግ በላይነት መከበር ልዩ ልዩ ተግባራትን የሚያከናውን ቢሆንም አገልግሎት አሰጣጡን በወቅቱና በጥራት በመስጠት ዙሪያ ጉድለት ያለበት መሆኑ በፍትህና ፀጥታ ተቋማት የጋራ መድረክ ላይ የተገመገመ ነው፡፡ ስለሆነም በወረራው የወደሙ ተቋማትና የተቋረጡ አገልግሎቶች መልሶ ማደራጀትና አገልግሎቱን ማጠናከር ከወቅታዊ ሁኔታው ጋር በተያያዘ የሚነሱ የአስተሳሰብ መዛነፎችና የነበሩ ድክመቶችን በማረምና በማስተካከል ህግና ስርአት የተከበረበት ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ክልል ለመፍጠር መስራት ይጠበቅበታል፡፡

በሌላ በኩል ቢሮው በክልሉ መንግስት ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አንፃር በተለይም በወንጀል እና ፍትሃብሄራዊ ጉዳዮች ከአጋርና ባለድርሻ በጋራ መስራትና የሚጠበቅበትን ውጤታ ለማምጣት ይቻል ዘንድ ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የፍትህ መጓደል ጉዳዮችን በጥልቅ በመገንዘብ ክልሉ ያለበትን የሰላም መደፍረስ ችግር በየጊዜው በመፈተሽና በመፍታት ረገድ ያለውን ጉልህ ድርሻ

በአግባቡ ለመወጣት የሚችልበትን እና ህብረተሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያለውን አመኔታ የማሳደግ ጠንካራ ስራ መስራት የሚጠበቅበት ሲሆን ወንጀልን በመከላከል ረገድ ህብረተሰቡ ለፍትህ ስርዓቱ ውጤታማነት የአጋዥነት ሚናውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በፍትሃብሄራዊ ጉዳዮች በተለይም የአቅመ ደካሞችን መብትና ጥቅም የማስጠበቅ፣ የመንግስትን ተደራድሮ ጉዳዮችን የማስፈፀም ውጤታማነትን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## 2.2. የለውጥ ተግባራትና የመልካም አስተዳደር አፈጻጸም

በ2015 በጀት ዓመት ቢሮው በቁልፍ ተግባርነት ትኩረት አድርጐ ከሰራባቸው ዋነኛ ተግባራት መካከል አንዱ ተልዕኮውን ማሣካት የሚችል ብቃት ያለው በህዝብና በመንግስት አመኔታን ያተረፈ አመራር፣ ፈፃሚ ኃይልና ተቋም መገንባት ነው፡፡ በዚህም የባለሙያውን አቅም ለመገንባት ተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ ባለሙያ በተቀረፁ የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም፣ የለውጥ ኘሮግራሞች የተሟላ ግንዛቤ በመያዝና የለውጥ ኘሮግራሙን በመምራት በኩል ዐቃብያነ ህግ ጉዳዮችን በፓናል በማየት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ የተደረገው ጥረት የተደረገ ቢሆንም ወጥነት የሚጎድለው በመሆኑ ተከታታይነት ባለው መንገድ መከናወን ይኖርበታል፡፡

በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ያሉትን የሙስና እና ብልሹ አሰራር አመለካከትና ተግባራት ችግሮች በመለየት በየደረጃው ያለው አመራርና ባለሙያ ግልፅ ግንዛቤ እንዲይዝበት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ትውውቅ በተደረገበት ወቅት መግባባት ላይ የተደረሰበት ሲሆን በበጀት ዓመቱ በ3፣ 6 እና 9 ወራት የዕቅድ አፈፃፀነም የነበሩ ጥንካሬና ድክመቶችን በማሳየት ከአመራሩ ጋር የጋራ መግባባት የተደረሰበት፡፡ በተለይም በአመራሩና ፈፃሚ ኃይሉ የሚሰጡ ውሣኔዎች በልማት ቡድንና አደረጃጀቶች እንዲሁም በማኔጅመንት ኮሚቴው በየጊዜው የሚገመገሙበትና የጋራ እውቀት ተይዞባቸው የሚፈፀሙበት ግልፅ አሠራር የተዘረጋ ቢሆንም ተግባራዊ ማድረግ ላይ ወጥነት የሚጎድለው በመሆኑ ውስብስብ ጉዳዮች በጋራ በፖናል ታይተው ውሣኔ የሚሰጥበት አቅጣጫን በአግባቡ መተግባር የውሣኔ ጥራትን ከማሣደጉም በላይ በውሣኔ አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮች በፍጥነት የሚታረሙበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥል፡፡ ለዚህም በክልሉ መንግስት የወጣውን የለውጥ ስራ አመራርን እና የውጤት ተኮር ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተጨባጭ ማስረጃ በተገኘባቸው የስነ-ምግባር ጥሰት በፈፀሙ ዓቃቤያነ-ህግ፣ ጠበቆች ላይ ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተጠያቂነት አሠራርን

ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ በቀጣይም ችግሮችን እየለዩ ተገቢ ማስተካከያዎች ወቅቱን ጠብቀው መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

የዓቃቤያነ-ህግን አመለካከት፣ እውቀት፣ ክህሎትና ስነ-ምግባር ከወቅቱ የህብረተሰብ ፍላጐት ጋር ለማስኬድ በትምህርትና ስልጠና እና የለውጥ ኘሮግራሞችን አተገባበር መሠረት በማድረግ በሚካሄድ የስራ አፈፃፀም ግምገማ እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ከዘርፉ ጋር በተያያዙ ችግሮች ላይ ያተኮረ የግምገማዊ ስልጠና መድረኮች በማዘጋጀት ዓቃቤ ህጉን የማብቃት ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም መሰረት የአጫጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠናን በሚመለከትም በበጀት ዓመቱ በበርካታ ርእሶች ዙሪያ ለተለያዩ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

ከአብክመ ሴቶች እና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከጎንደርና ከደብረ-ማርቆስ ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር ከአጋር አካላት በተገኘ የበጀት ድጋፍ ለሴት ዐቃብያነ-ህግ በሴቶች እና ህፃናት የሀይል ጥቃቶች የህግ ማዕቀፎችና የህግ ምለሽ አሰጣጥ በተመለከተ ዙሪያ ለ270 ሴት ዐቃብያነ ህግ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዩኒሴፍ የበጀት እና የቴክኒክ ድጋፍ ለፖሊስ እና የፍትህ ጽ/ቤት የእቅድ ዝግጅት ባለሙያዎች በህጻናት ጋብቻ ወንጀሎች በመከላከልና በመረጃ አያያዝ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠና መድረኩ ላይ ወንድ 17 ሴት 18 ድምር 35 ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከኘላን ኢንተርናሽናል ጋር በህፃናት፣ በሴቶችና ልጃገረዶች መብት ዙሪያ ለፍትሕ እና ባለድርሻ አካላት መድረክ ስልጠና ወንድ 64፣ ሴት 20፣ በድምሩ 84 ሰዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከአለም አቀፉ ፍልሰት ድርጅት ጋር በመተባበር ለክልል፣ ዞን እና ወረዳ የህግ አስፈጻሚ አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፣ በስልጠናዉ ላይ ወንድ 29 ሴት 3 በድምሩ 32 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌደሬሽን /ኢሰማኮ/ ጋር በመተባበር በሰው የመነገድና ሰዎችን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀሎችን ለመከላከል የተደራጁ የትብብር ጥምረትና የስራ ቡድን አደረጃጀቶችን ለማጠናከር የሚረዳ ስልጠና ለፖሊስ፣ ለትብብር ጥምረት አባል ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በመድረኩ ወ-9 ሴት-12 በድምሩ 21 ባለሙያዎች ተሳታፊዎች ሆነዋል፡፡ ከአብክመ ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር በሴቶችና ህፃናት መብት ዙሪያ ለመምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በመድረኩ 170 ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከUSAID ጋር በመተባበር በሁለት ዙር የአመራር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናው ወ 91፣ ሴ 8 ድ 99 በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች ተሳተፊ ሆነዋል፡፡ 2 የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች በመሠረታዊ የህዝብ ግንኙነት እና የኮሙዩኒኬሽን ሙያ ላይ ትኩረት ያደረገ የ10 ቀን ስልጠና በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የስልጠና

ማዕከል ገብተው ሰልጥነዋል ። በጠቅላላ ለ711 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። በአጠቃላይ 711 ለሚሆኑ አመራርና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል።

የረጅም ጊዜ ስልጠናን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ ከክልሉ መንግስት ጋር በመተባበር 1 ዐ/ህግ በውጭ ሀገር የ3ኛ ዲግሪ ትምህርቱን እንዲከታተል ተልኳል። በጎንደር፣ በደብረ-ማርቆስና በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲዎች በሁለተኛ ዲግሪ መርሀ-ግብር ወንድ 57 ሴት 7 ድምር 64 ባለሙያዎች በመማር ላይ ይገኛሉ። ዲፕሎማ የነበሩ ዐ/ህግ በክረምት በመጀመሪያ ዲግሪ ወንድ 21 ሴት 9 ድምር 30 በደብረ-ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ መገኘታቸው፣ 8 በ2ተኛ ዲግሪ፣ 9 በመጀመሪያ ዲግሪ እና 1 በድፕሎማ በድምሩ 18 የአስተዳደር /ድጋፍ ሰጭ/ ሠራተኞች በማታና በርቀት ፕሮግራም ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል። ስለሆነም የሚሰጡ ስልጠናዎችን ፋይዳ መገምገም ይገባል።

በ2015 በጀት ዓመት የተቀመጡትን ግቦች ከማሣካትና ውጤትን ቀጣይነት ባለው መንገድ በማረጋገጥ ረገድ በሚፈለገው መንገድ የተገልጋዮችን እርካታ ያመጣ ነው ማለት አይቻልም። በየደረጃው ያለው አመራርና ፋጻሚ ሃይል በአመለካከት፣ ክህሎት፣ አሠራርና አደረጃጀት የሚታዩ ክፍተቶችን በአግባቡ ለይቶ ይህንን ሊፈታ የሚችል እቅድ በማዘጋጀት እና በመተግበር የአቅም ውስንነት ያለበት ነው።

በዘርፉ የተዘረጋው ቅንጅታዊ የአሠራርና የአደረጃጀት ስርዓቶች የዘርፉን ተቋማዊና ክልላዊ ራዕይ ለማሣካት ያለውን ከፍተኛ ፋይዳና ጠቀሜታ በእምነት የመያዝ ችግር ባይኖርም በባለቤትነት ያለመያዝ እና የዝግጁነት ማነስ ችግሮች ያሉበት ነው። እንዲሁም የጋራ መድረኮች አሠራር እና አደረጃጀትም የዘርፉን ዕድገት ለማስተግበር የሚያስችል የጋራ ክትትልና ድጋፍ ስርዓት ያልተዘረጋበት ከመሆኑም ሌላ መድረኮች መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጡ ክልላዊ አጀንዳዎች የህዝብ ንቅናቄን በመፍጠር የለውጥ ስራን ቀጣይነት የሚያረጋግጡ በመሆን በኩል ጉድለት የነበረባቸው ነበሩ።

በዚህም ምክንያት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራሙን በጋራ በመገምገም ወቅታዊ ችግሮችን በመፍታት ውጤታማ የማሻሻያ ስራዎችያ ለመስራት የለውጥ መሣሪያዎችንም ወጥና ተነባቢ ሆነው እንዲፈፀሙ ያለማድረግ፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች በጋራ ያለማከናወን እና በለውጥ ንቅናቄ የሚገኙ የአመለካከት፣ የእውቀትና የስነ-ምግባር ችግሮች በጋራ ለይቶ ያለመፍታት ችግሮች በስፋት ስለሚታዩ በቀጣይ በእቅዱ ዘመን በልዩ ትኩረት መንቀሣቀስ ይገባል።

የመዛግብት ፍሰት እየጨመረ የሚሄድ ቢሆንም በክልልና በዞን ደረጃ የባለሙያው ቁጥር እና የስራውን ፍሰት ለማጣጣም አለመቻሉ እንዲሁም የዳይሬክቶሬቱ አደረጃጀት በሁሉም ዞኖች ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት የተደረገ ቢሆንም የተወሰኑ ዞኖች ከመደበኛው የወንጀል የስራሂደት ጋር ደርቦ መስራት ችግር እየፈጠረ ቢሆንም ይህን ችግር በመቋቋም የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ ጥረት መደረጉ በጥሩ ጐኑ ተይዞ ወደፊት ግን የሰው ሀይልም ይሁን የማቴሪያ ችግር በጊዜ ተግባራት ማሳካት ይጠይቃል፡፡

በቅድመ መከላከል ረገድ የተከናወነ ተግባርን የንቃተ ህግ የሚታዩ የወንጀል ጉዳዮችን መሰረት አድርጎ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመለየት ጥራት ያለውን ንቃተ ህግ እንዲሰጥ የተደረገ ቢሆንም በተሰተው ልክ ወንጀልን ከመከላከል አንፃር የመጣውን ውጤት በመለየት በቀጣይ ችግሩን መፍታት ይገባል፡፡ በሚዲያ ለንግድና ለሽማቹ ማህበረሰብ በሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ዙሪያ የሚያስከትሉትን የህግ ተጠያቂነት አውቆ እንዳይፈጸምና አጥዎችን እንዲታገላቸው የንቃተ ህግ በሚዲያ መስጠት የሚገባ ሲሆን በአማራ ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ፕሮግራሞች ተደራሽ ለመሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ በቢሮው የቴሌግራም እና የፌስቡክ ገጽ ዜናዎች እንዲሰሩ በማድረግ በክልል ደረጃ ጥሩ አፈጻጸም ቢኖርም በዞኖች ያልተፈጸመ በመሆኑ በድክመት የሚታይ ነው፡፡

## 2.3. የአበይት ተግባራት አፈጻጸም

በ2015 በጀት ዓመት ውስጥ በፍትህ ቢሮ በወንጀል ፍትህ አስተዳደር፣ በፍትሀብሔር ፍትህ አስተዳደር፣ በሕግ ምክር ማርቀቅና ማጠቃለል፣ በሰነዶችና ጠበቆች ምዝገባና ማረጋገጫ፣ በሰብዓዊ መብትና በሌሎች ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ለተቋሙ ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶች አበረታች ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

### 2.3.1. የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተግባራት አፈጻጸም

በ2015 በጀት ዓመት በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ረገድ የመጀመርያው ተግባር የሆነው የወንጀል ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በወንጀል መከላከል ረገድ የንቃተ-ህግ ትምህርት በመስጠት ወንጀልና የወንጀል ስጋቶችን በመቀነስ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት የመጠበቅ ስራ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ህብረተሰቡ የወንጀል አስከፊነትን አውቆ ለመከላከል የራሱን ድርሻ እንዲወጣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሲተገበር መቆየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ወንጀል ፈጻሚዎችን በህግ ፊት አቅርቦ ራሳቸውንና ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል ተመጣጣኝ ቅጣት

የማስቀጣት ስራ ሲከናወን በመቆየቱ ምክንያት የክልሉ ሕብረተሰብ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ሊኖረው የሚገባውን አመኔታ በየጊዜው እንዲጨምር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት አቃቤ ህግ የወንጀል መዛግብትን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር ያለውን የማጥራት ምጣኔ አፈፃፀም ስንመለከት በበጀት ዓመቱ የማጥራት ምጣኔ 100% ለመፈጸም ታቅዶ 98.05% መፈፀም ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ አፋጣኝ ውሳኔ አለመስጠቱ፤ የመዛግብት መብዛትና የዐቃቤያነ ህግ ቁጥር ማነስ ሊቀረፍ የሚገባው ችግር ነው፡፡

የእጅ ከፍንጅ ወንጀለኞችን በተፋጠነ ፍርድ አሰጣጥ ስርዓት መሰረት (RTD) ወዲያውኑ አቅርቦ ፍርድ እንዲያገኙ በተፋጠነ ፍርድ አሰጣጥ ስርዓት መሰረት ውሳኔ ሲሰጥባቸው ቆይቷል፡፡

የተፋጠነ ክስና ፍርድ አሰጣጥ በሁሉም አካባቢ ወጥነት የጎደለው ሲሆን የዚህም ምክንያት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ በተወሰኑ ዳኞች፣አቃቤ ሕጐችና ፖሊሶች ለጉዳዩ ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ እንዲሁም በተፋጠነ የፍርድ ስነ-ስርዓት የሚታዩ ጉዳዮችን የሚመለከት ዝርዝር የህግ ማዕቀፍ አለመዘጋጀቱ ነው፡፡

አቃቤ ህግ የወንጀል መዛግብትን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት አንጻር ያለውን የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀም ስንመለከት በቀጥታ ክስ 95.2% ታቅዶ 91.81% መፈፀም ተችሏል፡፡ በዐቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር ጉዳዮች 86% ለማድረስ በዕቅድ ተይዞ 87.62% ተከናውኗል፡፡ በፍርደኛ ይግባኝ እና በፍርደኛ ሰበር አቤቱታ 87% ለመፈፀም ታቅዶ 86.76% መፈፀም ተችሏል፡፡ የማቋረጥ ምጣኔን 4% ለማድረስ ታቅዶ አፈፃፀሙም 11.35% ነው፡፡ ስለሆነም ተገቢውን ምስክርና ማስረጃ በወቅቱ በማቅረብ ውሳኔ ማሰጠት የሚጠይቅ ነው፡፡ የማስቀጣት ምጣኔ አፈፃፀሙ ጥሩ የሚባል ቢሆንም በዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር መድረስ ያልተቻለ በመሆኑ ለመፈፀም የሚያስችልና ተደራሽ የሆነ ዕቅድ በማዘጋጀት መስራት ይኖርበታል፡፡

ከታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ ያልተቻለው የተለያዩ ችግሮች በመኖራቸው መሆኑ ተስተውሏል፡፡ ዓቃቤ-ሕግ የወንጀል ሥነ-ስርዓት ህጉን መሰረት ያደረገና ጥራት ያላቸው ክሶች፣ መልሶችና ክርክሮችን ካለማድረግ አንጻር የሚታይ ሲሆን ከውጫዊ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ፖሊስ የሚያሰባስባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ምስክሮች በአካል ቀርበው በፍርድ ቤት ከሚሰጡት ቃል ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ መኖርና የሀሰተኛ ምስክርነት መበራከት፣ ፍርድ ቤቶች

ክርክሮችን በአግባቡ ያለማስኬድና ውሳኔዎችንና ትዕዛዛትን በአግባቡ ካለመስጠት ጋር የሚያያዙ ችግሮች በመኖራቸው በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት በቅንጅት መስራትን ይጠይቃል፡፡

የወንጀል አቤቱታን በተመለከተ ከቢሮ እስከ ንዑስ ወረዳ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤቶች ድረስ ባሉ አደረጃጀቶች ልዩ ልዩ አቤቱታዎች ከቀረበው ውስጥ 97.06 በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡ ዋስትናን በተመለከተ ከቀረበው 98.08% በመቶ መፈጸም ተችሏል፡፡

በወንጀል ተከሰው የሚቀጡ ግለሰቦች የተላለፈባቸው ቅጣት ለሌላው ማስጠንቀቂያ እንዲሆን አስተማሪ ውሳኔዎች የሚዲያ ሽፋን እንዲገኙ ማድረግ ይገባል፡፡ በመዝገብ ማጥራት ረገድ በአብዛኛው መዛግብት በተቀመጠላቸው የግዜ ወሰን ውስጥ ሳይዘገዩ የማጥራት ሁኔታ ጥሩ ቢሆንም ተሰርተው ማለቅ ከነበረባቸው ጊዜ በላይ በተጨማሪ ምርመራና በሌሎች ምክንያቶች መዘግየት እና በመመሪያው የሚመላለስ መዝገብ በሁሉም ዞን መኖሩ በድክመት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ሌላው በመዝገብ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ በሚያዙ የወንጀል ፍሬ በሆኑ ኤግዚቢቶች ላይ ውሳኔ ሳይሰጡ ማዘግየት አንዱ ችግር ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የወንጀል ፍሬ የሆነው ኤግዚቢት ተብሎ በክስ አለመጥቀስ ችግር ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ዓመት ችግሮቹን እንዳይከሰቱ አጥብቆ መስራት ይጠይቃል፡፡ ክስ በመስርተንበትና በምንከራከርባቸው ጉዳዩች የውጤታማነት መጠናችን ስናይ በአመቱ እናሳካዋለን ብለን ካስቀመጥነው ጥሩ አፈጻጸም ላይ ያለ ቢሆንም በዚህም በርካታ ከህገ ወጦች የተያዘ ንብረትና ቅጣት ማስገባታችን የሂደቱን ጥሩ አፈጻጸም የሚያሳይ ቢሆንም በአንጻሩ ክስ ጥራት እና በሌሎች ምክንያቶች በዞን ደረጃ ነጻ የሚወጡ ተከሳሾች በመኖሩ ችግሮች የሚስተዋልባቸው አካባቢዎችን ለይቶ መፍታት ይጠይቃል፡፡

በምስክር ወይም በተከሳሽ አለመቅረብ ምክንያት የሚዘጋ መዛግብት በበጀት አመቱ ለመቀነስ እቅድ ቢያዝም የተቋረጡ መዛግብት አሉ፡፡ ይህም አፈጻጸም ደግሞ ብዙም ከፍተኛ ባይባልም እንኳን የተዘጉ መዛግብቶች ተከሳሾች በተከሰሱበት ወንጀል ሳይጠየቁ የተዘጉ በመሆኑ እነዚህን መዛግብት ለማንቀሳቀስ ጥረት ማድረግ ይጠይቃል፡፡

በክልል ደረጃ በፍትህ አካሉ ያለውን የክህሎት ክፍተት በመሙላት ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎም ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል በክልሉ ለሚገኙ መርማሪ ፖሊሶች፤ በኢኮኖሚ ወንጀል የስራ ክፍል ለተደራጁ ዐ/ህጎች፤ ለዳኞች እና ለንግድ ባለሙያወች ስልጠና በመስጠት ስራዎችን ለማሳለጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ የአጋር አካላትን መድረክ በመፍጠር አጋር አካላትን በመለየት ስራዎችን ለመገምገም እና ግንኙነት ስርዓት በመዘርጋት አጋር አካላት ለምንሰራው ስራ አጋዥ ሆነው

እንዲቆሙ ለማስቻል በክልል እና በተወሰኑ ዞኖች የተደረገ ጥረት ቢኖርም በአብዛኛው ዞኖች የሚፈለገውን ያክል ርቀት ለመሄድ አልተቻለም፡፡

ወንጀልን ለመቀነስ ይቻል ዘንድ በ2015 በጀት ዓመት 5,339,608 በክልሉ ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች የንቃተ ህግ ትምህርት ለመስጠት የታቀደ ሲሆን የፍትህ ሥርዓቱን በማጎልበት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ይቻል ዘንድ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግና በሂደቱም ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ህብረተሰቡ ህገ-መንግስታዊ መብትና ግዴታዉን በመገንዘብ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና ለህግ የበላይነት መጎልበት ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫዎት ለማድረግ የሚያስችል ትምህርት መስጠት ተገቢ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በበጀት ዓመቱ 12 ወራት ለወንድ 1,477,601 ለሴት 1,251,897 በድምሩ 2,729,499 ግንዛቤ ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ከ12 ወሩ ዕቅድ ያለው አፈፃፀም 51.0 በመቶ ነው፡፡

ስልጠናው የተሰጠባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ያለእድሜ ጋብቻ፤ አስገድዶ መድፈር፤ የሴቶች የህጻናትና ወጣቶች መብት፤ ስለ ሰብአዊ መብት፤ ስለ ቤተሰብ ህግ፤ ስለ ህግ የበላይነትና በወንጀል መከላከል ረገድ የህብረተረሰቡ ሚና በሚሉት ርዕሶች ላይ የንቃተ ህግ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ የንቃተ ህግ ትምህርት ከመስጠት ባሻገር ያመጣውን ውጤት መለካት ጊዜ የሚጠይቅ ቢሆንም ያመጣውን ውጤት መፈተሽ ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

በዞን እና የወረዳ ፍትህ መምሪያና ጽ/ቤቶች በአግባቡ እየተዘጋጁ የንቃተ ህግ ትምህርት ይሠጡ ዘንድ የንቃተ ህግ ትምህርት ማስተማሪያ ማንዋል ወጥ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቶ በመላኩ ትምህርቱ እየተሰጠ ሲሆን በየበጀት ዓመቱ ለህብረተሰቡ በተለያዩ ጉዳዮችና የንቃተ ሕግ ትምሕርት ለመስጠት እቅድ እየተያዘ በታቀደው መሰረት ሲተገበር ቆይቷል፡፡

በዚህም ግብዓት ህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤ ኖሮት ወንጀለኛን በመጠቆም፣ ማስረጃ ሆኖ በመቅረብ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ሕብረተሰቡ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ፣ እንዲሁም ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንደሚቀንሱ፡ ማሕብረሰቡም መብቱን የመጠቀምና ግዴታውን የመወጣት ልምዱን እያዳበረ እንዲመጣ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

የንቃተ ህግ ሰነድ ዝግጅት እና የትምህርት አሰጣጥ ጥራትን ለማጠናከር የሚያስችሉ አሰራሮች እና ዘዴዎች እየተመቻቹ ቢሆንም ውጤቱ ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሰ በመሆኑ ተጨማሪ ስራዎችን የሚጠይቅ ነው፡፡ የሚሰጠው የንቃተ ህግ ትምህርት የየአካባቢውን የወንጀል ባህሪ በማጥናት አካባቢ ተኮር የንቃተ ህግ ትምህርቶች የሚሰጡበትን ሁኔታ በቀጣይ ማመቻቸት ይገባል፡፡

### 2.3.2. በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ

ቢሮው በበጀት ዓመቱ አዲስ አደረጃጀት ተግባራዊ ከማድረጉ ጋር ተያይዞ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት በአዲስ መልኩ በማደራጀት ስራ መጀመር የተቻለ ሲሆን በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ በሙስና ወንጀል ተከሰው ከተፈረደባቸው ግለሰቦች ተጨማሪ ምርመራና ማጣራት በማካሄድ ሀብታቸውን የማሳገድና የመከራከር ተግባራት እየተከናወነ ሲሆን ዳይሬክቶሬቱን በአዲስ ማደራጀት የተቻለ ቢሆንም የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ እንዲያከናውን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ከፖሊስ ተቋማት ጋር የጋራ የምርመራ ስራ በመስራት ቀደም ሲል በኮሚሽኑ ሲሰሩ የቆዩ ተግባራትን በመረከብ የፍ/ቤት ክርክር በማድረግ ተገቢውን ሀበት ለማሰባሰብ ጥረት እየተደረገ በመሆኑ ተግባሩን አጠናክረን መስራት ይጠበቅብናል፡፡

### 2.3.3. የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ጉዳዮች አፈጻጸም

በ2015 በጀት ዓመት በፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ጉዳዮች የመንግስት እና የሕዝብ ጥቅም ለማስከበር በታቀደው መሰረት ተከታታይ የህግ ድጋፍና ምክር በመስጠት፤ የውል ረቂቅ በመመርመርና በማዘጋጀት፣ ድርድር፣ ክርክር፣ የንብረት ማሳገድ እና ውሳኔ ማስፈጸም ተግባራት ትኩረት ተሰጧቸው ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

በፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደሩ ረገድ የመጀመርያው ተግባር የሆነው የመንግስት፤ የህዝብ እና ነፃ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅም እንዲከበር ሰፊ የቅድመ መከላከል ስራ መስራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚከናወኑ ተግባራት የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ የተጠናከረ የህግ ምክርና ድጋፍ በመስጠት፤ የመንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ስልቶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በመስራት ተቋማቱ ተግባራቸው በህግ አግባብ ለመፈጸም እንዲችሉ ድጋፍ እገዛ ተደረጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውል ከመግባታቸው በፊት መርምረን አስተያየት እንድንሰጥባቸው ከቀረቡት ውስጥ 100% በሚሆኑት ላይ የውል ረቂቅ ምርመራና ዝግጅት ድጋፍ በመስጠት ከውሉ የሚጠበቀውን መብትና ጥቅም እንዲያገኙና የሚጠበቅባቸውን አንጻራዊ ግዴታ ለይተው እንዲያውቁ በማድረግ ከፍተኛ ግምት ያለው የመንግስትን ሀብትና ንብረት ከብክነት በማዳን የሕዝብና የመንግስትን ጥቅም ማስጠበቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ ይህ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰጠው ድጋፍ ተከታታይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ የሚሰጠው ድጋፍ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ብክነት

እና ምዝበራ የሚፈፀምባቸው ተቋማት ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ በቀጣዩ የእቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቶት ሊከናወን ይገባል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የመንግስት መ/ቤቶች የውል ግዴታ ከገቡ በኋላ ግዴታቸውን አለመፈፀም ከውሉ የሚጠበቀውን መብትና ጥቅም አለማስፈፀም፤ ውሉን በዘፈቀደ ማቋረጥና ለውል መፍረስ ምክንያት በመሆን መ/ቤቱን ለከፍተኛ ወጭ መዳረግ፤የመስሪያ ቤቱን ጥቅም ለተዋዋይ ወገኖች አሳልፎ መስጠት፤ህገወጥ ተግባር ከፈፀሙ በኋላ ዐቃቤ ህግ በመንግስት ስም ሽፋን እንዲሰጣቸው የመፈለግ ዝንባሌ ስላለ ወደፊት በየተቋሙ ባለሙያዎችን በመመደብ ቁጥጥር፤ የክትትልና ድጋፍ ማጠናከር ይጠይቃል፡፡

የውል ረቂቅ ምርመራና ዝግጅት አገልግሎት አሰጣጣችንም ቢሆን ወጥነት የጎደለውና አልፎ አልፎ በውሉ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ውዝግቦችን መፍታት የማያስችል ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ ወደፊት ጥራትና ቅልጥፍናውን ማሻሻል ይጠይቃል፡፡

**ጉዳዮችን በድርድር መፍታትን በተመለከተ፡-**

የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ከሌሎች አካላት ጋር ባደረጉት ግንኙነት አለመግባባት ሲፈጠር ከፍርድ ቤት ውጭ ጉዳያቸው በድርድር እንዲፈታ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በድርድር እልባት እንዲያገኙ ከተደረጉት ጉዳዮች ገቢ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን ከፍ ለማድረግ እና በክርክር የሚወጣውን ጊዜና ወጭ በመቀነስ ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ ለመጨረስ የሚያስችል አማራጭሆኖ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በዚህ አግባብ በድርድር እልባት ያገኙ ጉዳዮች ከታቀደው 28% ግብ አኳያ በንፅፅር ሲታይ በመዝገብ 18.84% መፈፀም ተችሏል፡፡

ድርድርን አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ አድርጎ በመጠቀም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮች፡- የመንግስት መስሪያ ቤት ተወካዩች ለድርድር ሲጠሩ ፈቃደኛ ያለመሆን፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመንግስትን ጥቅም ለተደራዳሪዎች አሳልፎ ለመስጠት የመፈለግ፤ድርድሩን የሚመሩ ዓቃቤ ህጎች ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠትና በቂ ዝግጅት አለማድረግ፤ድርድሩ የሚመራበት የአሰራር ስርአት የሚወስን መመሪያ ባለመኖሩ ሀላፊነት ወስዶ ለመደራደር አለመቻል ዋና ዋና ችግሮች በመሆናቸው በቀጣይ በትኩረት ሊሰራበት የሚገባው ነው፡፡

**የመዛግብት ማጥራትን በተመለከተ፡-**

የምንወክላቸው አካላት የሚገጥማቸውን የመብት ጥሰትና ጥቅም ግጭት በድርድርና በመግባባት ካልተፈታ ጉዳዩን ተቀብሎ በተገቢው ጊዜ መርምሮ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶችህብረት ስራ ማህበራት እና ነጻ ድጋፍ ለሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ያቀረቡዋቸውን ጉዳዮች ዐቃቤ ህግ በመቀበል የተለያየ ውሳኔ የተሰጠባቸው ሲሆን በ2015 በጀት ዓመት 12 ወራት መዝገብ የማጥራት አቅም ከተያዘው 100% እቅድ አንፃር 99.19% መፈፀም ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ አፋጣኝ ውሳኔ አለመስጠቱ፤ የመዛግብት ፍሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመርና የዐቃቤያነ ህግ ቁጥር ማነስ፤ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃወች በቀላሉ የማይገኙ በመሆኑ በቀጣይነት ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባው ነው፡፡

## የክርክር ውጤታማነትን በሚመለከት፡-

በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሚቀርቡ ጉዳዮች በየደረጃው ባሉ የፍርድ ቤት እርከኖች ተከራክሮ አሸናፊ መሆን የሚጠይቅ ሲሆን በአጠቃላይ በመንግስት እና ነፃ የህግ ድጋፍ ለሚሹ አካላት በፍርድ ቤት ስንከራከርባቸው ከነበሩ መዛግብት ውስጥ የማሸነፍ አቅም አፈፃፀም በጥቅል ስንመለከት በ2015 በጀት ዓመት 12 ወራት 92% ለማድረስ ታቅዶ በመዝገብ 91% ተከናውኗል፡፡ የተቀመጠውን ዕቅድ መፈፀም ባይቻልም የተሻለ አፈፃፀም በመኖሩ በቀጣዩ የእቅድ ዘመንም ከዚህ የተሻለ ለመፈፀም የሚያስችልና ተደራሽ የሆነ ዕቅድ በማዘጋጀት መስራት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ጉዳዮች ዓቃቤ-ሕግ ጥራት ያላቸው ክሶችንና መልሶችን ከማቅረብ ክርክሮችን በአግባቡ ካለመምራት፣ የችሎት ዝግጅት ካለማድረግ እና ጉዳዮችን በጥልቀት ከህግና ከማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ በውል ካለመለየት ጋር የተያያዘ ሲሆን በተለይ በነፃ ህግ ድጋፍ ጠያቂዎች እና በመንግስት መ/ቤቶች ተገፋፍቶ ጉዳዩ እንደማያዋጣው እየታወቀ ፍ/ቤት ይወስነው በሚል ክስና መልሶችን የማቅረብ አሰራር ወደፊት ታርሞ ዓቃብያነ ሕግ ሙያዊ ነፃነታቸውን ጠብቀው ጥራት ያላቸውን ጉዳዮች ብቻ በማቅረብ ያላቸውን ተቀባይነት ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከውጫዊ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚላኩ የሰውና የሰነድ ማስረጃና ምስክሮች በቂ አለመሆን፤ማስረጃዎችን አለመስጠት፣ውሉን ያለበቂ ምክንያት ማቋረጥ በተጋነነ ዋጋ ውል መስጠት፤ የግንባታ አማካሪ ድርጅቶች የሚሰጡትን ውሳኔ አለመቀበል፤ የመንግስት መ/ቤቶች በሚከሰሱበት ጊዜ በፍ/ቤት የተያዘው ቀጠሮእስኪደርስ መጥሪያውን በእጃቸው

አቆይተው በቀጠሮው ቀን ለዐ/ህግ ማቅረብ አልፎ አልፎ በራሳቸው መልስ ከሰጡ በኋላ ድጋፍ መጠየቅ፣ ፍርድ ቤቶች ክርክሮችን በአግባቡ ያለማስኬድና አንዳንድ ውሳኔዎችና ትዕዛዞች የህግ መሰረትና ተገማችነት የሌላቸው ስላሉ በቀጣይ ማስተካከል ይጠበቃል፡፡

ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በሚመለከት የተሠጠው አገልግሎት ሽፋን አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃወች የት፤እንዴት ለማን፤መቸ፤ ማቅረብ እንዳለባቸው ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ እጥረት ያለባቸው፤በራሳቸው ፍርድ ቤት ካቀረቡ በኋላ ሲሸነፉ ድጋፍ የሚጠይቁ በመሆኑ ጉዳያቸውን ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ጠበቆችን እና ነጻ ድጋፍ የመስጠት ፈቃድ ያላቸውን በህግ ትምህርት ቤቶች አካቶ ተከታታይ ስራዎች መስራት ይጠይቃል፡፡

## ንብረት ፈልጎ ማሳገድን በሚመለከት፡-

በከሳሽነት የሚቀርቡ ጉዳዮች በየደረጃው ባሉ የፍርድ ቤት እርከኖች ተከራክሮ አሸናፊነት ከተረጋገጠ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው ተግባር በፍርድ የተረጋገጠውን መብት እንዲፈፀም ማድረግ ነው፡፡ ፍርድን በአስተማማኝ ለማስፈፀም ደግሞ አስቀድሞ ወይም በአፈፃፀም ሒደት ንብረት ፈልጎ ማስከበርና የማሳገድ ያስፈልጋል፡፡ የፍርድ ማስፈፀሚያ ዋስትና የሚሆኑ ንብረቶችን ማሳገድና ፍርድን ማስፈፀም ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ሲሆን 50.0% ዕቅድ ተይዞ አፈጻጸሙ በመዛግብት **63.0%** ላይ ይገኛል፡፡

ክስ ከቀረበበት መዛግብት ውስጥ መታገድ የነበረበት ንብረት ሙሉ በሙሉ ያልታገደበት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው ለጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ በወቅቱ ንብረት አለመፈለግና እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መ/ቤቶች የትብብር ማነስ፤ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ተቋማት ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተፈጠረ በኋላ ለብዙ አመት አቆይተው የሚልኩት በመሆኑ ተከሳሾች ንብረታቸውን ለማሸሸና ወደ 3ኛ ወገን ለማዞር ምቹ ሁኔታን የፈጠረላቸው በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባዋል፡፡

## በድርድርና በፍ/ቤት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን ማስፈፀምን በተመለከተ፡-

ውሳኔ በማስፈጸም ረገድ በመንግስትና በነጻ የሕግ ድጋፍ ውሳኔ ካገኘውና በድርድር ከተቋጩ ጉዳዮች በ2015 9 ወራት 188 ሚሊየን ብር ለመንግስት ገቢ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በእቅድ ዘመኑ ማብቂያ ከተያዘው 70.0% እቅድ አንጻር አፈጻጸሙ ወይም ገቢ የሆነው መጠን 91.64%ነው፡፡

ከስር ዐቃቤ ህግ ለሚቀርቡ የመሪ ትእዛዝ ጥያቀወችና የክስ ወይም የይግባኝ አይቀርብም ውሳኔወች በበላይ ዐቃቤ ህግ ተመርምረው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ቢሆንም በታችኛው እርከን ላይ ለሚገኙ ዐቃብያነ ህግ ያለውን የክህሎት ክፍተት የሚሞሉ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡

አቤቱታን በተመለከተ በ2015 በጀት ዓመት ብዛት ያላቸውን አቤቱታወች የቀረቡ ሲሆን 98% ለማከናዎን ታቅዶ 99.16 በመቶ ለሚሆኑት ምላሽ ተስጥቷል፡፡ ሆኖም ዐቃቤያነ ህግ ትዕዛዝ በሰጡባቸው አቤቱታዎች እስከ መጨረሻው አፈጻጸማቸውን በመከታተል ረገድ ውስንነቶች ስለሚታዩ ወደፊት በትኩረት ሊሰራ ይገባዋል፡፡

### 2.3.4. የሰነዶች ማረጋገጥ እና የጠበቆች ጉዳይ ተግባራት አፈጻጸም

ቢሮው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ የሰነዶች፣ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የጠበቆች ክትትል እና ምዝገባ ስራ ነው፡፡ ለህብረተሰቡ ተደራሽ የሆነ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ስርዓት በመዘርጋት ዜጐች በቅርብርቀትና በአነስተኛ ወጪ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ለመፍጠር በየደረጃው የተለያዩ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡
በዚህም አገልግሎት ለመንግስት ብር 1,134,343,201.23 ብር ገቢ ተደርጓል፡፡ ክንውኑም ከተደራሽ ግቡ ጋር ሲነጻጸር በመጠን የቀረበው ጉዳይ ተፈጻሚ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጅ ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር አልፎ አልፎ በጥራትና ከማስተገናገድ አኳይ ችግሮች ተስተውሏል፡፡ በተለይም ከላይ የተጠቀሰው ከፍተኛ ገንዘብ በገቢነት እየተሰበሰበ ያለ ቢሆንም ይህንን ገንዘብ በሃላፊነት ሰብስቦ ገቢ ሊያደርግ የሚችል የገንዘብ ሰብሳቢ ሰራተኛ በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች በቋሚነት ባለመመደቡ ለስራው እንቅፋት ስለሆነ ሊስተካከል ይገባል፡፡

በክልላችን ውስጥያለውን የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥና አሰራር ትግበራ አፈጻጸምሁኔታን በተመለከተ መስሪያ ቤቱ ጉዳዩን የሚከታተል ዲሲፕሊን ጉባኤ እና የፈቃድ አሰጣጥ ቦርድ አቋቁሞ ልዩ ልዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡  በመሆኑም ለ848 ጠበቆች የፈቃድ እድሳት የተደረገ ሲሆን 143 ለሚሆኑ አዲስ የጥብቅና ፈቃድ ጠያቂዎች ያቀረቡትን ሠነድ በመመርመር ህጋዊ መስፈርቱን ያሟሉትን 2ኛ ደረጃዎችን በፈተና 1ኛ ደረጃዎችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

የጠበቆችን 50 ሰዓት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፈቃድ ወስደው በማገልገል ላይ የሚገኙ ጠበቆችን የመክፈል አቅም የሌላቸው ዜጐች ነፃ የህግ አገልግሎት ተሰጧል፡፡ በዚህም ወንድ-290 ሴ-430 ድ-720 የህብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የ50 ሰዓት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ በ351 መዝገቦች አሸናፊ በ71 መዝገቦች ተሸናፊ ሆነዋል፡፡ 274 መዝገብ የዞረ ነው፡፡

የማሸነፍ ምጣኔአቸው 83.1 በመቶ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጠበቆቹ በያዙት ነጻ አገልግሎት መዝገብ ላይ ያስመዘገቡት ውጤትና የተገልጋዩን እርካታ በተመለከተ ክትትል በማድረግ ረገድ ውስንነት የታየበትና ጠበቆች ጥሩ ስነ-ምግባር በመያዝ የፍትሕ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆኑ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት ውስንነት የታየበት ነው፡፡

ጠበቆች በተሰጣቸው ፈቃድ ህግን መሰረት አድርጎ ከመስራት ይልቅ ሀሰተኛ ሰነድ ከማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እና ከአንዳንድ መንግሥታዊ ተቋማት ሰነድ አሠርቶ ለፍርድ ቤት ማቅረብ፣ የዓቃቤ ህግ ምስክሮችን እንዳይመሰክሩ ማባበልና መደለል፣ የደንበኞቻቸውን ሚስጢር ለተቃራኒ ደንበኛ መግለጽ፣ በነጻ አገልግሎት ላይ ክፍያ መጠየቅ፣ ከፍትህ አካላት ጋር አላስፈላጊ ግንኙነት መፍጠር፣ ከደንበኞቻቸው ጋር ውል አለመያዝ፣ የሚያዋጣና የማያዋጣውን ጉዳይ ሳይለዩ ክፍያ ለማግኘት ብቻ አዋጭ ያልሆኑጉዳዩችንምጭምርመያዝ የመሳሰሉት የስነ-ምግባር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

ከላይ የተገለጹትን የሥነ-ምግባር ችግሮች በሚፈጥሩ ጠበቆች ላይ የሚቀርቡ ክሶችና አቤቱታዎችን በማጣራት እና ለጠበቆች የዲስፒሊን ጉባዔ በማቅረብ ውሣኔ ማሰጠት እና ጠበቆች ጉዳዩን ወደፍ/ቤት በይግባኝ ሲያቀርቡት ተገቢውን ክርክር በማድረግ የማስወሰን ጉዳይ የተጀመሩ ጅምሮች አበረታች ቢሆኑም የተሰራው ስራ በህብረተሰቡ ከሚነሱት ችግሮች አንጻር አፈጻጸሙ በቂ አይደለም፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በተመለከተ በየደረጃው ባሉ የቢሮው አደረጃጀቶች እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን አዲስ የተመዘገቡ በጎ አድራጎት ድርጅቶች /ማህበራት/ ብዛት 1፣ ነባር ተመዝግበው የሚገኙ በጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት ብዛት 206፣ አጠቃላይ አዲስ እና ነባር ተመዝግበው የሚገኙበጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት ብዛት 210፣ አጠቃላይ በአስራ አንድ ወሩያሳደሱ በጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት ብዛት 15፣ በሩብ አመቱ አመታዊ ሪፖርት ያደረጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች/ማህበራት ብዛት 2፣ አጠቃላይ በዓመቱ አመታዊ ሪፖርት ያደረጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች/ ማህበራት ብዛት 26 ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባና ክትትልን በተመለከተ ከክልል እስከ ወረዳ ስራው በተሟላ የሠው ሃይል አደረጃጀት ያልተጀመረ በመሆኑ የምዝገባ፤ የፈቃድ እድሳቱ እና የቁጥጥር ሰራው ውስንነት ያለበት እና ወደፊት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

### 2.3.5. የህግ ምክር፣ ማርቀቅ እና ማጠቃለል ተግባራት አፈጻጸም

ቢሮው በክልሉ የሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች በማርቀቅና አስተያየት ሲጠየቅም ተገቢውን የህግ ቅርፅ እንዲይዙ በማድረግ በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን የህግ ጉዳዮችን የማማከር ስራም ያከናውናል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት ልዩ ልዩ አዋጅ፣ ደንቦችና

መመሪያዎችን በማዘጋጀትና ህግ ምክር አገልግሎት በመስጠት የተጣለበትን ተግባር በብቃት ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት 12 ወራት በበጀት ዓመቱ 12 ወራት 4 አዋጅ፣ 24 ደንቦች፣ 36 መመሪያዎች 2 ማንዋል ተሰርተው ተልከዋል፡፡ ለ6 ጉዳዮች የህግ ምክር ተሰጥቷል፡፡ የሕግ ማጠቃለልን በሚመለከት በክልሉ የወጡና በፌዴራል ደረጃ ወጥተዉ በክልሉ ተፈፃሚ የሆኑ ሕግጋትን በማሰባሰብ ለአንባቢያን ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በ12 ወሩ 3 ቅጾች ታትመው በመሰራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀሪው 4ኛ ቅፅ በቀጣይ የሚታተም ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራው በበቂ ስልጠና ላይ ያልተደገፈ እና የባለሙያ እጥረት በመኖሩ የጥራት ጉድለት የሚታይ መሆኑ፣ የባለሙያ እጥረት፣ የተቋማት ሃላፊዎች ባለባቸው የግንዛቤ እጥረትና በየጊዜው የሚለዋወጡ በመሆናቸው ምክንያት የሚያመነጯቸውን ረቂቅ ህጎች ወደ መ/ቤቱ ሳይልኩ ማጸደቅ ወይንም በራሳቸው ማጽደቅ፣ በመ/ቤቱ ያልታዩ ረቂቅ ህግጋት እንዳይጸድቁ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ያለመኖር፣ የህግ አጽዳቂ አካላት የጸደቁ ህግጋትን ለማጠቃለል ለመስሪያ ቤቱ የማይልኩ መሆኑ፣ ስልጠናዎችን ለመስጠት እያጋጠመ ያለ የበጀት እጥረት፣ በመሥሪያ ቤቱ ወጪ በመማር ላይ ካሉ ባለሙያዎች መካከል ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑት የትምህርት እድል ያገኙ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን አለማጠናቀቃቸው፣ የሕግ ማጠቃለል ሥራው በበጀት እጥረትና ሕግጋት ከተሰባሰቡ በኋላ ለህትመት ዝግጁ ለማድረግ የሙያ ክህሎት ችግር የሚያጋጥም በመሆኑ በተገቢው ጊዜ ማሳተም አለመቻል እና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ለማጠናቀቅ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊታረሙ ይገባል፡፡

### 2.3.6. የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን በተመለከተ

የሰብዓዊ መብት ጥሰት አጋጥሞናል በሚል በቀረቡ 3 አቤቱታዎች ላይ ማጣራት በማድረግ ምርመራ እንዲደረግ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፤ ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በ3 ማረሚያ ቤቶችና 2 ፖሊስ ጣቢያዎች ጉብኝት በማድረግ የታራሚዎችና የተጠርጣሪዎችን መብት ለማስጠበቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ክልላዊ የማረሚያ ቤቶችና የፖሊስ ጣቢያዎች ጉብኝት ማንዋልን በማዘጋጀት ከሚመለከታቸው አካል ጋር የመወያየት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር በመተባበር የሰብዓዊ መብት ጥሰት ደረሰብን በሚል አቤቱታ ያቀረቡ ዜጎችን ምስክርነት የመስማትና የዜጎችን ሰብዓዊ መብት በማስከበር የተሰሩ ስራዎችን የማስረዳትና በቀጣይ ሊደረጉ በሚገባቸው ተግባራት ላይ ውይይት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በሴቶች እና ህፃናት ላይ በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያት እየደረሰ ባለው ጉዳትና በባለድርሻ አካላት ግዴታ ዙሪያ ባደረገው ጥናት ላይ ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ባህርዳር ቅርንጫፍ በ24 ማረሚያ ቤት ባደረገው ክትትል የጊዜ ቀጠሮ አልፎባቸው ማ/ቤት የሚገኙ 303 ታራሚዎችን በተመለከተ ችግሩ እንዲፈታ ለየመምሪያዎቹ የተገለጸላቸው ሲሆን በዚህ መሰረትምስራቅ ጎጃም (ቢቸና=62፤ ደ/ማርቆስ=34፤ ድምር=100)፣ ደቡብ ጎንደር አዲስ ዘመን=51፣ ደ/ታቦር=12፣ ጋይንት=10 ድምር=73)፣ ምዕራብ ጎጃም (ባህርዳር=60)፤ ደቡብ ወሎ (ወረኢሉ=7፣ ሃይቅ=5፣ ድምር=12)፣ ዋግሕምራ (ሰቆጣ=30)፣ ማዕከላዊ ጎንደር (ጎንደር ከተማ=14)፣ ሰሜን ጎንደር (ዳባት=3)፣ ሰሜን ሸዋ (አጣዬ=11)

የክልሉን የፍልሰት ማስተባበሪያ ምክር ቤት ረቂቅ ደንብ አስመልክቶ በአመራር ደረጃ ምክክር መድረክ የማካሄድና አቅጣጫ የማስቀመጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በምክክር መድረክ የተሰጡ አስተያየቶች መሰረት በማድረግ ረቂቅ ደንቡን በማዘጋጀት ለመስተዳድር ም/ቤት እንዲላክ ለቢሮው የማቅረብ ስራ ተሰርቷል፡፡

የህፃናት ጋብቻና በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚደርሰውን የኃይል ጥቃት በመከላከልና ምላሽ በመስጠት ዙሪያ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ወይም ምላሾችን በተመለከተ ከሴቶችና ህፃናት ቢሮ እና ከጠቅላይ ፍ/ቤት ጋር በመተባበር የዳሰሳ ጥናት የማድረግና ውጤቱን ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፤ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ በፍትህ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎች አስመልክቶ በተደረገው ጥናት ላይ ከህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት የቀጣይ አቅጣጫዎችን የማስቀመጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዩኤንዲፒ የበጀት ድጋፍ እንዲሁም ከሴቶች እናህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር ለሴት ዐቃብያነ ህግ የአቅም ግንባታ ስልጠና የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2014 ዓ.ም፣ በ2015 ዓ.ም 6 ወራት ECM&VAC የተከናወኑ ተግባራትን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የክልል፣ የዞንና ፕሮግራም ወረዳ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን የመገምገም ስራ ተሰርቷል፤

በዩኒሴፍ የሚለቀቁ በጀቶችን የመደልደል ፣የመጠቀምና አፈጻጸሙን የመከታተል እና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የመላክ ስራ ተሰርቷል፤

በዩኤንዲፒና በዩኒሴፍ የበጀትና የቴክኒክ ድጋፍ ለወረዳዎች፣ ለዞን፣ ለቋሚ ምድብና ለቢሮ በተለይ በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች 43 ኮምፒውተሮች፣ 42 ፕሪንተሮች፣ 15 ላፕቶፕ፣ 3 ፎቶኮፒ፣ 1 ከለርፕሪንተርና 1 ስካነር ግዢ ተፈጽሞ የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል፡፡

በ5 ፍትህ ጽ/ቤቶች እንዲሁም በዩኒሴፍ ባልታቀፈ 1 ፍትህ ጽ/ቤት እና 2 ዞን ፍትህ መምሪያ ላይ በመገኘት ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከሴቶችና ህጻናት ቢሮና ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር ሴቶችን እና ህፃናትን በሚመለከት በሃገራችን የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች ከዓለምአቀፋዊና አህጉራዊ ስምምነቶች ጋር ተጣጥመው መውጣቸውንና አፈፃፀማቸውን በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ተደርጓል፡፡

የአንድ ማዕከላትን ለማጠናከር የሚረዳ በአመራር ደረጃ ምክክር መድረክ የማካሄድ ተሰርቷል፡፡ በውይይቱ መሰረት በተቋማት መካከል የመግባቢያ ስምምነት የመፈራረም ስራ ተሰርቷል፡፡ የአንድ ማዕከል ፕሮቶኮል ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ በዩኒሴፍ የበጀትና የቴክኒክ የህፃናት ጋብቻ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የሚያግዝ 64 ቀናት በአየር ላይ የሚተላለፍ የንቃተ ህግ ትምህርት መርሃ ግብር በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የራዲዮና የኤ ኤም ስርጭት ጣቢያዎች እየተላለፈ ይገኛል፡፡

የባህር ዳር ሪፈራል ሆስፒታል የአንድ ማዕከል የ9 ወር ሪፖርት በተገለጹ ችግሮች ዙሪያ ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ተወካይ ኃላፊ እና ፎካል ፐርሰኖች ጋር ውይይት እና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

በዩኒሴፍ የበጀትና የቴክኒክ ድጋፍ በ2016 እና በ2017 በጀት ዓመት የሚከናወኑ ተግባራት የሁለተኛው ረቂቅ እቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የመላክ ስራ ተሰርቷል፡፡

በሰው የመነገድና  በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተከናወኑ ተግባራት የክልሉን የትብብር ጥምረት የ2014 ዓ/ም አፈጻጸም ሪፖርት፣ የትብብር ጥምረት የ2015 ዓ/ም እቅድ ዙሪያ፣ የትብብር ጥምረት የ2015 የ6 ወራት አፈፃፀምን የመገምገም ስራ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በደብረ ታቦር ከተማ የመገምገም ስራ ተካሂዷል፤

ከአለም አቀፍ የህፃና ትድርጅት /Save The Children/ ጋር በትብብር ጥምረት ማጠናከርና ወንጀል በመከላከል ዙሪያ ውይይት ጎንደር ከተማ ላይ ተደርጓል፤ በመድረኩ ላይ 150 ሰዎች ተሳታፊ ሆነዋል፤

ከኢሰማኮ ጋር በመተባበር ወንጀሎችን ለመከላከልና የትብብር ጥምረት ለማጠናከር የሚረዳ ስልጠና በባህርዳር ከተማ ለፖሊስ፣ ለትብብር ጥምረት አባል ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ ትበብር ጥምረት እንቅስቃሴን በተመለከተ ከፌደራል ጥምረት ከሚመጡ ባለሞያዎች ጋር በመሆን በክልልና በዞን የክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተከናዉኗል፡፡ የተደረገውድጋፍናክትትልሪፖርትግብረ-መልስለሚመለከተውአካልተልኳል፡፡

IOM ድጋፍ ለትብብር ጥምረት ማጠናከሪያ የመጡ የተለያዩ የስራ እና የቢሮ ቁሳቁሶችን በመረከብ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፤

ከCIVPOL Ethiopia ጋር በመተባበር ወንጀሎች ለመመርመር ናለማስቀጣት በተዘጋጀ የአሠራር ማንዋል ላይ ከየካቲት 3-4/2015 ባህርዳር ከተማ ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በመድረኩ ፖሊሶች፣ ዐ/ሕግና ዳኞች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከወንጀልና ፍታብሔር ባለሙያዎች ጋር በመሆኑን ቢሾፍቱ ከተማ ላይ IOM ባዘጋጀው መድረክ በመገኘት በፍልሰት ተጐጂዎች የነፃ የሕግድጋፍ ማንዋል ላይ ግብዓት የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡ Freedom fund ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር በሰው የመነገድና ሰውን በህገ-ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀሎችን በመከላከልና ምላሽ በመስጠት በኩል

በትብብር ጥምረቱ የተከናወኑና በምስራቅ አማራ በኩል ባሉ ችግሮች ዙሪያ ከክልል፣ ዞንና የወረዳ አመራሮች ጋር የ1 /አንድ/ ቀን ውይይት ባህር ዳር ከተማ ላይ ተካሂዷል፡፡ Freedom fund ከተባለ ድርጅት ጋር በመተባበር የአዲስ አበባ የትብብር ጥምረትና የፍልሰት ምክር ቤት አሰራርና አደረጃጀትን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል፡፡ በውይይቱ ላይ ከፍትህ ቢሮ፣ ከቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከስራና ስልጠና ከሴቶችና ህጻናት ቢሮዎች ከፍተኛ አመራሮችና ዳይሬክተሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በዩኤስኤይድ የበጀት እና የቴክኒክ ድጋፍ የዐቃብያነ ህግ ስነ-ምግባር፣ የደረጃ እድገት እና የአፈፃፀም ምዘናን በሚመለከት የተዘጋጀውን ማንዋል ለማስተዋወቅ የሚያስችል የቫሎዴሽን ወርክሾፕ (ከዩኤስ ኤይድ ፍትህ ተግባራት በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር) የማካሔድ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመድረኩ ላይ ወ = 83 ሴ = 4 ድ = 87 ሰዎች ተሳታፊ ነበሩ፤

በዩኤስ ኤአይዲ ፍትህ ተግባራት በኢትዮጵያ ትብብር አማካኝነት የተካሔደውን ተቋማዊ የዳሰሳ ጥናት ውጤት እንዲቀርብ ተደርጓል፤ በመድረኩ ላይ ወ = 33 ሴት = 1 ድምር = 34 ሰዎች ተሳታፊ ነበሩ፤

በዩኤስ አይድ ፍትህ ተግባራት በኢትዮጵያ አማካኝነት ይከናወኑ የነበሩ የፕሮግራም ስራዎች በመጠናቀቃቸው ምክንያት በባህር ዳር ከተማ የነበሩ የተለያዩ የቢሮ እና የመስሪያ እቃዎችን የመረካከብ ስራ ተሰርቷል፤

**ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/ በስራ ቦታ መከላከልን በተመለከተ**

በስራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከል ስራ ለመስራት ዓመታዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ የተላከ ሲሆን ለዕቅዱ ማስፈፀሚ የሚሆን 100,000.0 ብር በጀት ተይዟል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ 9 ወራት በሰራተኞች የኤድስ ፈንድ መዋጮ ለሚረዱ ችግረኛ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ እየተደረገ ሲሆን 2 ሴት ችግረኛ ህፃናትን በየወሩ 600 ብር እና በመ/ቤታችን ከሚገኙ ወንድ-1 ሴት-1 ድ-2 ሰራተኛ በወር 400 ብር ድጋፍ በማድረግ በድምሩ 4 ችግረኛ ሰዎችን ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ 9 ወራት ውስጥ ለወርሃዊ ክፍያ 18,000.00 ለአዲስ ዓመት የበዓል መዋያ 5,000.00 በድምሩ 23,000.00 ብር ወጪ ተደርጓል፡፡

የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ አፈጻፀማችን ከእቅዱ አኳያ ገና ብዙ ያልተሰራበትና በቀጣይ ትኩረት ተደርጎበት ሊሰራ የሚገባ ተግባር መሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል:: ይሁን እንጂ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥሰት በመከላከልና ምላሽ በመስጠት በኩል እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራሩን ከማጠናከር አኳያ ጅማሮው ጥሩ ቢሆንም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር የበለጠ ለማጠናከር በአዲስ መልክ የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ስራውን አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ይሆናል፡፡

## 2.3.7. ይቅርታ ቦርድ

በክልላችን በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች በዝውውር መጥተው እየታረሙ የሚገኙ የፌዴራል ታራሚዎች ውስጥ የይቅርታ መስፈርቱን የሚያሙሉ እና ማስረጃቸው የተሟላላቸውን 15 ታራሚዎች በፌዴራል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ይቅርታ እንዲሰጣቸው ማስረጃዎችን የመላክ ስራ ተሰርቷል፡፡

በክልላችን በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች በዝውውር መጥተው እየታረሙ የሚገኙ የፌዴራል ታራሚዎች ውስጥ የይቅርታ መስፈርቱን የሚያሟሉና ማስረጃ ከተላከላቸው ታራሚዎች 3 ታራሚዎች በይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የይቅርታ ምስክር ወረቀት የተላከላቸው፣ 4 ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ ደግሞ ውድቅ በማድረግ የፌዴራል ይቅርታ ቦርድ ወስኖ የተላከ በመሆኑ በውሳኔው መሰረት እንዲፈፀም ለክልሉ ማ/ቤት ኮሚሽን የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

2 በሰው መግደል ወንጀል የተፈረደባቸው የፌደራል ፍርደኞችን የፌደራል የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት የይቅርታ ጉዳዩን አይቶ ለመወሠን ማስረጃ አሟልቶ የመላክ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በዝውውር ወደ አማራ ክልል የመጡ ታራሚዎችን ማስረጃ እንዲላክላቸው በተደጋጋሚ በጠየቁት መሰረት ማስረጃው ፍርዱን ከሠጠው አካል እንዲመጣ ከሚመለከተው የማረ/ቤቶች ኮሚሽን ጋር በመነጋገር እንዲመጣ እና የመጣውን ማስረጃ ለቦርዱ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ በ2010 ዓ.ም ምህረት ተደርጐለት የነበረ ሰው ምህረት የተደረገለት ሰርተፊኬት ማስረጃ የጠፋበት መሆኑን ማስረጃ እንዲሰጠው በጠየቀው መሠረት ይህን ተረጋግጦ ማስረጃውን የመስጠት ስራ ተሰርቷል፣

በ2015 ዓ.ም የሚሰጠውን ይቅርታ ምክንያት በማድረግ በክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ ሥርዓት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 136/1998 ዓ.ም እና ይህንኑ ለማስፈጸም በወጣው የተሻሻለው የይቅርታ መስፈርት መወሰኛ መመሪያ ቁጥር 30/2010 ዓ.ም የተደነገጉ መስፈርቶችን ያሟሉ፡-ወንድ-4,308 ሴት-93 በድምሩ-4,401 ታራሚዎች በይቅርታ እንዲፈቱ ለቦርድ በማቅረብ የቦርዱን የውሳኔ አስተያየት ውሳኔ እንዲሰጥበት ለመስተዳድር ምክር ቤቱ በመላክ ምክር ቤቱ ባደረገው ስብሰባ በይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

በማጭበርበር ወይም በሃሰተኛ ማስረጃ የተለቀቁ ታራሚወች ከተገኙ ማሰረጃወችን በማጣራት ይቅርታው እንዲሰረዝ ለቦርድ ማቅረብ እና ማስወሰን ይቅርታው ተሰርዞ ታራሚወች ቅጣታቸውን እንዲጨርሱ ለማድረግ ታቅዶ በዚህም መሰረት ወንድ 13 ሴት 0 ድምር 13 ታራሚወች በማጭበርበር ይቅርታ የተሰጣቸው መሆኑን እና ይቅርታቸው እንዲሰረዝ ለቦርድ አቅርቦ በማስወሰን ለምክር ቤቱ በመላክ

ይቅርታቸው እንዲሰረዝ ተደርጎ የሚመለከተው አካል በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽም የማሳወቅ እና ክትትል የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በክልላችን የሞት ፍርድ ቅጣት ተወስኖባቸው በክልላችን ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ፍርደኞች ቅጣቱ እንዲሻሻልላቸው ወይም ይቅርታ እንዲደረግላቸው በፌደራል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት በኩል በሚመለከተው አካል አቤቱታቸው እዲታይ ልከው ምላሽ ያልተሰጣቸው እና አሁንም አቤቱታ እያቀረቡ ያሉ ታራሚወችን በተመለከተ አቤቱታቸው ምላሽ እንዲያገኝ ከፌደራል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ጋር የመነጋገር ስራ ተሰርቷል፡፡

4 በሰው መግደል ወንጀል ተፈርዶባቸው ባህርዳር እና ሞጣ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ታራሚወች በይቅርታ እንዳይፈቱ በሟች ቤተሰቦች በኩል የቀረቡ አቤቱታወችን አጣርቶ ምላሽ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡

በሀሰተኛ ማስረጃ ይቅርታ ተጠቃሚ በመሆን ከእስር ተፈቷል የተባለን አቤቱታ ምርመራ እንዲጣራ ለክልል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ የስራ ክፍል እና ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ የመጠየቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

2014 ዓ/ም በማረሚያ ቤት ሁነው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ እና የማካካሻ ትምህርት እንዲወስዱ ጥሪ የተደረገላችሁ ተማሪያዎች ይቅርታ እንዲደረግላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ከመመሪያው አኳያ ምላሽ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በክልላችን የሞት ፍርድ ቅጣት ተወስኖባቸው በክልላችን ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ፍርደኞች ቅጣቱ እንዲሻሻልላቸው ወይም ይቅርታ እንዲደረግላቸው በፌደራል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት በኩል በሚመለከተው አካል አቤቱታቸው እዲታይ ልከው ምላሽ ያልተሰጣቸው እና አሁንም አቤቱታ እያቀረቡ ያሉ ታራሚወችን በተመለከተ በፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚታዩ የህግ ታራሚወች የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 966/2015 ወጥቶ በስራ ላይ የዋለ እና በክልል ፍርድ ቤቶች የሞት ቅጣት ፍርድ ተወስኖባቸው ማረሚያ ቤት የሚገኙ ታራሚወችን የይቅርታ ጉዳይ የሚሸፍን በመሆኑ መደበኛ የይቅርታ ማጣራት ስራው ሲሰራ የእነዚህም ታራሚወች ተጣርቶ እንዲላክልን ለማረሚያ ቤት ኮሚሽን የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

በፌደራል ይቅርታ ቦርድ የሚታዩ የህግ ታራሚወች የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና እና አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 966/2015 ወጥቶ በስራ ላይ የዋለ በመሆኑ በክልላችን ማረሚያ ቤቶች በዝውውር

መጥተው እየታረሙ የሚገኙ የፌደራል ታራሚወች ይቅርታ በመመሪያው መሰረት ተሰርቶ እንዲላክ ለሚመለከተው ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

በክልላችን የሚገኙ በዝውውር የመጡ የፌዴራል ታራሚዎች፣ በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ተፈርዶባቸው በክልላችን የሚገኙ ታራሚዎች የፌዴራል ጉዳይ ሆኖ በውክልና በክልላችን ፍርድ ቤቶች ታይተው የመጨረሻ ፍርድ አግኝተው በየማረሚያ ቤቱ የሚገኙ ታራሚዎችን ይቅርታ ጉዳይ የክልሉ ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት አጣርቶ ለቦርድ በማቅረብ የውሳኔ ሀሳብ በማሰጠት ለፌዴራል ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት እንዲላክ ውክልና የተሰደጠው በመሆኑ በውክልናው መሰረት እያንዳንዱ ማረሚያ ቤት የፌዴራል ታራሚዎችን የይቅርታ ጉዳይ አጣርተው እንዲልኩ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

### 2.3.8. የመስሪያ ቤቱ የኮምኒኬሽን ተግባራት አፈጻጸም

ዜና በ12 ወራት 44 ዜናዎች ለመስራት ዕቅድ ተይዞ 48 ዜናዎች ተሰርተዋል፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫ በበጀት ዓመቱ 4 ጋዜጣዊ መግለጫ ለማሰጠት ዕቅድ ተይዞ 4 ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡ በ13 ርዕሰ ጉዳዩች የሕግ ሙያዊ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ከዩኤስ አየ አይ ዲ ፍትህ ተግባራት በኢትዮጵያ ጋር በመተባበር 2 ፕሮገረራሞች በቴሌቪዥንና ሬድዮ ተሰርቷል፡፡ በአዲስ ዓመት ተቋሙ/ ቢሮው ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በኤፍ/ኤም ሬድዮ 21 ጊዜ በድግግሞሽ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ የዜና ጥቆማን በተመለከተ በ17 የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩች ለመገናኛ ዘዴዎች የዜናና የፕሮግራም ዘገባ ሽፋን እንዲሰጡ ጥቆማ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የፓናል ውይይት ማዘጋጀት ዕቅድ 2 ክንውን 1 ተደርጓል፡፡ ድረ-ገጽ በተመለከተ በመስሪያ ቤቱ የፌስቡክ አድራሻ 966 መረጃዎች ተጭነዋል፡፡ የተከታይ ቁጥር 23,830 ሰዎች ናቸው፡፡ በተመሣሣይ በቴሌግራም ገፃችን ተመሣሣይ መረጃዎች የተጫኑ ሲሆን 2,233 ተከታይ ሰዎች አሉት፡፡ በቲውተር እና የዩቲዩብ ገፃችን የተመረጡ መረጃዎች ተጭነዋል፡፡

በየደረጃው የለውጥ ኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ በመዘርጋት በስትራቴጂው መሰረት የተደራጀ የተተነተነና ወቅታዊ መረጃ ለሕብረተሰቡ፣ ለባለድርሻ አካላትና ለፈጻሚ ሠራተኞች የማድረስ፣ ግንዛቤ የማስጨበጥና የተቋሙን ገጽታ ለመገንባት ያስቻሉ ተከታታይ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በመሆኑም የተሰሩ ስራዎችን በማስተዋወቅ አቃቤ ህጎች፣ የአስተዳደር ሠራተኛዉ እና ባለድርሻ አካል ብሎም ሕብረተሰቡ ለለውጡ ቀጣይነትና ለፍትሕ ስርዓቱ ተልዕኮ መሳካት ባለቤትና አጋዥ ኃይል ለመፍጠር የሚያስችሉ ስራዎች እየተከናወኑና አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡

በዚህም መሰረት የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸውን የተመረጡ መዝገቦችን ለይቶ አስተማሪ ዜናዎችን በመስራት በየደረጃው ተከታታይ የሆነ መረጃ ለሚዲያዎች ተሰጥተውና የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙና እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም 4 ወቅታዊ በሆኑና በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ጋዜጣዊ መግለጫ እና በ9 ርዕሰ ጉዳዮች በዐቃብያነ-ህግ ሙያዊ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም በየደረጃው የፍትሕ እና ሕግ ነክ ዜናዎች በማዘጋጀትና ለባለድርሻ አካላት በማሰራጨት በለውጡ ሒደት ላይ የተከናወኑ ተግባራትን የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ የተከናወኑ ስራዎችን በሬዲዮና በቴሌቪዥን የአየር ላይ ሽፋን እንዲያገኙ የዜና ጥቆማ በመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

የመስሪያ ቤቱ ባለሙያዎች በተለያዩ ህግ ነክ ጉዳዮች ላይ በአካል እና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የህብረተሰቡን የህግ እውቀት ክፍተቶች ላይ ተመስርተው የህግ አስተያየት፣መግለጫ እና ማብራሪያ ሲሰጡ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በክልላችን ውስጥ የፍትሕ ዘርፉን እንቅስቃሴ አስመልክቶ በሚዲያ የሚወጡ አሉታዊ እና አዎንታዊ ዘገባዎች ላይ ክትትል እየተደረገባቸው የተዛባ አስተሳሰብና አመለካከት ያላቸውን የማስተካከል ተግባር በተከታታይ ተከናውኗል፡፡ የክልልና የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን በሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ማብራሪያዎችን እና መግለጫዎችን የመስጠት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ፣ የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲሁም የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎትን በማጠናከርና ስራዎችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የመደገፍ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በፍት ቢሮ ደረጃ የተዘጋጀውን የማኅበራዊ ሚዲያ፣ ድህረ ገጽ በመጠቀምም መረጃ በመስጠት ረገድ ትልቅ አስተዋጾ እያበረከተ ነው፡፡

ሆኖም ግን ሕብረተሰቡ የፍትሕ ስርዓቱን የሚያውቅበት የግንዛቤ ማስጨበጫ የኮሚኒኬሽን ስራ በተፈለገዉ ደረጃ አለመድረሱ፣ የምክክር መድረኮች እንዲሰፉና ያስገኙትን ዉጤት ገምግሞ ለህብረተሰቡ መረጃ ለመስጠት የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆን፣ መልካም ተሞክሮዎችን ቀምሮ የማስፋፋት ስራ ዉስንነትና የተቋሙን መረጃ በቴክኖሎጂ እየታገዙ አደራጅቶ የመያዝ እና በመስሪያ ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ተደራሽ በማድረግ በኩል እጥረት የተስተዋለ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡

### 2.3.9. የፍትሕ ባለሙያዎች ማሠልጠኛና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት አፈጻጸምን በሚመለከት

የክልሉ የዳኞች ስነ-ምግባር ደንብ መሻሻሉን ተከትሎ ለቅድመ ስራ ስልጠና የሚውለው የዳኝነት እና ስነ-ምግባር ሞጁል በከፊል የማሻሻል ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በተሻሻለው ካሪክለም መሰረት እና እንደ ሀገር እየተከናወነ ያለውን ለውጥ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በህገ-መንግስት ስልጠና ላይ ውጤታማ ስልጠና መስጠት ይቻል ዘንድ የህገ-መንግስት ሞጁል በአዲስ መልክ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ በተሻሻለው የቅድመ ስራ ስልጠና ካሪክለም መሰረት ለሚሰጠው የአስተዳደር ውል፣ ግዥ መምሪያ እና ኮንስትራክሽን ህግ ስልጠና ሞጁል እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

የ14ኛ ዙር የቅድመ ስራ ሰልጣኖችን ለመቀበል ምልመላ በማድረግ ወንድ 188 ሴት 106 ድ-294 በመቀበል በፍ/ቤቶችና ፍትህ ጽ/ቤቶች ተመድበው የተግባር ልምምድ ስልጠናውን ወስደው የተመለሱ ሲሆን ያዘጋጁትን የተግባር ልምምድ ሪፖርት መገምገም ተችሏል፡፡ ከተግባር ልምምድ በኋላ ልዩ ልዩ አዋጅና መመሪያዎች ላይ ስልጠና ተሰጥቶ የሰልጣኞች የስልጠና አቀባበል ምዘና ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ጥቅል የስልጠና እቅስቃሴ አመለካከትና ስነ-ምግባር ምዘና ተከናውኖ የስነ-ምግባር ጉድለት የታየባቸውን ሰልጣኞች በመለየት ምክር ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተደረገ ድጋፍና ክትትል የስነ-ምግባር ጉድለት የታየበትን 1 ሰልጣን በዲሲፕሊን መመሪያው መሰረት ተሰናብቷል፡፡ በዚህም መሰረት 173 ለዳኝነት 121 ለዐቃቤ ህግነት ተመድበዋል፡፡

በ13 ዙር የቅድመ ስልጠና በተግባር ልምምድ እያለኩ ከነበረው ፀጥታ አንፃር መመለስ ያልቻሉ 3 ሰልጣኞች ስልጠናውን እንዲቀጥሉ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

የ15ኛ ዙር የቅድመ ስራ ሰልጣኞችን የመመዝገብ ስራ በመስራት ወንድ-212 ሴት-79 ድምር-291 ሰልጣኞች በመቀበል ስለ ሥልጠናው አሰጣጥ፣ በሥልጠና ሂደት ስለሚኖራቸው ሚና፣ ሊከተሉት ስለሚገባው የሥነ-ምግባር ደንብ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ኦረንቴሽን ተሰጥቷቸው በስልጠና ላይ ይገኛል፡፡ የዳኞች እና ዐቃብያነ-ህግ ሥነ-ምግባር እና የቅጣት አወሳሰን ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በስልጠናዎች ላይ የሠልጣኞችን የስልጠና አቀባበል ሁኔታን ለመመዘን የሚያስችል አንድ ፈተና በመፈተን የምዘና ተግባር ለማከናወን ተችሏል፣

ለሰልጣኞቹ በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት እና ፍ/ቤቶች የተግባር ልምምድ ኦረንቴሽን ለሠልጣኞች ተሰጥቷቸዋል፣ በክልሉ ውስጥ ባሉ በተመረጡ 85 ወረዳዎች በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች እና በወረዳ ፍ/ቤቶች የተግባር ልምምድ እንዲያከናውኑ ስምሪት የተሰጠ ሲሆን በስምሪቱ መሰረትም በወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት የሚያከናውኑትን የተግባር ልምድ በማጠናቀቅ በወረዳ ፍ/ቤቶች የ3 ወር የተግባር ልምምድ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፣ ዓይነ-ሥውራን ሠልጣኞች በተግባር ልምምድ ወቅት

ውጤታማ ተግባርን ማካናወን እንዲችሉ አናባቢ ሠራተኞችን በኮንትራት ቅጥር በመቅጠር በየወረዳው አብረዋቸው እንዲሚደቡ ተደርጓል፣ የተግባር ልምምድ እያደረጉ ላሉ ሠልጣኞች ድጋፍ ለማድረግ እና የተግባር ልምምዱን ሱፐርቫይዝ ለማድረግ የሚያስችል የድጋፍ እና ሱፐርቪዥን ሥራ ለመስራት የባለሙያዎች ስምሪት በመስጠት የድጋፍ እና ሱፐርቪዥን ሥራ ለማከናወን የተቻለ ተችሏል፡፡ በተቋሙ የባለሙያ እጥረት በማጋጠሙ ምክንያት በሁሉም ቦታ ለተመደቡ ሰልጣኞች ድጋፍና ክትትል ማድረግ አልተቻለም፡፡ በዚህም በድጋፍ እና ሱፐርቪዥን ስምሪት መሰረት ውጤታማ ተግባርን ማከናወን እንዲቻል መስተካከል የሚገባቸውን ክፍተቶች ለመለየት ተችሏል፡፡

የ14ኛ ዙር የቅድመ-ሥራ ሥልጠና ወቅት ተመልምለው ሲሰለጥኑ ከነበሩ ሠልጣኞች መካከል 1 ሠልጣኝ በጤና ችግር ምክንያት ሥልጠናውን እንዲያቋርጥ ተደርጎ የነበረ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በመያዝ እና ሌላ ሰልጣኝ በህግ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ምክንያት ተጠይቆበት በነበረው ወንጀል እንደማይፈለግ ከወረዳው ፍትህ ጽ/ቤት እና መርማሪ ፖሊስ ማስረጃ በማቅረቡ ምንያት 2ቱም ግለሰቦች ያቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን ካቋረጡበት ከ15ኛ ዙር እንዲቀጥሉ ተደርጓል፣ በስልጠና ሂደትም ስልጠና ያቋረጡ 7 ሰልጣኞች በመኖራቸው በአሁኑ ወቅት ወንድ 214 ሴት 79 ድምር 293 ሰልጣኞች በስልጠና ላይ ናቸው፡፡

**የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በተመለከተ**

በማስረጃ ህግ ላይ ለሚሰጡ ስልጠናዎች ሞጁል ዝግጅት የመዝገብ ምልከታና መረጃ ስብሰባ በማካሄድ የሞጁል ዝግጅቱ የማጠቃለል ስራ ተሰርቷል፡፡ በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀም ጥቃት ረቂቅ የስልጠና ሞጁል ተጨማሪ ግብዓት በማሰባሰብ ነጥቦችን የማሟላት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተሸሻለው የቅድመ ስራ ስልጠና ካሪክለም መሰረት በአስተዳደር ውል፣ ግዥ መመሪያ እና የኮንስትራክሽን ህግ ላይ ለአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዙሪያ ወ-357 ሴ-66 ድ-423 ለሚሆኑ ዐቃብያነ-ህግ፣ ዳኞችና ፖሊሶች እንዲሁም ለንግድ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/2014 እና በተሻሻለው የአማራ ክልል ፍ/ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅን ቁጥር 282/2014 ላይ ለዳኞች ለወንድ 147 ሴት 33 ድምር 180 ለወረዳ እና ለዞን ዳኞች ሥልጠና መስጠት ተችሏል፡፡ በጠቅላላ በ9 ወራት ወንድ 504 ሴት

99 ድምር 603 በበጀት ዓመቱ 1,000 ለሚሆኑ የህግ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ከተያዘው እቅድ አንፃር አፈፃፀሙ 60.3% ነው፡፡

**የህግ ጥናትና ምርምር በተመለከተ** በክልሉ የፍትህ ተቋማት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በፍትህ አስተዳደሩ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያሳደረ ያለው አንድምታ በሚል ርዕስ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ 1 የህግ መምህር እንዲመደብ በማድረግ በጋራ የጥናት ፕሮፖዛል እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ በሰው መነገድና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እየተሰወሰዱ ያሉ እርምጃዎችና ውጤቶች በአማራ ክልል በሚል ርዕስ ለሚሰራው የጥናትና ምርምር ስራ የተዘጋጀውን ፕሮፖዛል የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡ ዓመታዊ የጥናትና ምርምር መፅሄት ግብዓት ከተጋባዥ ፀሀፊ መቀበል እና በበጀት እጥረት ምክንያ ሳይታተም የቀረ ዓመታዊ የጥናትና ምርምር መፅሄት ለማሳተም ጨረታ እዲወጣ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሊከናወኑ በዕቅድ ከተያዙት 2 ሙሉ የሕግ ጥናትና ምርምር ሥራዎች መካከል “በክልሉ የፍትሕ ተቋማት መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በፍትሕ አስተዳደሩ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያሳደረ ያለው አንድምታ” በሚል ርዕስ እየተከናወነ ለሚገኘው የምርምር ሥራ አስፈላጊው የጥናት መነሻ-ሀሳብ (ፕሮፖዛል) እንዲዘጋጅ በማድረግ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎች ከ3 ዞኖች ማለትም ከምስራቅ ጎጃም፣ ከአዊ ብ/ሰብ አስ/ር እንዲሁም ከማዕከላዊ ጎንደር ዞኖች በባለሙያው አማካኝነት የመሰብሰብ ተግባር ተከናውኖ መረጃዎችን የመተንተን ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

የክልሉን የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባራት ለመወሰን ከወጣው አዋጅ ቁጥር 280/2014 ዓ.ም ጋር በተገናኘ ከተለያዩ ተቋማት ለፍትሕ ቢሮ የቀረበውን ጥያቄ ተከትሎ በአዋጁ ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶችን በመለዬት ለቢሮው የመላክ ተግባር ተፈጽሟል፡፡

በ2013 ተዘጋጅቶ የነበረ ቅፅ 8 መፅሄት የማሳተም ስራ ተሰርቷል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የሕትመት ውጤት ለሆነው ቅፅ-9 ዓመታዊ የጥናትና ምርምር መፅሔት ግብዓት የሚሆን አንድ አጭር የጥናትና ምርምር ፅሁፍ ከተጋባዥ ፀሐፊ የመቀበልና የአርትዖት ሥራ የማከናወን ተግባር ተፈፅሟል፡፡

ወንጀሎችን በበቀል ተነሳሽነት ከመፈፀም እና ከይቅርባይነት ጋር በተገናኘ ያለውን የሕግ ማዕቀፍ በተመለከተ በአማራ ራዲዮ የቀጥታ ሥርጭት ላይ ሙያዊ ማብራሪያ የመስጠት ተግባር ተከናውኗል፡፡

# 3. ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች

ቢሮው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ዓ/ም የክልሉን የአስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት በወጣው አዋጁ እንደገና አዋጅ መሰረት የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባራትን በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በዋናነት ያለው ሀብት የሰው ኃይል በመሆኑና የሰው ኃይሉን እንደ ከፍተኛ ሀብት በመቁጠር በአግባቡ መጠቀም የሚኖርበት ሲሆን ምንም እንኳን የሰው ሀይል እጥረቱና ፍልሰቱ ክፍተኛ ቢሆንም ባሉት ፈፃሚዎች አማካኝነት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅዱን በውጤታማነት ለመምራት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መ/ቤቱ ካሉት የዐ/ህግ እና የአስተዳደር ሰራተኞች መካከል ከ1,703 ዐ/ህግ ውስጥ 1,236 (77.11%) የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ እንዲሁም ከ1,759 የአስተዳደር ሰራተኞች መካከል 618 (35.29%) የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ በድምሩ ከ3,354 ጠቅላላ ዐ/ህግና የአስተዳደር ሰራተኞች ውስጥ 1,854 (55.3%) የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ሲሆኑ ይሄንን ሀይል በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ በተቋሙ ላይ የሚፈለገውን ውጤት በማምጣት የህብረተሰቡን የፍትህ ፍላጎት ማሳካት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የቢሮውን ተልዕኮና ራዕይ ዕውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ካለን የሰው ኃይል በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 150 ዐ/ህግ እና 100 የአስተዳደር ሰራተኞች በተጨማሪነት የሚያስፈል ሲሆን በተጨማሪነት ከሚስፈልገን የሰው ኃይል ጎን ለጎን የፈፃሚዎችን አቅም ለማሳደግ በዲፕሎማ ደረጃ ያሉ ሁሉን ዐ/ህግ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲማሩ በማድረግ፣ ለ20 ዐ/ህግ እና ለ5 የአስተዳደር ሰራተኞች የ2ኛ ዲግሪ፣ ለ1 ዐ/ህግ ወይም የአስተዳደር ሰራተኛ የ3ኛ ዲግሪ ትምህርት እንዲገኙ በማድረግ አቅማቸውን በመገንባት ይህንንም የሰው ኃይል በመያዝ በተለይም በወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች የሚቀርቡ መዛግብት ላይ ፈጣን ውሳኔ መስጠት /የማጥራት አቅማችንን/ በማሳደግ፣ ወንጀለኞችን የማስቀጣትም ሆነ በፍትሃብሄር ጉዳዮች የማሸነፍ አቅማችን እንዲጨምር በማድረግ፣ በሰነዶች ምዝገባና ቅልጥፍና ላይ፣ በህግ ምክርና ማርቀቅ ረገድ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ስለሚሆን የሰው ኃይላችንን በብቁ ሁኔታ ማሟላትና የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት በሚያስችል ደረጃ ላይ ማድረስ ይጠበቅብናል፡፡

ስለሆነም በበጀት ዓመቱ ከዚህ በበለጠ ተከታታየነት ያለው የፈፃሚውን የመፈፀም አቅም የማሳደግ ስትራቴጂ በማዘጋጀት ተቋሙን በውጤታማነት ማስቀጠል ይጠበቃል፡፡

# 4. የዕቅዱ መነሻዎች፣ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዓላማዎች፤ ግቦች እና የትኩረት አቅጣጫዎች

## 4.1. ለቀጣይ እቅዳችን መነሻዎች

በ2015 በጀት አመት ቢሮው የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ለመቆየቱ በቀረበው የስራ ግምገማ ላይ አጠር ባለ መልኩ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በዚሁ ግምገማ የነበሩትን የአፈጻጸም ክፍተቶችና የተገልጋይ ፍላጐቶች ተለይተው ተልኮውን ከመፈጸም አንጻር ችግሮችን ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የሕግ የበላይነትን ለህ/ሰቡ ተደራሽ ለማድረግና እያጠናከሩ ለመሔድ በግምገማው የተለዩትን ክፍተቶችን እንዲሁም ከባለፈው የእቅድ በጀት ዓመት ያልተጠናቀቁ ተግባራትን መሰረት በማድረግ የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችሉ የዕቅዱ መነሻዎች፡-

የፌዴራልም ሆነ የቢሮው የ10 ዓመቱ (2013-2022) መሪ ዕቅድ፣ የአመራር መለኪያ ዕቅድ ሰነድ፣ ከUSAID Fitih Activity ጋር በመተባበር የተሰራው ተቋማዊ የ5 ዓመት (2015-2019) ዕቅድ፣ የፍትህ ተቋማት ሪፎርም ሰነድ፣ ሀገራችንና ክልሉ ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ ግምገማ፣ የዘርፉ ርዕይ፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፡-SDG/Sustainable Development Goals/ ዘላቂ የልማት ግቦች 17 ግቦች ያሉት ሲሆን 16ኛው ግብ ሰላማዊና ሁሉን አቀፍ ማህበረሰቦችን ለዘላቂ ልማት ማጎልበት፣ ፍትህ ለሁሉም ተደራሽ እና ውጤታማ ማድረግ ተጠያቂ እና አካታች ተቋማት በየደረጃው መገንባት በሚል የተቀመጠ በመሆኑና ቢሮው ይህንን ግብ ውጤታማ ማድረግ የሚጠበቅበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የአፍሪካ አጀንዳ 2063 በአለምአቀፍ አውድ ውስጥ በሚገባ የምትመራ፣ ሰላማዊ እና የባህል ማዕከል የሆነች አፍሪካ በመፍጠር በአፍሪካ ዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር እሴቶች እና ባህል በ2023 እንዲጠናከር ማድረግና ጥይት የማይሰማባት አፍሪካን መፍጠር የሚል ሲሆን ቢሮአችንም በዘላቂ የልማት ግቦችና በአፍሪካ አጀንዳ 2063 የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የበኩሉን አስተዋፅ መወጣት የሚጠበቅበት ሲሆን የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ትግበራ የተመዘገቡ መልካም ውጤቶችና በትግበራው ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችና ያጋጠሙ ፈተናዎች፣ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም ከባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችና ለውጦች በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሊያሳድሩት የሚችሉ አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች በልማት ዕቅዱ እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

## 4.2. የትኩረት አቅጣጫዎች

የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ የመንግስትና ህዝብን ጥቅም በማስከበር በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ውስጥ የልማትን ጉዞ በማፋጠን የ2015 በጀት አመት እቅዱን በማሳካት የተጀመረውን የልማት፣ የሰብዓዊ መብት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ለማሳደግ የህግ የበላይነትን በማስከበር የህብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት የተረጋገጠ እንዲሆን፤ የህብረተሰቡን ህገ-መንግስታዊ መብት እንዲረጋገጥ በማድረግ የፍትህ ስርዓቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊና ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ እቅድ ውስጥ ትኩረት የሚሠጥባቸው አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

## 4.3. ተልዕኮ

ሕገመንግስቱን፣ ሰብዓዊ መብትን እና ሕግን ማክበርና ማስከበር፤ ወንጀል በመከላከልና የወንጀል ህግን በማስከበር የህዝብ፣ የመንግስት እና የግለሰቦችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ፤ የመንግስትንና የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ፤ የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ ማሳደግ፤ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ የፍትህ አገልግሎት መስጠት፡፡

## 4.4. ርዕይ

በ2022 ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበረበት፤ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት፤ ፍትሕ የሰፈነበት ብሔራዊ ክልልን በመፍጠር ለተምሣሌነት የሚበቃ ተቋም ሆኖ ማየት፣

## 4.5. የተቋሙ መሰረታዊ እሴቶች

- ✓ ሰብዓዊ መብትን ማክበር፤
- ✓ ተደራሽነትና ውጤታማነት፤
- ✓ ቅንጅታዊ አሰራር፤
- ✓ ታማኝነት፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት፤
- ✓ በህዝብና በህግ የበላይነት የጸና እምነት፤
- ✓ የህዝብ አገልጋይነት፤
- ✓ የህዝብና መንግስት ጥቅሞችን ማስቀደም፤
- ✓ የተሟላ እውቀትና ብቃት፤
- ✓ አሳታፊነትና በቡድን የመስራት ባህል፤

- ✓ ሙያዊ ስነ-ምግባር፤
- ✓ ለለውጥ ዝግጁነት፤
- ✓ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን መፀየፍ፤

## 4.6. የባለ ድርሻዎች እና የአጋር አካላት ትንተና፣

የአብክመ ፍትህ ቢሮ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመፈጸም የራሱ ጥረት ብቻ በቂ አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ተቋሙ በሚያከናውናቸው ተግባራትና በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ባለድርሻ አካላት እንደጠቃሚነታቸው ሁኔታ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሣድራሉ፡፡ ስለሆነም በአፈጻጸም ሒደት ውጤታማ ለመሆን ይቻል ዘንድ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በጥንቃቄ ማስተናገድ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ መሰረተ ሐሣብ በመነሣት የውስጥና የውጭ ባለድርሻና የአጋር አካላት ትንተና ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

### 4.6.1. የውስጥ ባለድርሻ አካላት ትንተና

ሰንጠረዥ1 የውስጥ ባለድርሻ አካላት ትንተና

| ተ/ቁ | ባለድርሻ አካል | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | በመስሪያ ቤቱ በኩል የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመ/ቤቱ የበላይ አመራር | - የመስሪያ ቤቱ ራዕይ፣ ተልኮና እቅድ ተግባራዊ እንዲሆን፤ | - መ/ቤቱ የተቋቋመበትን አላማ ከግቡ ለማድረስ ይሣነዋል፡፡ | - ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ውጤት ማስመዝገብ፤ |
| 2 | የአቃቤያነ-ህግ አስተዳደር ዋና ጉባዔ | - በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ ዓቃቤያነ-ህግን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችና የሚተላለፉ ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ፤<br>- የተሻለ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲያገኙ፤<br>- የዐቃብያነ ህግን ስነ ምግባር እንዲሻሻል፤ | - አቃቤ ህጎች መብታቸዉ እንዳይከበር እና ግዴታቸውን እንዳይወጡ ያደርጋል፤<br>- የስራ ተነሣሽነት ይቀንሣል፤<br>- ኃላፊነትን መወጣት ያዳግታቸዋል፤<br>- በተገልጋይ ላይ ጉዳት ያመጣል፤<br>- የዐቃብያነ ህግ ፍልሰት ይኖራል | - ጉባዔው ወቅቱን ጠብቆ በመገናኘት ውሳኔዎችን እንዲሰጥ እና ውሳኔዎች እንዲከበሩ ማድረግ፤<br>- የዐቃብነ ህግን ስነ-ምግባር መገንባት፣ |
| 3 | የቢሮው ማኔጅመንት ኮሚቴ | - የመ/ቤቱ የስራ እቅዶች፣ አግባብነት ያላቸው ህጎች፣ የሚተላለፉ ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ | - የስራ ተነሣሽነትና ውጤታማነት ይቀንሣል<br>- ኃላፊነትን መወጣት ያዳግታቸዋል | - የስራ እቅዶችን፣ ሪፖርቶችን፣ ህጎች፣ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን በትጋት ተግባራዊ ማድረግ፤<br>- በኃላፊነት መንፈስ እንዲሰራ |

| ተ/ቁ | ባለድርሻ አካል | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | በመስሪያ ቤቱ በኩል የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| | | - ተገቢው ሪፖርት እንዲቀርብለት ይፈልጋል<br>- ለስራ አስፈላጊ የሆነ በጀት እና ቁሳቁስ በአግባቡ እንዲሟሉ | | ማድረግ፣ |
| 4 | የዳይሬክቶሬቶችና የስራ ክፍሎች ኃላፊዎች | - ብቃት ያላቸውና በስነምግባር የታነጹ ዐቃብያነ ህግና ሠራተኞች እንዲመደቡ፣<br>- ቀጣይነት ያለው የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲሰጣቸው<br>- ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በአግባቡ እንዲሟሉ<br>- የተሻለ ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲያገኙ ይፈልጋሉ፡፡ | - የስራ ተነሣሽነት ይቀንሣል<br>- ኃላፊነትን መወጣት ያዳግታቸዋል<br>- በተገልጋይ ላይ ጉዳት ያመጣል | - የትምህርት እድልን ማስፋት<br>- ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደብ<br>- የደመወዝና ጥቅማጥቅም ጥያቄዎችን መመለስ |
| 5 | ዐቃብያነ ህግና ሠራተኞች | - ተመጣጣኝ ደመወዝ እና የጥቅማጥቅም ክፍያ<br>- ፍትሐዊ የስራ ማነቃቂያ /ማትጊያ/<br>- ጤናማና አመች የስራ አካባቢ<br>- ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር<br>- የሙያ ነጻነት እንዲኖር፣ | - በተቋሙ ላይ እምነት ማጣት እና አለመረጋጋት፤<br>- የስራ ፍላጐት ማጣት፤<br>- ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አለመቻል፤<br>- መስሪያ ቤቱን መልቀቅ ይኖራል፤<br>- የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ ለመወጣት አለመቻልና ደንበኞችን አለማርካት፤<br>- በራስ አለመተማመን ይፈጥራል፣ | - ግልጽነትን የተላበሰ አሰራር እንዲኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤<br>- የሠራተኛውን የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ሊያዳብር የሚያስችሉ ወቅቱን የጠበቁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤<br>- ቀጣይነት ያለው የረጅም እና የአጭር ጊዜ የትምህርትና የስልጠና እድል መስጠት፤<br>- በውጤት ላይ የተመሰረተ ምዘና የደመወዝና የጥቅማጥቅም እንዲሁም የማበረታቻ ስርዓት እንዲኖር ማስቻል፤<br>- ህግን መሰረት ያደረገ የደረጃ እድገት፣ ምደባና ዝውውር መስራት፤ |
| 6 | ለቢሮው ተጠሪ የሆኑ የዞን | - ስልጠና፤<br>- ድጋፍና ክትትል፤<br>- ፍትሃዊ የሆነ የሰው ሃይል | - የክህሎት ክፍተት ይፈጥራል፡፡<br>- ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ | - ወቅቱን የጠበቀ ስልጠና መስጠት፤<br>- አስፈላጊውን ክትትልና እገዛ |

| ተ/ቁ | ባለድርሻ አካል | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | በመስሪያ ቤቱ በኩል የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| | ፍትህ መምሪያዎችና የወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች | የበጀት ድልድል | - የጉዳዮች መጓተትና የባለ ጉዳዮችን መጉላላት ያስከትላል፡፡ | ማድረግ፤<br>- ተገቢ የሆነ የሰው ሃይልና የበጀት ድልድል ማድረግ፤ |

## 4.6.2. የውጭ ባለድርሻ አካላትና የተገልጋይ ትንተና

### ሰንጠረዥ 2፡- የውጭ ባለድርሻ አካላትና ተገልጋይ ትንተና

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል/ተገልጋይ | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት | - ፖሊሲዎችን፣ ህጐችን በተለይም የፍትህ ስርዓት ማሻሻያና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ጥራትና ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ይፈልጋል፤<br>- በተጨባጭ መረጃ የተደገፈ ወቅታዊ ዕቅድና ሪፖርት እንዲቀርብ፣<br>- በጥናት የተደገፈ፣ ወቅታዊና ጥራት ያለዉ የህግ ረቂቅ እንዲቀርብ፣<br>- ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት እንዲሰጥ | - መንግሥት በተቋሙ ላይ አመኔታ ያጣል፤<br>- ድጋፍ መንፈግ፣<br>- እምነት ማጣትና በተቋሙ አመራርና የተቋሙ ህልዉና ላይ እርምጃ መዉሰድ፣ | - አሰራርና አደረጃጀትን ማሻሻል፤ ብቃት ያለው ባለሙያ ማፍራትና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፤ |
| 2 | የክልሉ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት | - መስሪያ ቤቱ በተደራጀበት አግባብና በተቋቋመበት ህግ መሰረት ፖሊሲን ህጋዊ አሰራርን አክብሮ መስራትን ይፈልጋል፤ | - ህግ የበላይነት አደጋ ላይ ይወድቃል፤ | - ህጎችን መሰረት አድርጎ አደረጃጀትንና አሰራርን መፍጠር፤ |
| 3 | የክልሉ መንግስት ምክር ቤት | - ችግር ፈች የሆኑ ህግጋት ተረቀው እንዲቀርቡለትና ለህዝብ ተደራሽ ሆነው ተግባራዊ የሚሆኑበት አግባብ እንዲፈጠር ይፈልጋሉ፤ | - የሚወጡ ህጎች እንዳይፈጸሙና ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚደረገው አሰራር ይፈጠራል፤<br>- የፍትህ ተደራሽነት እንዳይኖር ያደርጋል፤ | - በጥናት ላይ የተመሰረቱና ችግር ፈች የሆኑ ረቂቅ ህግጋት የሚዘጋጁበት ሁኔታ ማመቻቸትና የጸደቁ ህጎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል፤ |
| 4 | ፍርድቤቶች | - የሚቀርቡ ክሶችና ክርክሮች አግባብ ባላቸው ህጐችና በተገቢው ማስረጃ የተጠናቀሩ ሆነው እንዲቀርቡ ይፈልጋሉ፣<br>- በፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች መፈጸማቸው እንዲረጋገጥ<br>- ከፍ/ቤት ውጭ በተዘረጉ ዘዴዎች አቤቱታዎች እንዲፈቱና ፍ/ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች እንዲቀንሱ | - ጉዳዮች ለረዥም ቀጠሮ ይዳረጋሉ፤<br>- ባለ ጉዳዮች ይጉላላሉ፤<br>- የተዛባ ፍትህ ለመስጠት ምክንያት ይሆናል፤ | - በቂ ዓቃቤ-ህግ መመደብ፤<br>- የዓቃቤ-ህግን አቅም ማጎልበት፤ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል/ተገልጋይ | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| 5 | ፖሊስ | - በወንጀል ንቃተ ህግ በመስጠት እና ከባድ እና ውስብስብ መሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ የምርመራ እገዛ ይፈልጋሉ፤<br>- ለዓቃቤ ህግ የሚላኩ የምርመራ መዛግብት በአፋጣኝ ተመርምረው ተገቢና ጥራት ያለው ትዕዛዝ እና ውሣኔ እንዲሰጥባቸው ይፈልጋሉ፣<br>- የተጠናከረና ስራን ማዕከል ያደረገ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር፣<br>- ፖሊሳዊ የመፈፀም አቅምን የሚያሳድግ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያለው ስልጠና እንዲሰጥ፣<br>- የአሰራርና አደረጃጀት ስርአታቸዉ እንዲሻሻል፣<br>- የምርመራ ስራዎች ቴክኒካዊ ብቃታቸዉ እንዲያድግና ቴክኒካዊ ቁሳቁስ እንዲሟላላቸዉ፣<br>- በዘመናዊ ቴክኖልጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር<br>- ለወንጀል መርማሪዎች የህግ ከለላና ጥበቃ እንዲሰጥ | - በፖሊስ የወንጀል መከላከልና ህግና ስርዓት ማስከበር ዙሪያ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሣድራል፤<br>- ያላግባብ የምርመራ መዝገቦች መመለስ/መዘግየትን ያስከትላል፤<br>- ያለ በቂ ዝግጅት ክስ ስለሚመሰረት አጥፊዎች ሊለቀቁ ይችላሉ፣ ንጹሀን የሚንገላቱበት ሁኔታ ይፈጠራል፤<br>- የፍትህ መጓደል<br>- የህዝብ እርካታና አመኔታ ማጣት | - በወንጀል ምርመራና የመከላከል ስራ ተገቢውን ስልጠና የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤<br>- በቂ ዓቃቤ-ህግ መመደብ፤<br>- የዓቃቤ-ህግን አቅም ማሳደግ፤<br>- ምርመራን ተጋግዞ መስራት፤<br>- በአፋጣኝ ውሣኔ መስጠት፤<br>- ውጤት ለማስገኘት ጥረት ማድረግ፤<br>- የተጠርጣሪዎችን አያያዝ ሁኔታ መከታተል፤ |
| 6 | ስነ-ምግባርናፀረ-ሙስና ኮሚሽን | - የመንግሥት ሠራተኞችን እና ባለሙያዎችን ሥነ-ምግባር ለማነጽና ሙስናን ለመዋጋት አብሮ መስራት ይፈልጋሉ፣<br>- ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመታገል አንፃር በትብብር መስራት፣<br>- በተቋሙ የስነምግባር መከታተያ ክፍል እንዲደራጅ፣ ተቋሙ ከስነምግባር መጓደል እና ከሙስና የጸዳ እንዲሆን<br>- የስነምግባር ትምህርት ለመስጠት የሚረዳ የወንጀል ክስ ዉጤት መረጃዎች እንዲሰጣቸዉ፣<br>- የተቋሙ ሰራተኞች እና አመራሮች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ፣ | - ሙስና ወንጀል ድርጊቶች መስፋፋት የህዝቡ ሰላማዊ ኑሮ መናጋት ያስከትላል፤<br>- የሙስና መከላከል ብቃት መዳከም<br>- ሰራተኛዉ ለብልሹ አሰራር ተጋላጭ ይሆናል<br>- ተቋማዊ አመኔታ ማጣት | - ሠራተኛውንና ባለሙያው በስነ-ምግባር የማነጽና ስራዎችን መስራት ሙስናን መከላከል፤<br>- ከሙስና ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ዙርያ በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤<br>- ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤ |
| 7 | የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን | - በማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ታራሚዎች በየጊዜው እንዲጎበኙና የተጠናከረ የይቅርታ ስርዓት እንዲኖር ይፈልጋሉ፤ | - የታራሚዎች መብት ይጣሳል፤<br>- ጥራት የሌለው የይቅርታ አሰጣጥና ክትትል ይሰፍናል፤<br>- በዚህም የታራሚዎችና የህብረተሰቡ ቅሬታ ይጨምራል፤ | - በቂዓቃቤ-ህግ መመደብና አቅም መገንባት፤<br>- ቀጣይነት ያለዉ የማረሚያ ቤቶች ጉብኝት ማድረግና ጥራት ያለው የይቅርታ አሰጣጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፤ |
| 8 | ፌዴራል ፍትህ ሚ/ር | - ከፍትህ ስርዓቱ አንጻር መረጃ መለዋወጥና በዉክልና የተሰጡ ጉዳዮች በአግባቡ እንዲያዙለት ይፈልጋል፤ | - አገራዊ የመረጃ መዛነፍ ይፈጠራል፤<br>- በፌዴራል የስልጣን ደረጃ ስር የሚወድቁ ከባድ ወንጀሎች አያያዝ | - ከክልሉ ጋር የተያያዘ ተገቢዉን የመረጃ አያያዝ ስርዓት መዘርጋትና ጥቅም ላይ ማዋል፤ |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል/ተገልጋይ | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| | | - በቅንጅት መስራት፣ ተሞክሮ ልውውጥ እንዲኖር ይፈልጋሉ | ችግር የማህበረሰቡን ቅሬታ ይጨምራል፤<br>- የቅንጅት መላላት | - በውክልና የተያዙ የፌዴራል መንግስት ስልጣን ስር የሚወድቁ ወንጀሎችን ትኩረት ሰጥቶ መከታተልና ለዉጤት ማብቃት፤ |
| 9 | ህብረተሰቡ | - የህግ የበላይነት ሠፍኖ ማየት፤<br>- ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረዉለት ማየት ይፈልጋል፤<br>- ለሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ይፈላጋሉ፤<br>- ጥቆማዎች/አስተያየቶች/ አቤቱታዎች ለማን፣ እንዴትና የት እንደሚቀርቡ ግልጽ እንዲሆንላቸው፣<br>- አገልግሎቶች ፈጣን፣ ጥራት ያላቸው እና ወጭ ቆጣቢ እንዲሆኑ<br>- በተለዕኮ አፈጻጸማችን ላይ ተሳታፊ መሆን<br>- በአሰራሩ ላይ ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን<br>- አጥፊዎች በህግ እንዲጠየቁ ፣ የንጹሃን መብት እንዲጠበቅ<br>- ፍትህና የህግ የበላይነት ሰፍኖ ማየት፣<br>- የተመዘበረ የህዝብና የመንግስት ሃብት በህግ መሰረት እንዲመለስ<br>- የህግ ከለላና ጥበቃ<br>- የጥቆማ አሰጣጥ አሰራር ስርአት እንዲዘረጋላቸው<br>- ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ጥራት፣ ነጻና ተጠያቂነት ያለው የፍትህ አገልግሎት | - የሙስና መንሰራፋት፣ የወንጀል ድርጊቶች መበራከትና የህዝቡ ሰላማዊ ኑሮ መናጋት፤<br>- የፍትህ መዛባት እና በፍትህ ስርዓቱ ላይ አመኔታ ማጣት፤<br>- ተዓማኒነት ያለው የሰነድ ማስረጃ ያሳጣል፤<br>- በፍትህ ስርአቱ መስፈን አጋዥ አለመሆን | - ለህብረተሰቡ የፍትህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ለፈፃሚዎች ማከናወን፤<br>- የፍትህ ተደራሽነትን በመጨመር ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ ተገቢ ውሳኔ ማሰጠት፤<br>- ለፍትህ ስርአቱ አጋዥ እና ተገዥ ዜጋ እንዲፈጠር የራሱን ጥረት ማድረግ<br>- በምክንያት የሚደግፍና በምክንያት የሚቃወም ህብረተሰብ እንዲኖር የራሱን ደርሻ መወጣት |
| 10 | ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህፃናት፣ የአካልጉዳተኛ፣ የአረጋዊያንና ለኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች | - ፍትሐብሔራዊ መብትና ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩላቸው እና ከወንጀል ጥቃት እንዲጠበቁ እና ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸዉ እንዲከበሩላቸዉ ይፈልጋሉ፤<br>- በሕገመንግስቱ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በአግባቡ እንዲከበሩ፣ እንዲፈፀሙላቸው እና በዝርዝር ሕግጋት እና ዕቅዶች እንዲካተቱ<br>- ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ሆነ በሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ልዩ ትኩረት እንዲሰጥላቸው<br>- ልዩ ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ | - ለጉዳት ተጋላጭ በመሆን ፍትሐብሔራዊ ጥቅሞቻቸው አይከበሩም፤<br>- የሰብዓዊ መብት መጣስን ያስከትላል፤<br>- የፍትህ መጓደልና በተቋሙ ላይ እምነት ማጣት | - ለጉዳት በተጋለጡ ህብረተሰቦች ላይ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አጠባበቅ በተመለከተ ትምህርት መስጠት፤<br>- ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤<br>- ወንጀል እንዳይፈፀምባቸው መከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝ ለፍርድ ማቅረብ፣<br>- የአካቶ ትግበራ መፈፀም፤ |
| 11 | የጠበቆች ማህበር እና ልዩ ፍቃድ | - ቀልጣፋ አገልግሎት እና ድጋፍ | - ጠበቆች በፍትህ አስተዳደሩ | - ጥራት ያለዉና የተፋጠነ አገልግሎት |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል/ተገልጋይ | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| | የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ድርጅቶች | እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፤<br>- ቀልጣፋ፣ ተደራሽ፣ ጥራት፣ ነፃና ተጠያቂነት ያለው እንዲሁም ወጪ ቆጣቢ የፍትህ አገልግሎት እንዲኖር<br>- ተከታታይ የሕግ ስልጠና እንዲሰጥ<br>- በፍትህ ስርዓቱና በጠበቆች አስተዳደርና ክትትል መሳተፍ<br>- የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ ተገማች፣ ፈጣንና ጥራት ያለው እንዲሆን<br>- የባለሞያ የሙያ ክፍተት እና ስነምግባር ብቃት ለማዳበር ተከታታይ የሕግ ስልጠና እንዲሰጥ<br>- የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም መመርያ እንዲወጣ<br>- በጠበቆች አስተዳደርና ክትትል ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ | የሚኖራቸውን ሚና በአግባቡ እንዳይወጡ ያደርጋል፤<br>- በህዝብና በመንግሥት መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት ያስከትላል፤<br>- በፍትህ ስርዓትና በተቋሙ ላይ እምነት ማጣት<br>- የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ደካማ እንዲሆን ያደርጋል | መስጠት፤<br>- የሙያ ብቃታቸውን እንዲያጐለብቱ ድጋፍ ማድረግ፤ |
| 12 | የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች | - የህግ ምክር፣ ክትትል እና ድጋፍ፣ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በቀረቡባቸው ጉዳዮች ላይ ጉዳያቸው በፍ/ቤትና በአማራጭ እንዲፈታ ይፈልጋሉ፤<br>- የመንግሥት ፖሊሲዎችን፣ሕጎችንና የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ ጥራትና ብቃት ያለው አገልግሎት በቅልጥፍና ማግኘት<br>- የሕግ ምክር አገልግሎት በተቀላጠፈ መልኩ እንዲሰጣቸው<br>- በተቀላጠፈና ፈጣን በሆነ መልኩ የሕግ ረቂቅ እንዲዘጋጅ እና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ የሆኑ ሕጎች እንዲሻሻሉ | - የመንግስት ሃብት ይባክናል፤<br>- መስሪያ ቤቶቹ በተቋሙ ላይ እምነት ማጣት፤<br>- መንግስት ያቀዳቸው የመሰረተ ልማት ስራዎች በወቀቱ ስራ አይጀምሩም፤<br>- ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት መፍጠር፣ | - ወቅቱን የጠበቀ ክትትል እና ድጋፍ፤<br>- በፍርድ ቤት ጉዳዮቻቸውን በመያዝ ውጤታማ ማድረግ፤ |
| 13 | የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲቲዩት | - ስራቸውን ለማከናወን ከመስሪያ ቤቱ ቀልጣፋ የሆነ ጥራት ያለው አገልግሎትና የሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ይፈልጋሉ፤<br>- ለጥናት እና ምርምር የሚያግዙ መነሻ ርዕሶችን ይፈልጋሉ፤<br>- በተግባር ስልጠና ጊዜ ትክክለኛ ቦታ ላይ ተመድበው ውጤታቸው እንዲሞላ ይፈልጋሉ፤<br>- ተገቢ የሰልጣኞች ምልመላ እንዲካሔድ ይፈልጋሉ፤<br>- ከተጠሪነታቸው አንፃር ልዩ ድጋፍና ክትትል ይፈልጋሉ። | - በአቃቤ ህጎች እና በዳኞች ዙሪያ በሚፈጠረው የእውቀት ክፍተት በፍትህ አሰጣጥ እና በሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣሉ፤<br>- የህግ ክፍተትን ማሟላት አለመቻል፤ በስነ-ምግባር የታነጹ ዓቃቤያነ ህግ አለመፍጠር፤<br>- መስፈርቱን የሚያሟሉ ዓቃቤ ህጎችን ያለመመልመል እና ብቃት ያለው ተቋም አለመሆን፤ | - ለዳኞች እና ለአቃቤ-ህጎች የሚሰጡ የስራ ላይ እና የቅድመ-ስራ ላይ ስልጠና ጥራት ያለዉ እንዲሆንና ብቃት ያለዉ ምርምር ለማካሄድ እንዲችሉ የሙያ እና የቴክኒክ ብቃታቸው እንዲጐለብት ድጋፍ ማድረግ፣ |
| 14 | መገናኛ ብዙኃንና የመንግስት | - ስለመ/ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ወቅታዊ | - ስለመ/ቤቱ እንቅስቃሴ ህብረተሰቡ | - መ/ቤቱ ስለእንቅስቃሴውና |

| ተ.ቁ | ባለድርሻ አካል/ተገልጋይ | ፍላጐት ወይም የሚጠበቀው ውጤት | የሚጠበቀው/የሚፈለገው ጉዳይ ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ችግር | መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ |
|---|---|---|---|---|
| | ኮሚኒኬሽን ቢሮ | የሆነ ግልጽና ብቁ መረጃ ይፈልጋሉ፤<br>- የመረጃ ነጻነት እንዲከበር፣ ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር<br>- ተከታታይ የምክክር መድረክ እንዲኖር | ወቅቱን የጠበቀ እና ታማኝ መረጃ አይኖረውም፤<br>- የተቋም ገጽታ መበላሸት፣<br>- የመረጃ ነፃነት አለመከበርና ህዝቡ በተቋሙ ላይ አመኔታ ማጣት | ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በቂ መረጃ መስጠት፤ |
| 15 | የክልሉ ገንዘብ ቢሮ | - የበጀት ጥያቄ በወቅቱ እንዲቀርብለት ይፈልጋል፣<br>- ለመ/ቤቱ የተመደበው በጀት በቁጠባ ለታቀደለት አላማ በወቅቱ አገልግሎት ላይ እንዲውል ይፈልጋል፤<br>- ወቅታዊና ተአማኒ የሆነ ሪፖርት እንዲቀርብ፣<br>- የተቀናጀ የፋይናንስና መረጃ ስርዓት በተሟላ እንዲተገበር<br>- የተጠናከረ ዉስጥ ኦዲት እንዲኖር | - የገንዘብ ብክነት ያስከትላል፤ ውጤታማነት ላይ ችግር ይፈጥራል፤<br>- በጀት በበቂው መንገድ አለመመደብ<br>- እምነት ማጣት | - የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን ለመሙላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት፤<br>- መስሪያ ቤቱ የሂሳብ እና የበጀተ ሪፖርቶችን በወቅቱ እና በጥራት ማቅረብ፤ |
| 16 | የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | - የክልልና የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አስተዳደር ህጎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ፣<br>- በተቋሙ ዉስጥ የሰራተኞች ስነ ምግባር መከታተያ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ፣ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት እንዲዘረጋ፣<br>- የለውጥ ስራዎች በአግባቡ እንዲተገበሩ<br>- የተቋሙ የሰዉ ሀብት አመራር መረጃ በዘመናዊ ዘዴ የተደገፈ እንዲሆን ይይፈለጋል | - የፍትህ አገልግሎት አሰጣጥ ደካማ እንዲሆን ያደርጋል | - የፍትህ ስርአቱ አጋዥ እንዲሆኑ አልሞ መስራት |
| 17 | ፕላንና ልማት ቢሮ | - ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው የተቋሙን እቅድና ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት ይፈልጋል፤ | - ተቋሙ ያለእቅድ ይመራል፡፡<br>- የክልሉ መንግስት በመስሪያ ቤቱ የተከናወኑ ተግባራት ላይ እውቅና አይኖረውም፤ | - ወቅቱን የጠበቀ ጥራት ያለው እቅድና ሪፖርት የሚዘጋጁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣<br>- ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲደርስ ማድረግ፤ |
| 18 | ሲቪክ ማህበራት | - የወከሏቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅም እንዲከበር፣<br>- ለአባላቶቻቸዉ የንቃተ ህግ ስልጠና እንዲሰጥ<br>- በተቋሙ የህግ አወጣጥ፣ እቅድና አፈፃፀም በባለቤትነት እንዲሳተፉ | - በተቋሙ ላይ አመኔታ ማጣት | - ህግን መሰረት አድርገው በሚያቀርቡት ጥያቄ ላይ ተገቢ መልስ መስጠት<br>- የፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆኑ ማበረታታት |

### 4.6.3. የአጋር አካላት ትንተና

## ሰንጠረዥ3፡ - የአጋር አካላት ትንተና

| ተ/ቁ | አጋር አካላት | የትብብርመስኮች | አንፃራዊጠቀሜታው |
|---|---|---|---|

| ተ/ቁ | አጋር አካላት | የትብብርመስኮች | አንፃራዊጠቀሜታው |
|---|---|---|---|
| 1 | የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ | - የተለያዩ የኩነት ማስረጃዎችን ሲጠየቅ በወቅቱ ማቅረብ፤<br>- በሃሰተኛ የወሳኝ ኩነት ሰነዶች የሚፈጸሙ ኩነቶችን መከላከልና ተፈጽመው ሲገኙ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ | - አስፈላጊ እና ትክክለኛ የሆኑ ማስረጃዎችን ለማግኘት ያግዛል፤ |
| 2 | የመንግስትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | - በትምህርትና በስልጠና፣ በህግና በሰብዓዊ መብት ምርምር፣ በሰው ኃይል ልማት ጉዳዮች ዙርያ እና በነፃ የህግ ድጋፍ በትብብር መስራት፤ | - የክልሉን የፍትህ ስርዓት እና የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ያሣድጋል፤ |
| 3 | በህግና በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተባባሪ ድርጅቶች | - የህግና የሰብዓዊ መብቶችን ትምህርትን ለህብረተሰቡ በማስተማር እና ጥናት እና ምርምሮች እንዲካሔዱ በማድረግ ረገድ አብሮ መስራት፤ | - አብሮ በመስራት የሰብዓዊ መብት ግንዛቤ እንዲስፋፋ በማድረግ እና ሰብዓዊ መብት እንዲከበር እና እንዲሟላ ማድረግ፤ |
| 4 | የአጐራባች ክልሎች ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤቶች | - በድንበር አካባቢ በሚፈጠሩ ወንጀሎች እና በሌሎች ተመሳሳይ የጋራ ጉዳዮችላይ በትብብር መስራት፤ | - ለፍርድ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ንብረቶች እንዳይሸሹ ያደርጋል፤<br>- የወንጀል ድርጊት ፈጻሚዎች ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል አይደበቁም፤<br>- የጋራ እድገት ይፈጠራል፣ የጠነከረ ፍትህ ስርዓት ይኖራል፤<br>- አስተማማኝ የመረጃና የማስረጃ ልዉዉጥ ይኖራል፤<br>- ውሳኔዎችን የመፈጸምና የማስፈጸም ብቃት ይኖራል፤ |

## 4.7. የጥንካሬና የድክመት ማሳያዎች፣ የመልካም አጋጣሚና የስጋት መገለጫዎች ሰንጠረዥ፣

### 4.7.1. የጥንካሬና የድክመት መገለጫዎች

ሰንጠረዥ4፡- የጥንካሬ እና የድክመት መገለጫዎች

| ተ.ቁ | ዋናጉዳዮች | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | አደረጃጀትና አሠራር | • የክልል የአስፈፃሚ አካላት አዋጅ 280/2014 መዘጋጀቱና በክልል ምክር ቤት መጽደቁ፤ አዋጁን መሰረት ያደረገ የቢሮውን የአሰራርና አደረጃጀት ማንዋል መዘጋጀቱና ጸድቆ ወደ ትግበራ መገባቱ፤<br>• የ10 አመቱን እቅድ መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ መዘጋጀቱና አፈጻጸሙ መገምገሙ፤<br>• የማስፈፀም አቅም እየተሻሻለ መምጣቱ፤<br>• ስራን ማዕከል ያደረገ ግልጽ የሆነ ተቋማዊ አደረጃጀት መዘርጋቱ፤<br>• ስራን በእቅድ የመስራት፣ ሪፖርት የማድረግ፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖሩ፤<br>• የተለያዩ የአሰራር ማንዋሎች እና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለፈጻሚው የደረሱ መሆኑ፤<br>• የለውጥ ቡድን አደራጅቶ ስራዎችን ለመስራት ጅመሮች መኖራቸው፤<br>• ህዝቡን በፍትህ ስርዓቱ ማሳተፍ መጀመሩ፤<br>• የዜጎች ቻርተር እና የመልካም አስተዳደር እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መገባቱ፤<br>• ለውጡን ለመምራት የተደራጀ አካል መኖሩ፣<br>• በስራ ባሕርያት ላይ ተመስርተው የተደራጁ ዳይሬክቶሬቶችና የስራ ክፍሎች መኖራቸው፤<br>• ከባለድርሻ እና ከአጋር አካላት ጋር ተባብሮ የመስራት ባህል ጅምር መኖሩ፤<br>• ፍትህ ቢሮ በአዲስ መልክ ሲደራጅ በተለያዩ ተቋማት የነበሩ የምርመራ እና ክርክር መዛግብትን በመረከብ በተገቢው መልኩ ወደ ስራመገባቱ፣<br>• ለሴቶች፣ ህጻናትና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብት ለማስጠበቅ በእቅድ አካቶ ለመስራት ጥረት እየተደረገ መሆኑ<br>• የዐቃቢ ህግ ገለልተኝነት ለማረጋገጥ ዐቃቢ | • ከስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ይልቅ በደራሽ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፤<br>• የክትትልና ግምገማ አሠራር በመመሪያ የተደገፈ አለመሆን እንዲሁም በቂ፣ በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ አለመሆን፤<br>• በክልል፣ በዞን እና በወረዳ በተዋቀሩት አደረጃጀቶች በበቂ የሰዉ ኃይል አለማሟላት፤<br>• ወጥ እና ግልጽ የሆነ የምዘና ስርዓት አለመኖር፤<br>• ደካማ የሆነ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥ እና አጠቃቀም፤<br>• የለውጥ መሳሪያዎችን እና የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን በአግባቡ አለመተግበር፤<br>• ለዓቃቤያነ-ሕግ እና ለአስተዳደር ሠራተኞች የማትጊያ ስርዓት አለመኖር፤<br>• ወቅቱን የጠበቀና ወጥነት ያለው የደመወዝና የጥቅማጥቅም ክፍያ ስርዓት አለመኖር፤<br>• የዐቃብነ-ህግ የትምህርት እና የስራ ልምድ ልዩነት ሁኔታ ከግምት ዉስጥ ያላስገባ ደረጃ እና አሰራር መኖር፤<br>• ወቅቱ የሚጠይቃቸው የተለያዩ ቅንጅታዊ አሰራሮች የተፈለገውን ያህል የተጠናከሩ አለመሆናቸው፣<br>• የፖሉስ እና የዐቃቤሕግ የጋራ የወንጀል ምርመራ አሰራር ግንዛቤ ይዞ ውጤታማ ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩ፣<br>• ቅንጅታዊ አሰራር ከጊዜ ጊዜ እየተዳከመ መምጣቱ፣<br>• የተጠያቂነት አሰራር ላይ ክፍተት መኖር<br>• የህዝብን ፍታብሔራዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር በተለይ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ያለ የፍትሀብሔር ጉዳዮች አያያዝ ላይ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖረው ግፊት አለማድረግ፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ህግ ከማንናውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ነጻ እንዲሆን በህግ የተወሰነ መሆኑ<br>• የሙያ ስነ ምግባር ደንብና ሌሎች የአሰራር ስርአቶች እየተዘጋጀ መሆኑ፤ | |
| 2 | የሰው ኃይል | • የሰው ኃይሉን ለማብቃት ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤<br>• የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ያለው ሰራተኛ እየጨመረ መምጣቱ፣<br>• ስራው የሚያስፈልገውን ዓቃቤ ህግ እና የአስተዳደር ሠራተኛውን ቁጥር ለማሟላት ጥረት መደረጉ፤ | • ከፍተኛ የሆነ የሰዉ ኃይል ፍልሰት መኖሩ፤<br>• በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የዓቃቤ ሕጉችና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዲሟላ አለመደረጉ፤<br>• የዓቃቤያነ ህግ እና የአስተዳደር ሰራተኛ በተፈለገው መጠን የአቅም ግንባታ ስራ አለመኖር፤<br>• በበቂ ሁኔታ የሚፈጸም የደሞዝና ጥቅማጥቅም ክፍያ አለመኖር፤<br>• በቂ የሆነ እና ጥራት ያለው የሰው ኃይል የመረጃ አያያዝ ስርዓት አለመኖሩ፤<br>• ግንባር ቀደም የለውጥ ኃይል በሚፈለገው ቁጥር አለመድረስ፤<br>• በአንዳንድ ባለሙያዎችና ሰራተኞች የሚታዩ የስነ-ምግባር ችግሮች መኖራቸው፤<br>• የክህሎትና የስራ ልምድ ክፍተት መኖሩ፤<br>• የአስተዳደር ሰራተኞች ምደባ የስራ ክፍሎችን ተጨባጭ ሁኔታና የስራ ፍሰትን ታሳቢ ያደረገ አለመሆኑ፤ |
| 3 | የአገልግሎት አሰጣጥ | • የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፤<br>• የአገልጋይነት ስሜት እየዳበረ መምጣቱ፤<br>• የአገልግሎት አሰጣጥን ለመለካት የሚረዱ አንድ አንድ አሰራሮች መኖራቸው፤<br>• የአገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽነት ለማድረግ ቋሚ ምድቦችን፣ንኡስ ወረዳዎችንና ተዘዋዋሪ ችሎት በመክፈት ለተገልጋዩ አገልግሎቱን መስጠት መቻሉ፤<br>• አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አስተያየት የመቀበል | • የአገልግሎት አሰጣጥ በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረሱ፤<br>• የሚነሱ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን አሰባስቦ በመተንተን ማስተካከያዎችንና ተሞክሮዎችን አለመቀመር፤<br>• አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፤ ባለውም ቴክኖሎጂ አለመጠቀም፤<br>• ለዞኖች እና ለወረዳዎች በቂ ድጋፍና ክትትል አለማድረግ፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ጅምርመኖሩ፤<br>• መ/ቤቱ ለፍትሕ ሴክተሩ የተቀናጀ አሰራር እንደድልድይ ሆኖ ለማገልገል ጅምር መኖሩ፤<br>• የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ላይ የተጠያቂነት ስርዓትን ለማጠናከር ጥረት መደረጉ፤<br>• የዜጎች ቻርተር መዘጋጀቱና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ባለጉዳይ እንዲስተናገድ መደረጉ፤<br>• በተለያዩ ምክንያት ታስረው ለሚገኙ ታራሚዎች በይቅርታ አዋጁ መሰረት ይቅርታ መሰጠቱ፤ | • ለአገልግሎት አሰጣጥ የሚሆኑ የተሽከርካሪና ሌሎች ግባዓቶች ከፍተኛ እጥረት መኖሩ፤<br>• ተገልጋዮችን ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታ አለመኖር፤<br>• የደንበኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በእቅዱ መሰረት አለመፈጸሙ፤<br>• ወደ ህብረተሰቡ የተቀላቀሉ ታራሚዎች ያመጡትን ለውጥና ከህብረተሰቡ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በዳሰሳ ጥናት አለመለየት፤<br>• በተቋሙ የሚከናወኑ ስራዎችን ለህዝብ ከማድረስ ረገድ በቂ የሆነ የህዝብ ግንኙነት ስራ አለመሰራቱ፤<br>• ተከሳሽና ምስክር ባለመቅረባቸው የሚቋረጡ መዛግብት ከጊዜ ወደ ጊዜ መበራከት፤ |
| 4 | የአመራር ብቃት | • ለውጡን ማራመድ/መምራት/ የሚችል የእርስ በእርስ መግባባት ያለው ዓቃቤ ሕግና ሠራተኛውን በተለያዩ ተግባራት ለማሳተፍ ጥረት መደረጉ፤<br>• ከሌሎች የፍትሕ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት ጥረት መደረጉ፤<br>• ሀገራዊና ክልላዊ ፋይዳ ባላቸዉ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመስራት ጥረት መደረጉ፤ | • አልፎ አልፎ ከነባሩ አሠራር ያለመላቀቅ፤<br>• የውስጥ አቅምን አሟጦ አለመጠቀም፤<br>• የተቀናጀ አመራር ስርዓትና ጠንካራ የቡድን ስራ በሚፈለገው ደረጃ ያለመኖር፤<br>• ተተኪ አመራርን በየደረጃው ማብቃት አለመቻል፤<br>• የሴት አመራሮች ተሳትፎ አናሳ መሆን፤<br>• ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ አለማሟላት፤<br>• አመራሩ በደራሽ ስራዎች በመጠመዱ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ያለመስራት፤ |
| 5 | የፋይናንስ አሰራር | • የመንግሥት ደንብና መመሪያን በተከተለ መልኩ የበጀት አጠቃቀም መኖሩ፤<br>• ከመንግስት ከሚመደብ በጀት በተጨማሪ የሌሎች አጋር አካላትን የበጀት ድጋፍ ማግኘትና መጠቀም መጀመሩ፤<br>• የተቀናጀ የበጀት መረጃ ስርአት መዘርጋቱ፤ | • ከመንግሥት በጀት ውጭ በቂ ሀብት የማፈላለግ ውስንነት መኖሩ፤<br>• የግዥ አፈጻጸም ሒደቱ ረጅም ጊዜ የሚወስድና የቅልጥፍና ችግር ያለበት መሆኑ፤<br>• የተፈቀደ በጀትን በአግባቡ አሟጦ አለመጠቀም፤<br>• የቴክኖሎጂ /IBEX and payroll/ አጠቃቀም አቅም አናሳ መሆን፤ |
| 6 | ተቋማዊ ባሕል | • ስራዎችን እንደየ ስራ ባሕሪያቸው በየዳይሬክቶሬቶችና በየስራ ክፍሎች መመደቡ፤ | • በፈጻሚዎች ዘንድ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ በአግባቡ አለመስረጽ፤<br>• የመረጃ አያያዝ ባህል አለመዳበር፤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • በቡድን መስራትና ልምድ ማካፈል፤<br>• የፍትሕ ተደራሽነትን ለማጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፤<br>• የተቋሙን አመራርና ሰራተኛ የእርስ በዕርስ ግንኙነት ለማጠናከር ጥረት መደረጉ፤<br>• መንግስት የሚያወጣቸውን አዳዲስ ለዉጦችን እና አሰራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ መጣር፤<br>• ከሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት ልምዶችን ለመቅሰም መጣር፤<br>• ብልሹ አሰራርን እና ሙሰናን መታገል መጀመሩ፤<br>• የሃይማኖት አክራሪነትንና አሸባሪነትን በጽኑ መታገል፤<br>• የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤<br>• በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ተቀናጅቶ ለመስራት የሚያስችል ጥረት መኖሩ፤<br>• ህገ-ወጥ የመሬት ወረራን ለመከላከል በቅንጅት ለመስራት ጥረት መደረጉ፤ | • ስራን መሠረት ያደረገ የግምገማ ባህል አለመዳበር፤<br>• ማኅበራዊ ግንኙነትን በሚፈለገው መልኩ አጠናክሮ አለማስቀጠል፤<br>• ስራዎችን ከተቋሙ ዕሴቶች ጋር አስተሳስሮ የመስራት ባህል አለመዳበር፤<br>• የዐቃብያነ ህግ እና የድጋፍ ሰጪዉን የአሰራር ግንኙነት አድማስ ልዩነትን በአግባቡ አለመለየት፤<br>• በተለያዩ ቅንጅታዊ አሰራሮች ላይ የጋራ የሆነ ግንዛቤ አለመኖር፤<br>• ተቋሙ ነባር ባለሙያዎችን ለማቆየት የሚያስችል ስራ አለመስራቱ፤ |
| 7 | አቅርቦት (ግብዓት) | • ባለው አቅም ግብዓቶችን ለማሟላት መሞከሩ፤<br>• የንበረት መረጃ አያያዝ እና ምዝገባ ሁኔታ የተጀመረ መሆኑ፤ | • የሚገዙ ንብረቶች የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ፤<br>• ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት የግዥ ስርዓቱ ችግር ያለበት መሆኑ፤<br>• የቢሮ ጥበት መኖሩ፤<br>• የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መገልገያ መሳሪያዎች ለፈጻሚዎች በተሟላ መልኩ አለመዳረስ፤<br>• ያሉ ውስን ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም አቅም ውስንነት፤<br>• በመሠረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናት መሠረት አስፈላጊው አቅርቦት አለመኖራቸው፤<br>• ያለውን አቅርቦት በአግባቡ የመጠቀም ችግር፤<br>• የግብዓት መረጃ አያያዝ እና ምዝገባ ሁኔታ የተጠናከረ አለመሆኑ፤<br>• የተገዙ ንብረቶች ለተገዛላቸው የስራ ክፍሎች አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ጅማሮ ቢኖርም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው አለመሆን፤<br>• አዲስ የተገዙ ዕቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ በሚቆሙበት ወቅት አማራጮችን አሟጦ ሳይጠቀሙ ወደ ንብረት ክፍል ማስቀመጥ፤<br>• ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በወቅቱ የሚሟሉ አለመሆናቸው፤<br>• የተሸከርካሪ እጥረትና የስምሪት አስተዳደር ችግር አለመፈታቱ፤<br>• ድረ-ገጽ በማልማት ውጤታማ አለመደረጉ፤<br>• የመረጃ ዳታ ቤዝ ስርአት አለመዘርጋቱ፤ |

### 4.7.2. የመልካም አጋጣሚና የስጋት መግለጫዎች

ሰንጠረዥ5፡ - የመልካም አጋጣሚ እና የስጋት መገለጫዎች

| ተ/ቁ | ዋናዋናሁኔታዎች | መልካምአጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|---|
| 1 | ፖለቲካዊና ህጋዊሁኔታዎች | • ለህግ የበላይነትና ለዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር ያረጋገጠ ህገ-መንግሥት መኖሩ፤<br>• የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ፖሊሲ መዉጣቱ፤<br>• የብሔራዊ ሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ-ግብር ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፤<br>• የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የፖሊቲካና የህግ ሥነ-ምህዳር እንዲሁም አመራር መኖሩ፤<br>• የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት፣ ተጠሪነት በግልጽ የሚያሳይና ሊያሰራ የሚችል የህግ ማዕቀፍ መኖሩ፤<br>• ከፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤት ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ የምክክር መድረኮች በማድረግ ጅምር መኖሩ፤<br>• የፍትህ ስርዓት ማሻሻያና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞች ለተቋሙ መልካም አስተደደርና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ጠቃሚ መሆናቸው፤ | • በአጎራባች ክልሎችና በክልሉ ውስጥ የሚፈጠሩ ብሔርንና ሃይማኖትን ምክንያት ያደረጉ ግጭቶች መከሰት፤<br>• በፍትህና በሚመለከታቸው አካላት መካከል ወንጀልን በመከላከል ረገድ ያለዉ ቅንጅታዊ አሰራር የተፈለገዉን ያህል ያለመጠናከር፤<br>• የወንጀል ፖሊሲውን መውጣት ተከትሎ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ-ስርዓት ወይም ሌሎች ሊሻሻሉና ሊወጡ የሚገባቸው ህጎች አለመውጣት፤<br>• እየተገነባ ያለውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሽፋን በመጠቀም፣ሀሣብን የመግለጽ፣መብታቸውን ያላግባብ በመጠቀም የክልሉን ህዝብ ሰላምና ድህነትን የሚያበጣብጡ ግለሰቦች እና ቡድኖች መኖር፤<br>• የህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር መበራከት፤<br>• ሀገራዊም ሆነ ክልላዊ አለመረጋጋቶች፤<br>• ከአጐራባች ክልሎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር የተለያዩ የምክክር መድረኮች አለመጠናከር፤ |

| ተ/ቁ | ዋናዋናሁኔታዎች | መልካምአጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|---|
| 2 | ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች | • የኢንቨስትመንት በክልሉ ውስጥ መስፋፋት ስራ አጥነትን ስለሚቀንስ የወንጀል ድርጊት ፈጻሚዉ የህብረተሰብ ክፍል እንደሚቀንስ መታመኑ፤<br>• የክልሉ ገቢ በመጨመሩ ለመ/ቤቱ የሚመደብ በጀት እየጨመረ መምጣቱ፤ | • በኢኮኖሚዉ ዘርፍ የሚታየዉ ፈጣን እድገት የማይቀጥል ከሆነ በድህነት ዉስጥ ያለዉ የህብረተሰብ ክፍል የወንጀል ድርጊት ምንጭ መሆኑ ይቀጥላል፤<br>• ከኢኮኖሚ ጋር ተያይዞ የገበያ አለመረጋጋት መኖር እና በኢኮኖሚ ግንኙነት ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ መኖርና በወንጀል መከላከል ረገድ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩ፤<br>• የዋጋ ግሽበት መኖሩና ቁጠባን መሰረት ያደረገ የበጀት አጠቃቀም አለመኖር፤ |
| 3 | ማህበራዊ ሁኔታ | • የክልሉ ማህበረሰብ ህገ-ወጥ ድርጊትን የመጸየፍ የዳበረ ባህል ያለዉ በመሆኑ በህግ የበላይነት የሚያምንና አጥፊዎች ተገቢውን ፍርድ ማግኘት አለባቸው የሚል ግንዛቤ መኖሩ፤<br>• ህ/ሰቡ ራሱን ለመከላከል ያለው ተነሳሽነት እየጨመረ መሄዱ፤<br>• ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ደረጃ በደረጃ እየቀነሱ መምጣታቸው፤<br>• የእምነትና የሃይማኖት ነፃነት በህገ-መንግሥት በመረጋገጡ ህዝቦች ተከባብረውና ተቻችለው መኖራቸው፤<br>• ህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን በህግ አግባብ የመጨረስ ዝንባሌዉ እየጨመረ በመምጣቱ ፍትሃብሄራዊ ጥቅሞቹን እያስጠበቀ ከመሆኑም በላይ ሊያስከትል የሚችለውን የወንጀል ስጋት እንዲቀንስ ማድረጉ፤<br>• ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች መኖራቸው፤ | • ከህ/ሰቡ ሁለንተናዊ እድገት ጋር እየተከሰቱ የሚመጡ ወንጀሎች ረቂቅና ዉስብስብ መሆን፤<br>• ጸረ-ሰላም ግለሰቦች እና ቡድኖች በብሔር እና በሃይማኖት ሽፋን ግጭት መፍጠራቸው፤<br>• ህብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ ከጐጅና ልማዳዊ ድርጊቶች አለመላቀቁ፤<br>• በወጣቱ አካባቢ ለመጤ ጎጂ ባህልና ለአጉል ሱስ መጋለጡ በወንጀል ስራ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያደርግ መሆኑ፤<br>• ደም መመለስና መበቃቀል አይነት ጎጂ ልማዶች መኖራቸው፣ በሐሰት ክስ ማቅረብና የሀሰተኛ ምስክር መበራከት ለፍትህ አስተዳደሩ ከፍተኛ ችግር መፍጠሩ፤<br>• ህገ-ወጥ የሰዎች ዝዉዉር እየጨመረ መምጣት፤<br>• በማኅበራዊ ድህረ ገጾች የሚለቀቁ የጥላቻ ጽሁፎች እና አሉባልታዎች መበራከት፤<br>• ስራ አጥነት መበራከት ለወንጀል መንስዔ በመሆኑ ህግና ስርዓት በማስከበር ሒደት ጫና መፍጠሩ፤ |
| 4 | ቴክኖሎጅያዊ | • በኮምፒዩተር መረጃዎች የማደራጀት፣ የመተንተንና የማኅልበት ጥረት እየተደረገ | • በህገ-ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ፊልሞችና በኢንተርኔት የሚተላለፉ |

| ተ/ቁ | ዋናዋናሁኔታዎች | መልካምአጋጣሚ | ስጋት |
|---|---|---|---|
| | | መሆኑ፤<br>• ከኢንተርኔት የአገር ውሰጥና የውጭ ተቋማትን አሰራርና አደረጀጀት ለማወቅ እድል መፈጠሩ፤<br>• ቴሌግራም፣ ፌስቡክ፣ ፋክስ፣ ሞባይል አገልግሎቶች ለፈጣን መረጃ ልውውጥ አገልግሎት ላይ መዋላቸዉ፤<br>• የወንጀል ምርመራ ስራዎችን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ ዘመናዊ መሣሪያዎች እያደጉ መምጣት፤ | መልዕክቶች ህብረተሰቡን ለወንጀል የሚያነሳሱና ለሀገር ሰላምና ደህንነት ስጋት መሆናቸው፣<br>• ሰዎች የወንጀል ስራዎችን በተራቀቁ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በመጠቀም ሊፈጽሙ እና ማንነታቸው ሳይጋለጥ ሊቀሩ የሚችሉ መሆናቸው፤(የኢንተርኔት መረብ ደህንነት ወንጀሎች) መበራከት፤<br>• የኢንተርኔት አገልግሎት መቆራረጥ፤<br>• የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና መላመድ ውስንነት፤<br>• የማኅበራዊ ሚዲያዎችን አጠቃቀም ችግር፤ |

## 4.8. ዓላማ፣ ግቦች እና ዝርዝር ተግባራት

የ2015 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ የመ/ቤቱን ተልዕኮ፣ የባለድርሻ አካላት ፍላጐት፣ የአጋር አካላት ትንተና እና የትኩረት አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ የ2016 በጀት ዓመት ዓላማ፣ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ዓላማ 1፡-ተልዕኮውን ማሳካት የሚችል ጠንካራና ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ ኃይል መገንባት፤**

ጠንካራና ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ ዕውን ለማድረግ የተለያዩ የአቅም ማሳደጊያ ስራዎችን በመስራት ጠንካራ ተቋም ለመፍጠር የሚያስችል አላማ ነው፡፡

**ግብ 1፡- የአመራሩን አቅም ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- እስከ ወረዳ ላለው አመራር የአመራር ክህሎት ስልጠና መስጠት 1 ጊዜ (95) (በተለያየ ዙር)
- 164 ለሚሆኑ የዋና ጉባኤና ንዑስ ጉባኤ አባላት የጉባኤ ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- የፖሊስ እና የዐቃብያነ -ሕጎችን የወንጀል ምርመራ አቅም ማሳደግ የወንጀል ምርመራ ይዘት፣ ሂደት እና ቴክኒኮች ላይ ለዐቃብያነ - ሕጎች ስልጠናዎች ማዘጋጀት

- ስትራቴጂያዊ አመራር ለመስጠት የሚያስችሉ (ለዕለታዊና የመደበኛ ስራዎች ውክልና የመስጠት አሰራርን ጨምሮ) ተስማሚ የአደረጃጀት እና የአሰራር ማሻሻያዎችን መቅረጽና መተግበር
- የተተኪ ሥራ መሪዎች መመልመያ መስፈርት መመሪያ ማውጣት፤ የመረጃ ቋት ማደራጀት እና ተተኪ አመራር ማፍራት
- ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት የሚያስችል ስርዐት መቅረፅና መተግበር
- ተተኪ ሥራ መሪዎች የማብቃት እና የምደባ ስርዐት መቅረፅና መተግበር
- የአመራር ክህሎትን በተግባር እንቅስቃሴ ለመማር የሚያስችሉ በየወቅቱ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ የመስክ ምልከታ፣ ልምድ ልውውጥ፣ ግምገማ ነክ ስልጠና ስራ 2 ጊዜ ማካሄድ፤
- የአመራር ጥበብ ስልጠና 2 ጊዜ መስጠት (ፍትህ ማሰልጠኛ ተቋም)

**ግብ-2 የፈፃሚውን ሁለንተናዊ አቅም ማሣደግ**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- ከቢሮ እስከ ወረዳ ለሚገኙ ዐቃብያነ-ህግ የህግ የበላይነት ንቅናቄ መድረክ 1 ጊዜ በ2 ዙር ማካሄድ፤
- ለ500 ዓ/ህግ የክህሎት ስልጠና መስጠት ከዚህ ውስጥ ለ161 ሴት ዐ/ህግ ስልጠና መስጠት፤
- የሙስና እና የብልሹ አሰራር ምንነት ይዘትና አደጋዎች በተመለከተለመ/ቤቱ ሰራተኞች 1 ጊዜ የግንዛቤ ማሣደጊያ ስልጠና መስጠት፤
- በወንጀል ጉዳዮች 1 ጊዜ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የመንግስትና ህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ መስራትና ስልጠና መስጠት፤
- ተከራክረን በተሸነፍንባቸው የፍትሐብሄር መዛግብትን የማጥናትስራ በመስራት በዓ/ህግ የሚታዩትን የእውቀትና የክህሎት ክፍተቶች 1 ጊዜ ስልጠና መስጠት፤
- በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ህግና መመሪያዎች ዙሪያ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት፤
- በኮምፒዩተርና ቴክኖሎጂ ወንጀሎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት
- በተፈጥሮ ሀብትና አካባቢ ህጎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት
- በሀገር ግንባታና ሀገራዊ ውይይት ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት
- በግዥና ኮንስትራክሽን ዙሪያ ስልጠና መስጠት
- በውል ረቂቅ ምርመራ ዙሪያ ስልጠና መስጠት

- በሰው መነገድና ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል አዋጅ 1178/2012 እና በሌሎች ተያያዥ ህጎች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
- በሰው መነገድና ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል የተገኘ ሀብት ለማስመለስ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፤
- ቀልጣፋ የግዥ ፋይ/ ንብረት አስ/ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት፤
- እስከ ወረዳ ላሉ የዕቅድ እና የመዛግብትና መረጃ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፣
- የኮፒዩተር ጥገና ስልጠና መስጠት፤
- ለዐቃቤ ህግ እና ለቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞች በአመት 1 ጊዜ ስልጠና መስጠት
- 1 የአጫጭር ጊዜ የማሰልጠኛ ሞጁል ማዘጋጀት (በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- ለ1,250 ለፍትህ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት (በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- የአሰልጣኞችንና ተመራማሪዎችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ በ4 አርዕስቶች ላይ ስልጠና መስጠት፤
- በ3ኛ ዲግሪ 1፣ በ2ኛ ዲግሪ 1፣ በመጀመሪያ ድግሪ 1 እና በዲፐሎማ 1 የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎችና የአስዳደር ሠራተኞች (በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- በአብክመ የህግ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲቲዩት ለ300 የቅድመ ስራ ላይ ስልጠና መስጠት (በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- በመስሪያ ቤቱ አማካኝነት በስራ ላይ ላሉ ዓ/ህግ የክህሎት ክፍተት በጥናት በመለየት የስልጠና ሰነዶችን በማዘጋጀት በበጀት አመቱ ውስጥ በጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መ/ቤት በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም 1 የአጫጭር ጊዜ የማሰልጠኛ ሞጁል ማዘጋጀት፤
- በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም የአሰልጣኞችንና ተመራማሪዎችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ በ4 አርዕስቶች ላይ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- በፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም የተሰጡ ስልጠናዎችን ጥራት ከ71% ወደ 74% ማሳደግ፤
- በተቋሙ ያለውን የሰው ኃይል ፍልሰት ለመቀነስ በተለይም ብቃት ያለውን ባለሙያ ለማቆየት የፈፃሚ ባለሙያውን ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም፣ የማበረታቻ ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በማጥናት እና አገራዊ ስታንዳርድ እንዲኖረው በማድረግ 1 ጊዜ በጋራ በማጥናት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ዐቃብያነ ህግን የሚመለከቱ የደረጃ እድገት፣ የትምህርትና ስልጠና፣ ዝውውር የሙያ ስነ-ምግባር ደንቦች ፍትሀዊነት፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፤

- ዐቃብያነ ህግንና የአስተዳደር ሰራተኞች የስራ አፈፃፀም መለኪያ አተገባበርን በማጠናከር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ማለትም ውጤቱን መሠረት በማድረግ 1 ጊዜ ማበረታታት፣ መሸለም፣ መደገፍ፣ ማብቃትና ማረም፤
- በየደረጃው ባለው የፍትህ መዋቅር የሰው ኃይል ፍላጐት በማጥናት፣ በሙያ ብቃት እና በቁጥር ከስራው ፍሰት ጋር የተጣጣመ ለማድረግ አሁን ካለን የሰው ሃይል በተጨማሪ በዓመቱ 150 ዐቃብያነ ህግና 100 የአስተዳደር ሰራተኛ የሰው ኃይል ማሟላት፤
- በተቋሙ ውስጥ ለሚገኙ ለሴቶች፣ ለወጣቶች እና ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩዓቃቤ ህጎችን፣ የአስተዳደር ሰራተኞችና አመራሮች ያሉባቸውን ችግር በመለየት የማጠናከሪያ ስልጠና 1 ጊዜ መስጠት፤
- የፍትህ ቢሮ አመራሮች እና ባለሙያዎችን ለማጥራት የሚያስችል የአሰራር ማንዋል ማዘጋጀት
- የማጥራት ተግባሩን የሚያከናውን አደረጃጀቶችን መፍጠር
- የማጥራት ሂደቱን ተግባራዊ ማድረግ እና ማጠናቀቅ
- የተውጣጣ የኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ አስተግባሪ እና አደረጃጀትን ማዋቀር እና ወደ ስራ ማስገባት
- የኢ.ኮ.ቴ አደረጃጀት እና ፈጻሚዎች የዋና የስራሂደት አካል እንዲሆን የሚያስችል አደረጃጀት እና አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ
- ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የወንጀል ጉዳዮች አያያዝ ምቹ የሆነ የአደረጃጀት ማስተካከያ ማድረግ እና ወደ ስራ መግባት፡-
- በቢሮው ረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሰራተኞች የማበረታቻ ሥርዓት መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ፣
- ለስራ የሚያስፈልጉ ህንጻ እና ፋሲሊቲ የሚሟላበት ጥናት በማድረግ መፈጸም
- የቢሮው ሰራተኞች የግል የቤት መስሪያ መሬት እና ፋይናንስ ምንጭ የሚያገኙበት የአሰራር ሥርዓትን መቅረጽ እና ወደ ስራ ማስገባት

**<u>ግብ3፡-</u> የለውጥ ኘሮግራሞች አጠቃቀም ውጤታማነት ማጠናከር**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በአመራሩም ሆነ ፈፃሚ ኃይሉ በሪፎርም ኘሮግራሞችና የለውጥ መሣሪያዎች ላይ 2 ጊዜ የተሟላ ግንዛቤ መፍጠር፤
- የለውጥ መሣሪያዎችን በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሠረት መተግበራቸውን 4 ጊዜ በክትትልና ድጋፍ ማረጋገጥ፤
- የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓቱ አተገባበርና ያመጣውን ውጤት 1 ጊዜ በማጥናት ማጠናከር፤

- አዳዲስና ዘመናዊ የለውጥ መሳሪያዎች አጠቃቀም አገር አቀፍና አለም አቅፍ መልካም ተሞክሮዎችን መለየት እና መተግበር
- ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ 1 ዕቅድና 4 የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት፤

## ግብ 4፡- የሰው ኃይል አቅርቦትና አያያዝን ማሻሻል

### የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- ለስራው አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሃይልና ግብዓቶችን ማሟላት፤
- በህጉ መሠረት አስፈላጊውን ጥቅማጥቅምና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ የፈፃሚውን የስራ ተነሳሽነት መጨመር፣ የፈፃሚውን መሰረታዊ ፍላጎቶችን በማሟላት እርካታውን በማሳደግ ፍልሰቱን በበጀት አመቱ አሁን ካለበት 5.14% ወደ 0.5% መቀነስ/ዝቅ ማድረግ/፤
- ከሰው ሃይል አያያዝና አቅርቦት ጋር ተያይዞ ችግር ፈች ጥናት 1 ጊዜ በማካሄድ መፍትሄ እንዲሰጥበት ከሚመለከታቸዉ ጋር መስራት፤
- የተጠየቀ ደረጃ ዕድገት፣ ዝውውርና ቅጥር መፈፀም፤
- አስፈላጊ የስራ መደቦችን ማስፈቀድ፤
- ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ
- የዐቃብያነ-ሕጎችን የሥራ መደብ እና የደረጃ እድገት ስርዐት እንደገና መከለስ እና ማሻሻል፤
- ጉዳይ አደላደልን የሚመለከት ግልጽ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ መተግበር
- ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የትምህርትና ሥልጠና ስርዓት መቅረጽ መተግበር
- የሰራተኞችን የሥራ አፈፃፀም ዉጤት መመዘኛ ስርዐት ማሻሻልና መተግበር፣
- በአቃብያነ ህግ የአስተዳደር ጉዳዮችን አስመልክቶ የአቃብያነ ህግ አስ/ ጉባኤ የአሰራር እና የአደረጃጀት ተግባራትን ማጠናከር፤

## ግብ 5፡- የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ውጤታማነትን ማሳደግ

- ውጤታማ የሀብት ማሰባሰቢያ ስርዓት መዘርጋትና መተግበር፤
- የበጀት ዝግጅት ጥራትን በማሳደግ ከመንግስት በቂ በጀት እንዲመደብ የሚያሥችል ሥራ መስራት፤
- ከልማት አጋሮች የበለጠ የቴክኒክ አና የፋይናንስ ድጋፍ የሚግኝበትን ስትራቴጂ አውጥቶ መተግበር
- የበጀት አጠቃቀም ዕድገት 100% በመቶኛ ማድረስ፤

- የግዥ ሥርዓትን ማዘመንና ማጠናከር፣
- ውጤታማ የኃብት አጠቃቀም ንብረት አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ መተግበር፤
- የኦዲት ግኝትን መቀነስ፤
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን መተግበር፤
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን መተግበር፤

**<u>ግብ 6፡-</u>ከክልል ጠቅላይ ዓ/ህግ መ/ቤቶች/ፍትህ ቢሮዎችና ከልማት ተባባሪ ድርጅቶች ጋር ያለውን ትብብር ማጠናከር**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- ከፌደራል እና ከክልል የፍትህ አካላት ጋር አጋርነትና ግንኙነት የሚያጠናክር ስርዓት ዘርግቶ መተግበር፤ ከ2 ክልል ፍትህ ቢሮ/ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መ/ቤት የጋራ መግባቢያ ሰነድ መፈራረምና ተግባራዊ ማድረግ፤
- ከልማት ተባባሪ ድርጅቶች ጋር የተጀመረውን ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከርና በየአመቱ እቅድና ሪፖርት እያዘጋጁ በመፈጸም 1ጊዜ የጋራ ግምገማ ማድረግ፤
- በፍትሕ ስርዐቱ ውስጥ ተሳታፊ እና አጋዥ ከሆኑ አካላት ጋር የአጋርነት ስትራቴጂ አውጥቶ መተግበር የመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት አጋርነትና ትብብር ማጠናከር (በተለይ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ውል አያያዝና አስተዳደር፣ የመንግስት ንብረት አስተዳደር፣ መረጃ አሰባሰብ እና ፍርድ አፈፃፀም በተመለከተ)፤
- ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት በመፍጠር የሚገኝን ድጋፍ ማሳደግ
- ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት በመፍጠር የሚገኝን ድጋፍ ማሳደግ
- የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል
- የደም ልገሳ መርሃ ግብር ማካሄድ
- 2 ወላጆቻቸውን ያጡ እና ችግረኛ ህፃናትን መደገፍ

**ዓላማ 2፡-መልካም አስተዳደርን በማስፈን ህ/ሰቡ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ያለውን አመኔታ ማሣደግ፤**

ቢሮው እስከ ወረዳ ድረስ ያለው አሰራር በህብረተሰቡ ዘንድ ዓመኔታ ያለው ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የሚሰሩ ተግባራትን፣ ብልሹ አሰራርን ለመታገል የሚያስችሉ አሰራሮችን በመንደፍ ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትን አሰራር በመዘርጋት አገልግሎት አሰጣጣችንን ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያስቸሉ ተግባራት የተካተቱበት ዓላማ ነው፡፡

**ግብ 1፡-ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ማሣደግ፣የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በየደረጃው ያለውን የፍትህ ስርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ፣ የፍትህና የፖሊስ የጋራ ኮሚቴ፣ የኦዲት ግኝቶች ስትሪንግ ኮሚቴ፣ የሰብዓዊ መብትየድርጊት መርሀ ግብርኮሚቴ፣ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ግብረ ኃይል እና ሌሎች የክላስተር አደረጃጀቶች ተልዕኳቸውን ማሣካት በሚችሉበት ደረጃ ላይ መሆናቸውን 4 ጊዜ ክትትል ማድረግ፤
- በፍትሐብሔር ጉዳዮች ውል አያያዝና አስተዳደር፣ የመንግስት ንብረት አስተዳደር፣ መረጃ አሰባሰብ እና ፍርድ አፈፃፀምን በተመለከተ ከመንግስት መ/ቤቶች ጋር 1 ጊዜ የጋራ ምክክር መድረክ መፍጠር፤
- ትብብር እና አጋርነትን ለማሳደግ ቢሮው የሚያስተባብራቸውን ወይም አባል የሆነባቸውን ከፍትሕ ስርዐት ጋር የተያያዙ ኮሚቴዎች / መድረኮች አጠናክሮ መቀጠል የፍትህ ስርዓት አስተባባሪ ኮሚቴ፣ የፍትህና የፖሊስ የጋራ ኮሚቴ፣ የኦዲት ግኝቶች ስትሪንግ ኮሚቴ፣ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ኮሚቴ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ግብረ ኃይል ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ፍትሕ ቢሮው ከአጋሮች ያገኘው የቴክኒክና ሌሎች የሃብት ድጋፎች ጨምረዋል፤
- የዓቃቤ ሕግ ነጻነትን ይበልጥ የሚያጎለብቱ የሕግ፣ የአደረጃጀት እና የአሰራር ማሻሻያዎች እንዲወሰዱ ማድረግ፤ የዓቃቤ ሕግ ነጻነት መርሕ እውቅና እና አፈጻጸም በሕግ ( በክልሉ ሕገ መንግስት ጨምሮ) የሚካተትበትን በተመለከተ ጥናት ማድረግ፣ የውሳኔ ሀሳብ ለሕግ አውጪው ማቅረብ እና ክትትል ማድረግ
- የወንጀል ክስ ሂደትን የሚከታተለውን ክፍል በፍትሕ ቢሮው ስር የተወሰነ ነጻነት ያለው ( semi autonomous) ዲፓርትመንት ሆኖ እንዲዋቀር የሕግና የአደረጃጀት ማሻሻያ ሀሳቦች አቅርቦ መከታተል
- የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው በክስ ሂደቶች ላይ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ጣልቃ የዓቃቤ ሕግ ነጻነትን እና ገለልተኝነትን የሚያረጋግጥ የሕግ እና የአሰራር ማዕቀፍ ተዘርግቶ ስራ ላይ ውሏል፣ የዓቃቤ ሕግ ነጻነት እና ገለልተኝነት የሚያረጋግጡ የሕግና የአሰራር ማሻሻያዎች ብዛት ዕድገት በመቶኛ የሚገቡባቸውን ሁኔታዎች/ መመዘኛዎች በተመለከተ ግልጽ መመሪያ ማውጣት
- በዓቃቤ ሕግ ነፃነት ላይ ለሚመለከታቸው አካላት በቂ ግንዛቤ መፍጠር
- የዓቃቤ ሕግ ነጻነት እና የሕግ የበላይነት መርሆዋች እና ይዘት ላይ ለአስፈጻሚና ለምክር ቤት አባላ ግንዛቤ ለማዳበር የሚያስችል ሰነድ ማዘጋጀትና ስልጠና መስጠት፤ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት
- በክልል የፍትህ ተቋማት መካከል የቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓትን በማዘጋጀት የጋራ አደረጃጀት እና ገዢ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ

- በክልል አቻ የፍትህ ተቋማት ቀደም ሲል በተዘጋጀው መግባቢያ ሰነድ መሰረት የጋራ ዕቅድ፣ ሪፖርት እና የግምገማ ሥርዓትን ወደ ስራ ማስገባት
- የፍትህ አካላት የጋራ ፎረም በማጠናከር፤ በፍትህ ዘርፉ በሚያዙ ግቦች፣ የአፈጻጸም አቅጣዎች እና አፈጻጸሞች ላይ የጋራ መግባባት የሚደረስበት ቋሚ መድረክ ማቋቋም
- ክልል አቀፍ የፍትህ አካላት አመታዊ የአፈጻጸም ትንታኔ እና መልካም ተሞክሮዎች እንዲሁም ጥናቶች የሚቀርቡበት መጽሔት ህትመት እና የሩብ አመት አንኳር አፈጻጸም መጽሔት ህትመት ሥርዓት መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ
- ቀደም ሲል ተደራጅተው የቆዩትን ቋሚ ምድቦችን ማጠናከር
- የክልል ፍትህ ተቋማትን በዞኖች፣ በወረዳዎች እና ንዑስ ወረዳዎች ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል የጋራ የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት

**ግብ 2፡-የሙስና እና የብልሹ አሰራር አመለካከትና ተግባራትን ለመታገል ግልፅነትና ተጠያቂነትንማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በክልላችንም ሆነ በፌዴራል የወጡ ህጎች በአግባቡ ስለመተግበራቸውና ከህገ መንግስቱ ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው 3 ተቋም ላይ ጥናት ማድረግ፤
- የህግና ፍትህ ኢንስፔክሽን /Legal Auditing/ ስራ 4 ጊዜ በማካሄድ በግኝቱ መሠረት ስህተቶችን ማረም፤
- እልባት ያገኙ የፍትሐብሄር መዛግብትን የክርክር/የውሳኔ አግባብነት እና ጥራት የሚገመገሙበት የመዝገብ ኦዲት ስርዓት መዘርጋት እና የኦዲት ውጤቶችን ለማስተማሪያና ለተጠያቂነት ማዋል፤
- እልባት ያገኙ የወንጀል መዛግብትን በተመለከተ የክርክር / የውሳኔ አግባብነት እና ጥራት የሚገመገም በት የመዝገብ ኦዲት ስርዓት መዘርጋትን እና የኦዲት ውጤቶችን ለማስተማሪያና ለተጠያቂነት ማዋል፤
- የቀረቡ የዐ/ህግ የዲሲፕሊን ጉዳዮችን 100% ውሳኔ መስጠት፤
- 4 ጊዜ የውስጥ ኦዲትና ስራ በማካሄድ በግኝቱ መሠረት ስህተቶችን ማረም፤
- በመ/ቤቱ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ጉባኤዎች ተጠናክረው በህግ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር እንዲወጡ 2 ጊዜ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

**ግብ 3፡- በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ የህብረተሰቡን የተደራጀ ተሣትፎና ባለቤትነት ማሣደግ፤**

**የሚከናወኑዝርዝር ተግባራት**

- በፍትህ አስተዳደሩ ቀጥታ ተፅዕኖ ያላቸው የህዝብ አደረጃጀቶች (ዐ/ህግ፣ ዳኞች፣ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሌሎች የሙያ ማህበራት) በእቅድ አወጣጥ እቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ላይ 2 ጊዜ ማሣተፍ፤
- የቢሮውን የሩብ ዓመትና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ማሳተም እና ተደራሽ ማድረግ፤
- የቢሮውን አመታዊ ሪፖርት መድረክ አዘጋጅቶ ለህዝቡ ይፋ ማድረግ፤
- ቋሚ የህብረተሰብ ተሳትፎ መድረኮችን ማቋቋም
- ቀጣይነት ያለው የፍትህ ንቅናቄ መድረክ ሥርዓት በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ
- የህብረተሰብ ተሳትፎን ማሳኪያ ዝርዝር የአሰራር ማንዋል ማዘጋጀት
- በየደረጃው ለሚገኙ መዋቅሮች እንደመነሻ የሚያገለግል የንቃተ ሕግ ማንዋል 1 ማዘጋጀት
- በሬዲዮና ቴሌቪዥን የንቃተ ሕግ ትምህርት መስጠት፤
- አጠቃላይ የሕብረተሰቡን በተለይ የሲቪል ማህበራትን በፍትሕ ስርዐቱ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ማበልጸግያ ፕሮግራም መንደፍና መተግበር፣
- በክልሉ በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ባለሥልጣናት፣ ተሿሚዎች፣ የህዝብ ተመራጮች፣ ሠራተኞች እና የተመረጡ የግሉ ዘርፍ ተዋናዮች ስለህግ የበላይነት እና የመልካም አስተዳደር እሴቶች ላይ በየጊዜው ግንዛቤ መፍጠር
- ህዝቡ መብቱንና ግዴታውን አውቆ ህግ በማክብርና ማስከበር ወንጀልን በመከላከል በኩል የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ካለው የክልሉ ህዝብ ውስጥ 24% (5,651,760) የሚሆነውን የክልሉን የህብረተሰብ ክፍል የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፤ ከእነዚህ ውስጥ ወጣቶች 1,247,867 ህፃናት 749,077 አረጋውያን 333,046 አካል ጉዳተኞች 400,000 ሌሎች 2,921,770
- በቢሮው የህብረተሰቡን አገልግሎት አሰጣት እርካታ ለመለካት የሚያስችል ወጥ እና ቀጣይነት ያለው የአሰራር ሥርዓት መቅረጽ እና መተግበር፡-
- ህብረተሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ተሳትፎ ሊያድርግባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን እና አጀንዳዎችን መለየት
- በፍትህ ተቋማት መካከል የተናበበ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አፈጻጸም መለኪያ ሥርዓትን መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ
- ክልል አቀፍ የንቃተ ህግ አሰጣጥ ማንዋል መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ፡-
- የህግ መሰረተ ትምህርት ሥርዓትን መቅረጽ/ ተግባራዊ ማድረግ
- የንቃተ ህግ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ሥርዓትን መቅረጽ /ተግባራዊ ማድረግ

- በሁሉም የህግ ት/ቤቶች የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ
- ለመሰረተ-ማህበረሰብ የፍትህ አገልግሎት ሰጪዎች ተከታታይ መሰረታዊ የህግ ስልጠና መስጠት
- የመሰረተ-ማህበረሰብ ፍትህ አገልግሎት አሰጣጥን የሚደግፍ እና የሚከታተል ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር እና ወደ ስራ ማስገባት
- የዐቃብያነ-ሕጎችን መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት ማረጋገጥ፤
- የዐቃብያነ-ሕግ መተዳደሪያ ደንብን ዐቃብያነ-ሕጎችን ግለሰባዊ ነጻነት፣ መብቶች እና ጥቅሞች በተሟላና በአግባቡ በሚያስከብር መልኩ ማሻሻል እና መተግበር፤
- የዐቃብያነ -ሕጎችን የስራ ላይ ጤንነት እና ደህንነት መጠበቂያ መመሪያ በጥናት ላይ ተመስርቶ ማውጣትና መተግበር፤
- የየዓቃቤ ሕግ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር
- ግልጽ አሰራርን እና የስነምግባር መርሆዎችን መሠረት ያደረገ የተጠያቂነት ስርዐት ማጠናከር
- የዓቃብያነ ሕጎች የስነምግባር ደንብን ማጽደቅ፤ አሳትሞ ለዓቃብያነ ሕጎች ማሰራጨት፣ ማስረጽ፤
- ተቋማዊ የፀረ - ሙስና ፖሊሲ ማውጣት እና መተግበር
- የዐቃብያነ - ሕግ አስተዳደር ጉባዔ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት እና አቅም ማጠናከር
- ቀልጣፋ እና ውጤታማ የቅሬታ፣ ጥቆማ እና አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት ማጠናከር፤
- በሁሉም የቢሮው አግለግሎት መስጫ ቦታዎች በኢኮቴ የታገዘ የተገልጋይ አስተያየት መቀበያ ስርዓት መዘርጋት፤
- በሁሉም የቢሮው አግለግሎት መስጫ ቦታዎች የተገልጋይ እርካታ ሰርቬይ ስርዐት መዘርጋት እና ማካሄድ፤
- ህዝብ በዐቃቤ ህግ መ/ቤት አገልግሎት ያለውን እርካታና አመኔታ ቢያንስ 1 ጊዜ የእርካታ ደረጃ ጥናት ማካሄድ እና 80% ማድረስ፤
- የወንጀል ጠቋሚዎችንና ምስክሮችን ጥበቃ ማድረግ፤ (እንደቀረበው)
- ከዐቃቤ ህግ መ/ቤት ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የዐቃቤ ህግ አገልግሎት ያለበትን ደረጃ በመለየት 2 ጊዜ የጋራ የንቅናቄና የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፤

**ግብ 4፡- የህግ ማሻሻያ ጥናት ምክር ማርቀቅና ማጠቃለል ተግባሮችን በመፈጸም የተቋሙን ውጤታማነት ማሻሻል፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በመንግስት ተቋማት ለሚቀርቡ የሕግ ምክር አገልግሎቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ 100% ምላሽ መስጠት፡
- ጥራታቸውን የጠበቁ የሕግ ረቂቅ አዘጋጅቶ 100% ለታለመለት አላማ እንዲውሉ ማድረግ፣
- የማህበራዊ ፍርድ ቤት ኃላፊነትን በመፈተሽ ወጥ በሆነ መልኩ ማጠናከር
- ለቀበሌ ማህበራዊ በዓመት 4 ጊዜ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- ለማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አግባብነት ያላቸውንና በሥልጣናቸው ሥር የሚወድቁ ጉዳዮችን ለይቶ በጥራዝ ሰንዶ መስጠትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ድጋፍ መስጠት
- በፌድራል ወጥተው በክልሉ ተፈጻሚ የሚሆኑትንና በክልሉ የወጡ ህግጋትን በማሰባሰብ ቅፅ 4ን ማሳተም እና ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እና ዘመናዊ በሆነ መል ማሰራጨት፤
- የሕግ ምክር ስታንዳርድ መርምሮ ማሻሻያ ማድረግ
- አሰጣጥ መመሪያ እና ስታንዳርድ ማውጣትና መተግበር
- የሕግ ምክር አሰጣጥ ሂደት ላይ በዓመት 1 ጊዜ የዳሰሳ ጥናት እና ግምግማ ማድረግ
- በመንግስት አካላት ሕግን የተከተለ አሰራር መኖሩን በክትትል ማረጋገጥ
- በተቀመጠው ጊዜ እና ጥራት የተሰጡ የሕግ ምክር፣ ጥናት እና ማርቀቅ
- የህግ ጥናትና ረቂቅ ዝግጅት ጥራት ማረጋገጫ መስፈርት መቅረጽና በክልሉ የሚወጡ ሕጎች በፍትሕ ቢሮው ታይተውየሚያልፉበትን ስርዐት ዘርግቶ መተግበር፤
- ከመንግስት አካላት ለሚቀርቡ የሕግ ማርቀቅ ጥያቄዎች የአግልግሎት በተቀመጠው ማንዋል መሰረት መተግበር
- በ2016 በጀት ዓመት የተመረጡ 7 አጫጭር የህግ ጥናትና ምርምር ጽሁፎችን ቀሪ የአርትኦት ስራዎችን በመስራት ለህትመት ማብቃትና 750 ኮፒ ማሰራጨት፤ (ፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን 2 የጥናትና ምርምር ስራዎችን መስራት፤(ፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ተቋም)
- የወንጀል ሥነሥርዓት እና የማስረጃ ህግን ለማስፈጸም የሚያስችሉ ዝርዝር አደረጃጀቶችን፣ አሰራሮችን እና ማኑዋሎችን መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ
- ምክረ-ሀሳብ የተሰጠባቸው ህጎች ላይ የተዘጋጀ የውሳኔ ሀሳብ ለክልል ምክር ቤት ማቅረብ
- የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት ህጉን ለክልል ም/ቤት አቅርቦ በማስጸደቅ እና ለመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች እና ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ተከታታይነት ያለው ስልጠና የሚሰጥበት ሥርዓትን መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ

- ጉዳዮች በአማራጭ ሙግት መፍቻ ሥርዓት የሚፈቱበትን ተቋማዊ መፍትሔ በጥናት መለየት፤ አግባብነት ላላቸው ተቋማት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ
- የአማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓቶች በሙያ ማህበራት ውስጥ እንዲቋቋሙ አስፈላጊው የህግ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት

**ዓላማ 3፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ የሙስና፣ መደበኛ እና ኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ወንጀል ፈፃሚዎችን በማስቀጣት የህ/ሰቡን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ፤**

የሙስና፣ መደበኛ እና ኢኮኖሚ ነክ ወንጀል ፈፃሚዎችን ጉዳይ ቀልጣፋ ውሳኔ በመስጠትና በፍ/ቤት ውጤታማ ክርክር በማድረግ አጥፊዎች ተገቢውን ማስተማሪያ ቅጣት እንዲሰጣቸው በማድረግ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማስተበቅ የሚሰሩ ስራዎችን የያዘ ዓላማ ነው፡፡

**ግብ 1፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ የወንጀል ምርመራ መዛግብት ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች መርምሮ የመወሰን/መዝገብ የማጥራት አቅም ከ98.05% ወደ 100% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- የፖሊስ የምርመራ መዛግብት ርክክብ ከመደረጉ በፊት በምርመራው ሒደት እና በተገኙ ማስረጃዎች ላይ ከመርማሪ ፖሊሶች ጋር በመነጋገር ማስረጃዎች 100% ተሟልተው እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- ከፖሊስ የተላከን የወንጀል ምርመራ መዝገብ ከ3 እስከ 5 ቀናት ውሰጥ መርምሮ ህጋዊ አስተያየትና ውሣኔ መስጠት፣
- የወንጀል ምርመራ ጋይድላይን ማዘጋጀት
- ለተጨማሪ ምርመራ ለፖሊስ የተላኩትን የምርመራ መዛግብት ተከታትሎ ማስመለስ፤
- ውስብስብና የአገርንና የመንግስትን ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ የሚጐዱ ወንጀሎችን በጋራ በቡድን በማጣራት፣የተጠርጣሪዎችን የስልክ፣ የፖስታና ሌሎች ሚስጥራዊ ግንኙነት እንዲጠለፍ የዉሳኔ ሃሳብ ማቅረብ እና በፖናል በጋራ አይቶ በመወሰን ውጤታማ ክስ ማዘጋጀት፣
- ውስብስብ በሆኑ የወንጀል መዛግብት፣ ሰበርና ይግባኝ ጉዳዮች፣ ከስር ዓቃብያነ ህግ በሚቀርቡ የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄዎች ላይ መወሰን፤

- በግብር እና ታክስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን የሚተዳደረው ዓቃቤ-ሕግ አጣርቶ የክስ አይቀርብም ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች 100% መርምሮ ለጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ማቅረብ፤
- በፌደራል መንግስት የወጣውን ፖሊሲ በክልሉ በአግባቡ የሚፈጸምበትን ስርዓት መዘርጋትና መተግበር ፓሊሲው በክልሉ እየተተገበረ ያለበትን ደረጃ፣ ክፍተቶች እና መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች የሚለይ ጥናት ማድረግ በጥናቱ ላይ ተመስረቶ የድረጊት መርሀ ግብር አዘጋጅቶ መተግበር
- የመወሰን / መዝገብ የማጥራት ቅልጥፍናን ከ98.05 ወደ 100% ማሣደግ፣
- የወንጀል መዝገቦች / ጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር (case flow management) መመሪያ / ማኑዋል ማውጣት / ማሻሻል እና መተግበር
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ በአካል ጉደተኞችና ሌሎች ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጎጂ በሆኑባቸው ላይ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን ማሳደግ፤
- ምንጩ ያልታወቀ ሀብትን አስመልክቶ የተጠያቂነት ሥርዓትን የሚዘረጋ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና መጸደቅ፡
- የወንጀል ውዝፍ መዛግብትን እና ኤግዚቪት ለማጥራት የሚያስችል ድርጊት መርሀ ግብር ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ፡-
- በተከሳሽ እና ምስክር አለመቅረብ የሚቋረጡ መዛግብትን የሚቀንስ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት
- በወንጀል ምርመራ ላይ መረጃ ሰጪ ከሆኑ ተቋማት ጋር የሚኖር ውጤታማ የግንኙነት ስርዓትን መቅረጽ እና ወደ ተግባር ማስገባት፡-
- ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የወንጀል ጉዳዮች ተለይተው በልዩ ትኩረት የሚሰሩበት ሥርዓት መፍጠርእና መተግበር፡-
- በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በገንዘብ መቀጮ የሚቀጡትን ለመንግስት ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ፡-

**ግብ 2፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ የወንጀል ምርመራ ጥራትና ቅልጥፍናን ወደ 96% ማድረስ፤**

- በየደረጃው በሚገኝ ፖሊስ በምርመራ ሂደት ላይ ላይ የሚገኙ መዛግብትን ብዛት፣ ውጤታማነት፣ ይዘት እና ያሉበትን ሁኔታ ምርመራ ክፍል የመስክ ጥናት ማድረግ መደገፍ እና አስፈላጊወን ትእዛዝና ውሳኔ መስጠት በአመት 2 ጊዜ፤
- በጥናት በተለዩ ከባድና ውስብስብና የአገርንና የመንግስትን ጥቅም በከፍተኛ ሁኔታ የሚጐዱ ወንጀሎችን በጋራ በቡድን ማጣራትና ለውሳኔ ማቅረብ፣

- የወንጀል ምርመራ መዝገቡ እንደቀረበ ከመርማሪው ጋር መረጃ መለዋወጥ ተጨማሪ ምርመራ የሚስፈልጋቸውን ለይ በአጭር ጊዜ ተሟልቶ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- የፖሊስ የምርመራ መዛግብት ርክክብ ከመደረጉ በፊት በምርመራው ሒደት እና በተገኙ ማስረጃዎች ላይ ከመርማሪ ፖሊሶች ጋር በመነጋገር ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲቀርቡ ማድረግ፤

**ግብ- 3፡- የስር ዐቃቤ ሕግ የክስ አይቀርብም ውሳኔወችንና መሪ ትእዛዞችን በመመርመር የውሳኔ ጥራትና ተጠያቂነትን 100% ማረጋገጥ፤**

**ዝርዝር ተግባራት**

- በየደረጃው የሚቀርቡ የመሪ ትዕዛዞችን መርምሮ በሕግ በማስረጃና ተቀባይነት ባላቸው ምክንያች የተደገፈ ውሳኔ በመስጠት ልዩነት በማጥበብ የውሳኔ ተገማችነትንና ጥራትን ማረጋገጥ፤
- በስር ዐቃቤ ህግ የተሰጡ የክስ አይቀርብምና ውሳኔዎችን በመመርመር የዐቃቤ ሕግን የውሳኔ ጥራትና ማረጋገጥ፤
- ግድፈት የሚታይባቸውን የክስ አይቀርብም ውሳኔወች በጥልቀት በማየት እንዲስተካከሉ መመሪያ መስጠት እና እንደግድፈቱ ሁኔታ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤

**ግብ 4፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ በወንጀል መዝገቦች የዓ/ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅም ከ91.81% ወደ 95.5% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- ዐቃብያነ ህግ ወደ ችሎት ከመግባታቸው በፊት ከአንድ ቀን በፊት መዝገብ ደርሷቸው አጥንተው ወደ ችሎት መግባት፣
- እጅ ከፍንጅ ወንጀሎችን በተፋጠነ ፍርድ አሰጣጥ ስርዓት /RTD/ እንዲቀርብ በማድረግ በጊዜ ማግኘት /የሚጠፋን/ ማስረጃ መቀነስ፤
- ሁሉም የችሎት ዓ/ህግ የችሎት ውሎውንና የፍ/ቤት ትዕዛዞችን፣ የችሎት ሪፖርት በአግባቡ መመዝገብ/ማቅረብ፣
- በሙስና ወንጀል የተገኙ ንብረቶችና ገንዘቦችን ለመንግስት ማስመለስና በፍ/ቤት እንዲወረሱ ማድረግ፤
- በወንጀል ከተጠረጠሩ ሰዎች በምርመራ ምክንያት በኤግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶች አፋጣኝ ውሳኔ ማስጠት፤

- በግብር እና ታክስ የወንጀል ክስ መስርቶ ባካሄዳቸው ክርክሮች ላይ ያስገኛቸውን ውጤቶች አስመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ማቅረብና በጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መፈጸም፤
- በግብር እና ታክስ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን የሚተዳደረው ዓቃቤ-ሕግ በፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈፀማቸውንና መከበራቸውን መከታተል፣
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ በአካል ጉደተኞችና ሌሎች ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የወንጀል መዝገባት የማስቀጣት ምጣኔን ከ91% ወደ 100% ማሳደግ፤
- የፍርድ ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፤
- የዕርቅና ድርድር ደንብ ማዘጋጀት፤
- በናሙና የክርክር መዝገቦች እና አዲስ በሚወጡ የወንጀል ሕጎች ይዘት ላይ ትምህርታዊ ጉባዔ እና የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት
- በስራ ላይ ያሉ እና አዲስ የሚወጡ የወንጀል ሕጎች በወቅቱ በተሟላ መልኩ ለዐቃብያነ - ሕጎች የሚደርሱበትን ስርዓት መተግበር
- ውስብስብ እና ከባድ የወንጀል መዝገቦች ክርክር በጋራ በፓናል የሚታዩበት መመሪያ ማውጣት እና መተግበር
- የወንጀል መዝገብ ክሶች የሚቋረጡበትን ዋና ዋና ምክንያቶች የሚለይ ጥናት ማድረግ
- የወንጀል መዝገብ ክስ ማንሳት እና ማቋረጥ መመሪያ ወይም ማኑዋል/ ጋይድቡክ ማዘጋጀት እና መተግበር
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የፍርድ ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፤

**ግብ 5፡- የሃብት ምርመራ መዛግብት መርምሮ የማጠናቀቅ ምጣኔ ወደ 76% ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ጥቆማዎችን ተቀብሎ በአግባቡ በመመዝገብ እና የሃብት ጥናት ሥራ በማከናወን ወደ ሀብት ምርመራ የሚገቡ ጉዳዮችን በአግባቡ መለየት፣
- የሃብት ምርመራ በሚያስፈልጋቸዉ ጉዳዮች የምርመራ ዕቅድ ከማዉጣት ጀምሮ ከወንጀል ምርመራ ጎን ለጎን የሀብት ምርመራ ሥራ ማከናወን፣
- የሃብት ምርመራ መዛግብትን ከወንጀል ምርመራ መዛግብት ጋር እኩል ለማጠናቀቅ መሥራት፣

- ከወንጀል ምርመራ መዛግብት ጋር እኩል የተጠናቀቁ የሀብት ምርመራ መዛግብትን ጉዳዩን ለያዘዉ የወንጀል ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ማስረከብ፣
- ከወንጀል መዝገቡ ጋር ያልተጠናቀቁ የሃብት ምርመራ መዛግብት በተጠናቀቁበት ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ የወንጀል ጉዳዩን ለያዘዉ ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ማስረከብ ወይም ዳይሬክቶሬቱ በራሱ ተገቢዉን ዉሳኔ መስጠት፣

**ግብ 6፡- የሃብት ምርመራ መዛግብት ላይ ውሳኔ የመስጠት አፈፃፀም ወደ 90% ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ምርመራቸዉ ተጠናቆ የጥፋተኝነት ውሳኔ ባገኙ ወይም ጥፋተኝነት ውሳኔ በህጉ አግባብ በማይጠበቅባቸው ማዛግብት ላይ ለሀብት ማስመለስ ዐቃቤ ሕግ ተላልፈው በተቀመጠዉ ጊዜ ዉሳኔ መስጠት፣
- በምርመራ መዛግብት ላይ ጥራት ያለዉ ዉሳኔ መስጠት፣

**ግብ 7፡- የሀብት ማስመለስ ክስ የተመሰረተባቸው መዛግብት የመርታት ምጣኔ ወደ 95% ማድረስ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የሀብት ምርመራቸው ተጠናቆ የውርስ ውሳኔ ለማሰጠት ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ውርስ አቤቱታዎች ሀብት እንዲወረስ ማስወሰን
- የዉርስ ዉሳኔ የተሰጠባቸዉ መዛግብትን መነሻ በማድረግ በተቀመጠዉ የአፈጻጸም ክስ ማቅረብ ፣
- የዉርስ ዉሳኔ ያልተሰጠባቸዉ እና ተከሳሾች የተቀጡባቸዉ መዛግብትን መነሻ በማድረግ የዉርስ አቤቱታ በማቅረብና በመከራከር ማስወሰን
- በተለያየ መንገድ የተቋረጡ የወንጀል መዛግብትን መነሻ በማድረግ የፍትሐብሔር ክስ እንዲቀርብባቸው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ  የፍትሐብሄር ክስ በማቅረብ ማስወሰን

**ግብ 8፡- የሃብት ምርመራ በሚደረግባቸዉ መዛግብት የወንጀል ፍሬ የሆነን ወይም የጉዳት ማካካሻ ንብረት 90% ማድረስ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የተከሳሽ ንብረት ላይ አስቀድሞ የሀብት ጥናት ማከናወን፣
- የወንጀል ፍሬ የሆነዉን ወይም በወንጀል ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ ሊሆን የሚችል ተመጣጣኝ ንብረት ማሳገድ፣

**ግብ 9፡- የታገዱና የተያዙ ንብረቶች በአግባቡ ተጠብቀዉ የተያዙ ስለመሆኑ ማረጋገጥ**

**የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- የተያዙ ንብረቶች በአግባቡ ተጠብቀዉ የሚቀመጡበት ቦታ ማዘጋጀት ፣
- የተየያዙ ንብረቶች ሳይጉዱና ሳይበላሹ መቀመጣቸዉን የማረጋገጥ ሥራ መሥራት፣
- አስተዳዳሪ ሊሾምላቸዉ የሚገቡ ንብረቶች ወይም ቢዝነሶች ላይ አስተዳዳሪ ማሾም፤

**ግብ 10፡- የዐቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት ከ87.62% ወደ 88.0% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በይግባኝም ሆነ ሰበር አቤቱታ የሚቀርቡ ውስብስብ እና ከባድ የወንጀል ጉዳዮችን ቅሬታ በጋራ በፓናል በማየት አሣማኝ የህግና የፍሬ ነገር ጉዳዮች በማንሣት የተሣሣተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ማስለወጥ፡፡
- የስር ዐቃብያነ ህግ በሚያቀርቡት ይግባኝ ቅሬታና ሰበር አቤቱታ ላይ ፍርድ ቤቱ አያስቀርብም ትዕዛዝ ሲሰጥ ወይንም ጉዳዩን ውሳኔ ሲሰጥ ቅሬታውን ወይንም አቤቱታውን እንዲያውቀው ማድረግ፤
- በይግባኝም ሆነ ሰበር አቤቱታዎች በቂ ዝግጅት አድርጐ ችሎት በመግባት ውጤታማ ክርክር ማድረግ፣
- የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ መዛግብት ውጤታማነት በመለየት 1 ጊዜ በማጥናት ሁሉም ዓ/ህግ ከድክመትና ጥንካሬዎች ትምህርት እንዲወሰድ ማድረግ፡፡
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዓ/ህግ ይግባኝ እና ሰበር የጠየቀባቸው መዝገቦች አፈጻጸም ውጤታማነትን ከ78.47% ወደ 95% ማሳደግ፤

**ግብ 11፡- የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነት ከ86.76% ወደ 89% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በተከሣሽ በሚቀርቡ የይግባኝ ወይም ሰበር አቤቱታዎች መዝገቦች የቀረበውን መቃወሚያ ከስር ዓ/ህግ ክስ እና የፍ/ቤት ውሣኔ እንዲሁም አግባብ ካለው ህግና ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን መልስ ማቅረብ፣
- በይግባኝም ሆነ ሰበር አቤቱታዎች በቂ ዝግጅት አድርጐ ችሎት በመግባት ውጤታማ ክርክር ማድረግ፣
- የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ መዛግብት ውጤታማነት በመለየት 1 ጊዜ በማጥናት ሁሉም ዓ/ህግ ከድክመትና ጥንካሬዎች ትምህርት እንዲወሰድ ማድረግ፡፡

**ግብ 12፡- በቀዳሚ ምርመራ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች 100% ማስረጃ እንዲጠበቅ በማድረግ አጥፊዎችን በህግ ፊት ተጠያቂ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህጉ መሠረት በቀዳሚ ምርመራ መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ወድያውኑ ዐቃቤ ህግ በመመደብ እንዲከታተለው ማድረግ፣
- በቀዳሚ ምርመራ፣ በሚታዩ ጉዳዮች አቀራረብ እና የማስረጃ አያያዝ ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- በቀዳሚ ምርመራ የተመዘገበን ማስረጃ በመጠቀም በማስረጃ እጦት ምክንያት አጥፊዎች ከተጠያቂነት እንዳያመልጡ አትኩሮት ሰጥቶ መስራት፣

**ግብ 13፡- በፌዴራል ውክልና እና በክልል ጉዳዮች በቀጥታ ክስ ተከሣሽ፣ ምስክር፣ መልስ ሰጭ እና ተጠሪ አቀራረብን በማጠናከር የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን ከ11.35% ወደ 3.5% ዝቅ ማድረግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- የፍ/ቤት ቀጠሮ ከመድረሱ በፊት የፍ/ቤት የምስክር እና ተከሣሽ መጥሪያ ለፖሊስ መድረሱን ማረጋገጥ፣
- በተከሣሽና ምስክር አለመቅረብ በተደጋጋሚ የተቀጠሩ የክስ መዛግብትን በመለየት ለፖሊስ ማሣወቅ፣
- በተከሣሽና ምስክር አቀራረብ የሚታዩ ችግሮችን በጋራ ኮሚቴው መድረክ በመገምገም የተጠያቂነት አሠራርን ማጠናከር፣
- ተከሣሽ በሌለበት ውሣኔ ማሰጠት በሚቻልባቸው የወንጀል ክሶች ተከሣሽ በሌለበት ውሣኔ እንዲሰጥበት ለፍ/ቤት በማሣሰብ ውሣኔ ማሰጠት፣
- በተከሣሽና ምስክር አለመቅረብ የተቋረጡ መዛግብትን ለይቶ ለፖሊስ በማሣወቅና በጋራ መድረክ በመገምገም የተዘጉ መዛግብትን መልሶ ማስከፈት፣
- የወንጀል ጠቋሚዎች እና ምስክሮች ጥበቃ አሰራር መዘርጋት፡-
- ምስክሮች ያለባቸውን ስጋት ቀንሶ ለምስክርነት ተባባሪ እንዲሆኑ ለማስቻል የምስክሮችን መብት ጥበቃ ስርዓት ማጠናከር፣
- በሴቶች፣ የህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች መቋረጥ ምጣኔን መቀነስ፤
- ተከሣሽ፣ ምስክር፣ መልስ ሰጭ እና ተጠሪ በቀጠሮዎች የመቅረባቸውን መጠን የሚያሳድግ ስልት ነድፎ መተግበር

**ግብ 14፡- በሚቀርቡ የዋስትና ጉዳዮች ላይ ቀልጣፋና ህጋዊ አስተያየት 100% በመስጠት እንዲከበር ማድረግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ ወይም የተከሰሱ ሰዎች በሚያቀርቡት የዋስትና ጥያቄ አጣርቶ በ1ሰአት ውስጥ ውሣኔ መስጠት፣
- በዋስትና ጥያቄው ላይ አስተያየት ከመሰጠቱ በፊት እንደ አግባብነቱ የምርመራ መዝገቡን አስቀርቦ ማየት ወይም ተገቢውን ማስረጃ ከመርማሪ ፖሊስ መቀበል፣
- በዋስትና ጥያቄው ላይ የተሰጠው አስተያየት በማስረጃ የተደገፈና ህግን መሠረት ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በዋሶች የሚቀርብ ዋስትና ይነሳልኝ ወይም በዋስትና የተያዘ ንብረት ይለቀቅልኝ የሚል አቤቱታ ለፍ/ቤት ቀርቦ መልስ እንዲያቀርብ ሲታዘዝ መልስ በማቅረብ ክርክር ማድረግ፤

**ግብ 15፡- የወንጀል አቤቱታ አቀባበል ውሣኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነት 97.06% ወደ 98%ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- በወንጀሎች ቅጣት የሚያስከትሉ ድርጊቶች የተፈፀሙ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ በመኖሩ ወይም ጥቆማ በቀረበ ጊዜ ተገቢው ምርመራ ተጣርቶና በበቂ ማስረጃ ተደግፎ እንዲቀርብ ማድረግ፤
- የወንጀል አቤቱታዎችን እንደ አግባብነቱ በተዘጋጀው የአቤቱታ መቀበያ ፎርማት መሠረት በስልክ፣ በአካል ወይም በፋክስ መዝግቦ መቀበል፣
- የቀረበው አቤቱታ ወዲያውኑ በጽ/መ/አስ/ር ባለሙያ ተመዝግቦና ፋይል ተከፍቶለት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን ለአለው ባለሙያ መቅረቡን ማረጋገጥ፣
- በቀረበው የወንጀል አቤቱታ ላይ እንደ አግባብነቱ በ1ሰአት ውስጥ አጣርቶ ምላሽ መስጠት፣
- በቀረበው አቤቱታ ላይ ህጋዊና የማያዳግም ምላሽ መስጠት፣ የተሰጠውን ትዕዛዝ ተፈፃሚነት ተከታትሎ ማረጋገጥ፣
- ተደጋጋሚ አቤቱታ የሚቀርብባቸው ጉዳዮች እና አካባቢዎችን በመለየት የችግሩን መነሻ አውቆ መፍትሄ መስጠት፣
- የወንጀል ባልጉዳዮች አግልግሎት አሰጣጥ እና አያያዝ ማንዋል ማዘጋጀት
- የተገልጋይ ቅሬታ መቀበያ እና አስተያየት ማሰባሰቢያ ስርዓትን ማጠናከር፤ በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት የማሻሻያ እርምጃዎች መውሰድ፤

**ግብ 16፡- የይቅርታ አሰጣጥ ጥራትና ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት**

- ከታራሚዎች የሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎች አንድን የይቅርታ ጥያቄ ላይ አስተያየት ለመስጠት በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ እንዲያገኙ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናውን ማድረስ፣
- ለቀረበው የይቅርታ ጥያቄ የሚሰጠው አስተያየት ከህጐችና ከተቀመጠው መስፈርት አንፃር የተቃኘ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ መስራት፣
- በእስራት ዘመናቸው በስነምግባር የታነጹና በሰሩት ድርጊት የተጸጸቱ ታራሚዎችን በማጥናት ይቅርታ እንዲዳረግላቸው ለይቶ ማቅረብ፣
- የይቅርታ ቦርድን እና የይቅርታ ጽ/ቤት በተገቢው የሰው ኃይል በማደራጀት በህግ የተጣለበት ኃላፊነት በአግባቡ መወጣቱን ማረጋገጥ፣
- የማረሚያ ቤቶችን የዕርምት አሰጣጥ በመከታተል በአግባቡ የታነፁ እና የባህሪ ለውጥ ያመጡ ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከይቅርታ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አጣርቶ አግባብ ያለው ምላሽ መስጠት፣
- በይቅርታና በአመክሮ የተለቀቁ ታራሚዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን አኗኗር በማጥናት የተረጋጋና ሰላማዊ ህይወት እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- ክልላዊ የይቅርታ ምልመላ እና አሰጣጥ ስርዓቱ ተገማች፣ ግልፅና ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ እንዲሆን የሚያስችል አሰራር መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ

## ዓላማ 4፡-በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ጉዳዮች የመንግስትና የህዝብን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ

በፍትሃብሄር ጉዳዮች ቅድመ መከላከል ስራዎችን መስራት፣ የህዝብንና የመንግስትን ገንዘብ በድርድርና በህግ ክርክር በማድረግና በማስመለስ የመንግስትንና ህዝብን ጥቅም ለማስከበር የሚከናወኑ ተግባራትን የያዘ ዓላማ ነው፡፡

### ግብ 1፡- በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ስራን በማጠናከር የመንግስትና የህዝብን ሀብትና ንብረት ከብክነት መከላከል በመዝገብ 100% የነበረውን ማስቀጠል፤

### የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

- የህግ ባለሙያ ከሌላቸው ተቋማት ውጭ ሁሉንም የመንግስት ተቋማት እንደ ጉዳያቸው ፍሰት ደረጃ በህግ ጉዳዮች ድጋፍ የሚያደርግላቸው ዐቃቤ ህግ መድቦ መከታተል፡፡
- በተገልጋዩች የሚቀርብን የረቂቅ ውል ምርመራ እና የውል ሰነድ ዝግጅት በ5 ቀን ውስጥ በማዘጋጀት ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት፣

- የመንግስት መ/ቤቶችንና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የልማት ድርጅቶችን የህግ ምክርና ድጋፍን ጥያቄዎችን ተቀብሎ በጥናት ላይ ተመስርቶ ምላሽ በመስጠት ማከናዎን፣
- አገልግሎት ፈላጊዎች የሚያቀርቧቸውን ውሎች በአግባቡ መርምሮ ህጋዊ መሠረት እንዲይዙ በማድረግ በውል አያያዝ ክፍተት ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን መቀነስ፣
- በአገልግሎት ፈላጊዎች የሚቀርቡ የህግ ምከር አገልግሎት፣ ረቂቅ ውል ምርመራ፣ እና የውል ሰነድ ዝግጅት በአግባቡ ተመዝግቦና በውጤት እየተለካ መሠራቱን ማረጋገጥ፣
- በፍትሐብሄር ጉዳዮች አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የግምገማ ሰነድ በማዘጋጀት ከመንግስት ተቋማት ጋር በዓመት1 ጊዜ የምክክር መድረክ ማካሄድ፣
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን በውል ዝግጅትና የህግ ምክር ድጋፍ መስጠት፤
- በፍትሐብሄር ጉዳዮች ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ጋር ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ እና የትብብር ስርዓት መዘርጋት
- በእያንዳንዱ የፍትሐብሄር የሕግ አገልግሎት ሒደት የተገኙ መልካም ውጤቶችን እና እንቅፋቶች በየዓመቱ የዳሰሣ ጥናት/ ግምገማ ሰነድ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማካሄድ
- በፍትሐብሄር ጉዳዮች የተገልጋይ ቅሬታ መቀበያ እና አስተያየት ማሰባሰቢያ ስርዓትን ማጠናከር
- የህግ ድጋፍ ስርዓትን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ
- የፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደር የአሰራር ማንዋል ማዘጋጀትና ማጽደቅ

**ግብ 2፡- በፍትሐብሄር ከምንይዛቸው ጉዳዮች ውስጥ በድርድር መጨረስ በመዝገብ 18.84% የነበረውን ወደ 28.0% ማሳደግ፤**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- የድርድር ጋይድላይን ማዘጋጀት
- በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን ድርድርን ጨምሮ የፍትሐብሄር ጉዳዮች የሚመሩበት ደንብ በማስፀደቅ ውጤታማ የድርድር ስርዓት መዘርጋት፣
- በየደረጃው ያሉት የመንግስት ተቋማት ኃላፊዎችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተወካዮች ጉዳዮችን በድርድር መጨረስ አስፈላጊነትና ፋይዳን ማስገንዘብ፣
- ከሣሽም ሆነ ተከሣሽ በሆንባቸው ጉዳዮች አግባብ ያለው ማስረጃ መሠብሰቡን ከአረጋገጥን በኋላ ክስ ወይም መልስ ከመቅረቡ በፊት ሁሉንም ጉዳዮች በድርድር ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣

- ክስ ከተመሠረተ የክስ መልስ ከተሰጠ በኂላም ጉዳዩን በድርድር መጨረስ አዋጭ በሚሆንበት ጊዜ ጉዳዮን በድርድር ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣
- በድርድሩ ውጤት መሠረት ለመንግስት ወይም ነጻ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ ገቢ መደረጉን ተከታትሎ ማስፈፀም፣
- በድርድር ሒደት የተገኙ መልካም ውጤቶችን እና እንቅፋቶች በየዓመቱ የዳሰሣ ጥናት/ግምገማ ሰነድ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማካሄድ፡፡
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በድርድር መጨረስ፤
- ለሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ በድርድር ያለቁትን ገቢ ማድረግ፤

**ግብ 3፡- የክስ አመሠራረትና መልስ አቀራረብ ቅልጥፍናን /መዝገብ የማጥራት አቅም/ በመዛግብት 99.19% የነበረውን ወደ 100% ማድረስ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

- ከሣሽ ወይም መልስ ሰጭ በሆንባቸው ጉዳዮች አግባብ ያላቸውን ማስረጃዎች በማሰባሰብ በ12 ቀናት ውስጥ በመዝገቡ ላይ ውሣኔ መስጠት፣
- ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮችን በጋራ በፓናል አይቶ የመንግስትንና የህዝብ ጥቅም ማስጠበቅ ወይም ጉዳትን መቀነስ የሚያስችል የውሣኔ አማራጮች በማቅረብ መወሰን፣
- ክስ ለመመስረት ወይም /ስንከሰስ/ መልስ ለመስጠት የሚያበቁ የሰነድ፣ የሰው እና ሌሎች ማስረጃዎችን በተገቢው መንገድ በመመዘን አዋጭ ክስና መልስ ማቅረብ፣
- ክስ በማናቀርብባቸው ወይም ደግፈን በማንከራከርባቸው የስርዓ/ህግ ይግባኝ መዝገቦች አግባብ ያለው ግብረ-መልስ ለተቋሙ ወይም ለስርዓ/ህግ በመስጠት የራሣቸውን መፍትሄ እንዲወስዱ ማድረግ፣
- ሁሉም ዓ/ህግ የተመራለትን መዝገብ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ ውሣኔ ሰጥቶ እስከ መለሰበት ጊዜ ድረስ በመዝገቡ መከታተያ ሰንጠረዥ ተግባሩን በውጤት ለክቶ መመዝገቡን ማረጋገጥ፣
- በሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ በአካል ጉደተኞችና ሌሎች ልዩ ትኩረት በሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጎጂ በሆኑባቸው ላይ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን ማሳደግ፤

**ግብ 4፡- በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስና መልስ የዓ/ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅም በመዝገብ 91.0% ወደ 92% ማሣደግ፣**

**የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት**

